# ጅቡቲ

## የጥገኝነታችን መስፈሪያ

በለጠ በላቸው ይሁን

© መፅሐፉን በሙሉም ሆነ በከፊል ያለ ፀሐፊው ፈቃድ መልሶ ማሳተም በሕግ የተከለከለ ነው።
2006 ዓ.ም.

ምስጋና

- የመፅሐፉን ረቂቅ በማረም እና ገንቢ አስተያየታቸውን በመለገስ ላገዙኝ ለወ/ሮ ወርቀዘቦ ተገኝ እና ለአቶ በላቸው ይሁን
- ይህንን መፅሐፍ ለህትመት በሚሆን መልኩ ላሰናዳልኝ ለአቶ አያሌው ወርቁ

ለአስተያየትዎ: beletebelachewm@gmail.com

# ለ ወርቀዘቦ

ማውጫ ገፅ


መቅድም ......7

1. ምዕራፍ ፩፡ መግቢያ ......14

2. ምዕራፍ ፪፡ ጅቡቲን የማጣት መጀመሪያ ......27

   2.1. የፈረንሳይ ሱማሌ ግዛት ጅምር ......27

   2.2. የድንበር መካለል ......35

   2.3. የጅቡቲ የውስጥ ፖለቲካ ጅምር ......43

   2.4. የታላቋ ሰማሌ ህልም፣ የግብፅ ምኞት እና የቀዘቀዘው ጦርነት ተፅዕኖ....48

3. ምዕራፍ ፫፡ የኢትዮጵያ ፖሊሲዎች ዳሰሳ ......54

   3.1. የአፄ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት ......54

   3.2. ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ እና ጅቡቲ ......85

   3.3. ድህረ-1983 የግንኙነት አቅጣጫ ......122

4. ምዕራፍ ፬፡ ጅቡቲ–አዲስ አበባ ምድር ባቡር ......128

   4.1. የባቡር መሥመሩ ህልውና ጅምር ......128

   4.2. ደርግ እና የጅቡቲ-አዲስ አበባ ምድር ባቡር ......135

5. ምዕራፍ ፭፡ የጅቡቲ ወደብ፡ የጥገኝነታችን ቁልፍ ......163

   5.1. በጅቡቲ ወደብ የመጠቀም መብት በንጉሳዊያን ዘመን ......163

   5.2. ደርግና የጅቡቲ ወደብ ......169

   5.3. ድህረ-1983 ገፅታ ......178

6. ምዕራፍ ፮፡ መደምደሚያ ......199

   ዋቢ ጽሑፎች ......218

# መቅድም

በቀይ ባህር ደቡባዊ ጫፍ ወደ ህንድ ውቅያኖስ መዳረሻ የሚገኘው የጅቡቲ የጠረፍ ግዛት ኢትዮጵያን ከሚያዋስኑ መንግስታት በመጠን ትንሹ ነው። ከኢትዮጵያ ጋር ረጅም ወሰን ከሚጋሩት እንዲሁም ታሪካዊ ቁርኝታቸው ጎልቶ ከሚታዩ እንደ ሱዳን፣ ሶማሊያ እና ኬንያ ካሉ አገሮች ሲወዳደር ጅቡቲ ዝቅተኛ ግምትና ቦታ ይዞ የቆየ እና የተረሳ ይመስል ነበር። ግዛቱ ካለው አነስተኛ የህዝብ ቁጥር፣ የተፈጥሮ ሐብት ወዘተ አንፃር ሲገመት በእርግጥም እዚህ ግባ የሚባል ፋይዳ ያልተሰጠው ቢመስል አያስገርምም። ይህ ግምት በአብዛኛው ኢትዮጵያዊ ዘንድ የሚስተዋል ሲሆን አገሪቱን በመሩ ተከታታይ መንግስታት የግንኙነት ታሪክ ውስጥም ተንፀባርቋል።

በኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነት ታሪክ ውስጥ በተለምዶ የቀዳሚነት ቦታ ሲሰጣቸው የቆዩ ሌሎች የጎረቤት አገሮች ያላቸው ሁለንተናዊ ባህሪይ የጅቡቲን ወሳኝነት ማደብዘዙ ዕሙን ነው። የሶማሊያ ሪፐብሊክ ሲያራምደው የቆየው የታላቋ ሱማሌ መርህና አጋዴንን ወደ ግዛቱ የመጠቅለል ምኞት ዋነኛው የትኩረት ነጥብ ሆኖ ቆይቷል። ይህንንም አደጋ ለመቀልበስ በኢትዮጵያ በኩል ዘርፈ ብዙ መስዋዕትነት ተከፍሏል። ከሱዳን መንግስታት ጋር ሲያወዛግብ የቆየው የድንበር ክለላ ጥያቄ ብሎም ተከታታይ የካርቱም መንግስታት ደፋ የሆነ የኤርትራ ተገንጣዮችን ዓላማ መደገፍ እና ሌሎች ተቃዋሚ ኃይሎችን ማበረታታቸው ወዘተ በኢትዮጵያ በኩል የቅድሚያ ትኩረት እንዲያገኝ መንገድ ከፍቷል። በተለይ የሶማሊያና የኤርትራ ጉዳይ የተከታታይ የኢትዮጵያ መንግስታት ዋነኛ የውጭ ፖሊሲ አጀንዳ መሠረት ሆኖ እስካለንበት ወቅት ዘልቋል። ከኬንያ ጋር መመስረት የተቻለውን የወዳጅነት እና የትብብር ግንኙነት ጠብቆ ማቆየቱም የዘውትር ክትትል የሚሻ ጉዳይ ነበር። የዚህ አከባቢያዊ ውጥረት አንዱ ውጤት ለጅቡቲ የተሰጠው ትኩረት በአንፃራዊ መልኩ የተቀዛቀዘ መምሰሉ ነው።

የአውሮፓ ቅኝ ገዢዎች ወደ አፍሪካ ቀንድ መምጣትን ተከትሎ በአካባቢው የተፈጠረው አጠቃላይ ውዥንብር እና ቀውስ ኢትዮጵያ በጅቡቲ ላይ በነበራት እይታ ላይ የራሱን ተፅዕኖ ማሳደሩ አልቀረም። እንግሊዝ እና በተለይ ጣሊያን በአገሪቱ ላይ የፈጠሩት የተስፋፊነት አደጋ የኢትዮጵያ ትኩረት በተለይ እነዚህ አገራት ካስተዳደሯቸው የጎረቤት ግዛቶች ወደሚመጣው ችግር እንዲያተኩር መንገድ ከፍቷል። በኤርትራ፣ ሱዳንና ሶማሊያ ለተፈጠሩ ክስተቶች እና እነኚህ ክስተቶች በቀጣይ ጊዜያት በኢትዮጵያ ህልውና ላይ ላስከተሉት አሉታዊ ተጽዕኖ ዋነኛ መነሻዎቹ እንግሊዝ እና ጣሊያን እንደነበሩ እሙን ነው። በተቃራኒው ሦስተኛዋ ቅኝ ገዢ ፈረንሳይ ከኢትዮጵያ መንግስታት ጋር የመሠረተችው የወዳጅነት ግንኙነት ስለ ጅቡቲ የነበረውን አቀራረብ በእጅጉ ወስኖታል።

በተቀሩት የጎረቤት ቅኝ ግዛቶች የነበረው ውጥረት እና ከነፃነት በኋላ የተከሰተው አደጋ በጅቡቲ በኩል እንዳይደገም የኢትዮጵያና የፈረንሳይ የወዳጅነት ግንኙነት አስተዋፅኦ አበርክቷል። ይህ እውነታ በተለይ እስከ 1967 አብዮት ድረስ ዘለቀ። ምንም እንኳን ከአጠቃላይ የቅኝ ግዛት ፖለቲካ ውጥረቱ ኢትዮጵያ ተጎጂ ሆና መውጣቷ ዕሙን ቢሆንም በተለይ ጅቡቲን በተመለከተ ሂደቱ የተለሳለሰ እና ያልለየለት ሆኖ እስከ መጨረሻው እንዲዘልቅ ምክንያት ሆኗል። ይልቁንም ጅቡቲ የኢትዮጵያ ሉዓለዊ የግዛት ክልል እንደሆነች ሲታመን ቆየ፤ ግዛቱ ለዘለቄታው ሲታጣም ጉዳቱ በእጅጉ የሚቆጠቁጥ ሆነ።

ተከታታይ መንግሥታት ስለ ጅቡቲ የነበራቸው አመለካከት እንዲሁም ይህ እሳቤ በኢትዮጵያውያን ላይ ያሳደረው እምነት ግዛቱ ለዘለቄታው ሲታጣ ከተከሰተው ግራ መጋባት ጋር በእጅጉ የተቃረነ እንዲሆን መንገድ ከፈተ። ከየትኛውም የጎረቤት አገር በበለጠ የኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ህልውና ከጅቡቲ ጋር የተሳሰረ ሆኖ ቆይቷል። ወደቡ እና የባቡር ሃዲዱ የአገሪቱ ዋነኛ የወጪ እና ገቢ ንግድ መስመሮች ሆነው አገልግለዋል፣ እያገለገሉም ነው። ይህ እውነታ የኢትዮጵያ ሉዓላዊ ወደቦች - ምፅዋና አሰብ - ይሰጡት ከነበረው አገልግሎት በእጅጉ የላቀ ነበር። ከኤርትራ





ነፃነት በተለይም ከ1990-1992 የሁለቱ አገራት ጦርነት በኋላ ደግሞ ጅቡቲ አማራጭ የሌለው የንግድ በር ሆነ። በዚህም የተነሳ ግዛቱ የስትራቴጂ መሥመር እና የኢኮኖሚ ህልውና መሠረት ሆኖ ቆየ።

የቅርብ ጊዜ ታሪካችን በግልፅ እንደሚመሰክረው የተከታታይ መንግስታት የትኩረት አቅጣጫ በአመዛኙ የባህር በር ጥያቄን በማያዳግም መንገድ መመለስ ላይ ወይንም ከዚህ ጋር የተያያዙ ውጥረቶችን በመፍታት ላይ ያተኩራል። በአፄ ቴዎድሮስ፣ ዮሐንስ አራተኛና ምንሊክ ዘመነ መንግስታት ከእንግሊዝ፣ ግብፅና ጣሊያን ጋር የተደረጉ ጦርነቶች አንዱ መገለጫ ሉዓላዊነትን ከማስከበርም ባሻገር በቀይ ባህርና በህንድ ውቅያኖስ ዳርቻ ላይ ቋሚ የንግድ በር የማግኘት ጥረት ነበር። አፄ ምንሊክ እ.ኤ.አ. በ1891 ለታላላቅ መንግስታት መሪዎች ያስተላለፉት ዘዋሪ ደብዳቤ የአገሪቱን የግዛት ዳርቻ ከመግለጽም ባሻገር የባህር በር ድርሻ እንደሚገባት ያበክራል። አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኮንን በእንግሊዝ፣ ፈረንይና ጣሊያን በ1916 ያደረጓቸው መንግስታዊ ጉብኝቶች ዋነኛ ምክንያትም እነዚህ ኢትዮጵያን ከበው የያዙት ቅኝ ገዢዎች ከግዛታቸው ቆርሰው የመተላለፊያ በር ሊሰጡ የሚችሉበት እድል እንዳለ ለመዳሰስ እንደነበር ይታወቃል።

በ1946 ኤርትራ በፌዴሬሽን ወደ ኢትዮጵያ ከተቀላቀለች በኋላ ለረጅም ጊዜ ታጥተው የነበሩትን የምፅዋና አሰብ ወደቦች መልሶ ማግኘት ተቻለ። ይህ ለአገሪቱ ታላቅ ስኬት ቢሆንም ከጥቂት ዓመታት በኋላ በኤርትራ የተጀመረው የትጥቅ ትግል ወደቦቹ ሊሰጡት የሚችሉትን አገልግሎት በእጅጉ ቀነሰው። ከውስጣዊው ችግርም ባሻገር በተለይ ከመካከለኛው ምሥራቅ አገራት የተሰነዘረው ቀይ ባህርን በብቸኝነት የአረብ ባህር የማድረግ ዘመቻ የወደቦቹን ግልጋሎት ከማቀጨጭ አንፃር ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክቷል። በዚህ አስቸጋሪ ወቅት አገሪቱ በአሰብ ወደብ በአንጻራዊነት የተጠቀመችበት ቢሆንም የወጪና ገቢ ንግድን ከማቀላጠፍ አንጻር ግን ወደቦቹ የተፈለገውን ያክል ሚና ሊጫወቱ አልቻሉም።

ከሰላሳ ዓመታት ጦርነት በኋላ ኤርትራ ነፃ አገር ስትሆንም ችግሩ ዘላቂ መፍትሄ ሳይሰጠው ታለፈ። በኢትዮጵያና አድሲቷ ኤርትራ መካከል ተመስርቶ በነበረው ጊዜያዊ ወዳጅነት መሠረት አሰብን በተለይ ለመጠቀም ተችሎ ነበር። ይህ የልዩ ተጠቃሚነት መብት ግን በተጨባጭ ውል ላይ ሳይሆን በመንግስታቱ መካከል በነበረው መቀራረብ ላይ ብቻ የተንተራሰ ስለነበር ብዙም ሊዘልቅ አልቻለም። በግንቦት 1990 የመንግስታቱ ግንኙነት በድንገት ከፍፁማዊ ፍቅር ወደ ለየለት ጠላትነት ለማምራቱ ዋነኛው ምክንያት የአሰብ የወደብ አጠቃቀም ጉዳይ ሆነ። የዚህ ሁሉ እውነታ ድምር ውጤትም አስደናቂ በሆነ መንገድ ከቀይ ባህርም ይሁን ከህንድ ውቅያኖስ በአስርትና መቶ ኪሎ ሜትሮች ርቀት ላይ የምትገኝ የባህር በር አልባ አገር መፈጠር ነው። ሌላኛው እውነታ ደግሞ የጅቡቲ ወደብ እና የባቡር ሐዲዱ ከተቀረው ዓለም ጋር ለመገናኘት ብቸኛ አማራጭ ሆነ።

በዘመናዊው ኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ጅቡቲን ዋነኛ የንግድ በር ሆኖ ለመቆየት ያስቻሉ አሳማኝ ምክንያቶች ነበሩ። ቀዳሚው ምክንያት የአገሪቱ በቅኝ ገዢዎች ከበባ ሥር መዋል ነው። ይህ እውነታ ከቀጥተኛ አገዛዝ በመለስ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚያዊ ህልውና በአውሮፓውያኑ ቁጥጥርና ተፅዕኖ ሥር እንዲሆን መንገድ ጠረገ። ተያይዞም በፍጥነት እየተቀያየረ በመጣው የዓለም የፖለቲካና የኢኮኖሚ መስተጋብር ውስጥ የሉዓላዊ አገርን ቁመና ለማስጠበቅ ወሳኝ የሆነውን የባህር በር የማግኘቱ አማራጭ አጣብቂኝ ገጠመው። ኤርትራን መልሶ ማግኘት እስከተቻለበት እስከ 1940ቹ አጋማሽ ድረስም ጅቡቲ ብቸኛው ከተቀረው ዓለም ጋር የመገናኛ በር ሆኖ ቆየ። ይህም እውነታ በፈረንሳይ በጎ ፈቃድ ላይ ብቻ የተመሠረተ ነበረ።

በነዚህ ጊዜያት ኢትዮጵያ ተደጋጋሚ የወረራ አደጋ ተጋርጦባት የነበረ መሆኑና ይህንንም ለመቀልበስ የከፈለችው መስዋዕትነት የአገሪቱን ለአደጋ ተጋላጭነት በይፋ ያሳየ ነበር። ከግብፆች፣ ደርቡሾችና ጣሊያኖች የተቃጣ መስፋፋቶችን ለመቀልበስ የተቻለው በጅቡቲ በር ለመጠቀም እና የጦር መሳሪያ





ለማስገባት በመቻሉ መሆኑ ግልፅ ነው። በተለይ አፄ ምኒሊክ በ1888 ጣሊያንን አድዋ ላይ ለማሸነፋቸው አንዱና ዋነኛው ምክንያት በጊዜው ጦራቸውን ሊያስታጥቁ የቻሉት ዘመናዊ መሳሪያ ነበር።

በወቅቱ ከወራሪው ኃይል እምብዛም የማይተናነሰውን ትጥቅ ለማግኘት የተቻለው ከፈረንሳይ መንግስት ጋር ሊመሠርቱት በቻሉት ጥብቅ ወዳጅነትና በጅቡቲ በር ለመጠቀም የሚያስችል የልዩ ተጠቃሚነት መብት ማስከበር በመቻላቸው መሆኑ አያከራክርም። ይህንን መብት ማስጠበቅ ባልተቻለባቸው ጊዜያት ደግሞ የአገሪቱ ህልውና ታላቅ አደጋ ሲጋረጥበት ቆይቷል። በአንፃራዊነት ወዳጅ የነበረችው ፈረንሳይ ጀርባ በሰጠችበት ወቅት ከ1928 እስከ 1933 ባሉት አምስት ዓመታት ኢጣሊያ በቀላሉ ኢትዮጵያን መያዝ ችላ ነበር። እንዲሁም የሲያድ ባሬ ሶማሊያ ወረራ በፈፀመበትም ጊዜ ለመጠቃታችን አንዱ ምክንያት የጅቡቲ የእጅ አዙር ወገንተኝነት ነበር።

ጅቡቲን ተመራጭ ያደረገው ሌላኛው ምክንያት ግዛቱ በቀጠናው አጠቃላይ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ወታደራዊ አሰላለፍ አንፃር የያዘው ቁልፍ ቦታ ነው። በገቢር የአረብ ባህር ለመሆን ችሎ የነበረው የቀይ ባህር ዳርቻ በተጋሯ የአረብ መንግስታት ተፅዕኖ ሥር መዋሉ እና አገራቱ ይህንን እሳቤ ከግብ ለማድረስ በብርቱ መንቀሳቀሳቸው በኢትዮጵያ ጥቅሞች ላይ ችግር ማስከተሉ አልቀረም። ስለሆነም በ1940ቹ አጋማሽ እውን የሆነውን የኤርትራን መመለስ ተከትሎ አገሪቱ ሉዓላዊ የባህር በሮች ባለቤት መሆን ችላ የነበረ ቢሆንም የምፅዋና የአሰብ ወደቦች ይሰጡ የነበረው አገልግሎት የጅቡቲን ሚና ሊተካ አልቻለም።

በተለይ በሰሜን ኢትዮጵያ ለረጅም ጊዜ የተከናወነው የእርስ በርስ ጦርነት የቀይ ባህር ወደቦችን አስተማማኝነት በእጅጉ አኮስምኖታል። ተከታታይ መንግስታትም ከምፅዋና አሰብ ይልቅ ምስራቋዊውን በር የአገሪቱ ህልውና መሠረት አድርገው መውሰዳቸው ከዚህ እውነታ የመነጨ ነው። ከ1983

በኋላ ከነፃይቱ ኤርትራ ጋር ተመሠርቶ የነበረው ጥምረት በአሳዛኝ ፍፃሜ ሲደመደምም ወትሮም አሳማኝ ያልነበረው የአሰብ ወደብ ተጠቃሚነት ተቋርጦ ሙሉ በሙሉ በጅቡቲ ላይ ጥገኛ ወደመሆኑ መመለሱ አማራጭ የሌለው ግዴታ ሆነ። በተጨማሪም በአፍሪካ ቀንድ የሚገኙ መንግስታት በአመዛኙ ሲያራምዱት የቆዩት ፀረ-ኢትዮጵያ አቋም አገሪቱ ተለዋጭ የባህር በር አማራጭ እንዳይኖራት አድርጓል። በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ በተደጋጋሚ እንደተስተዋለው በአንድም መልኩ ይሁን በሌላ ሶማሊያና ኤርትራ የጥቃት ምንጮች ሆነው ቆይተዋል። ሱዳንና ኬንያ ደግሞ ከግንኙነት ታሪኩ እውነታ ባሻገር ካላቸው አንፃራዊ ጂኦግራፊያዊ አቀማመጥ እና በአገራቱ መካከል ካለው እጅግ ኋላቀር የመሠረተ ልማት መዋቅር የተነሳ የኢትዮጵያን ፍላጎት ሊያሟሉ ከሚችሉበት ደረጃ አልነበሩም። ስለዚህም ጅቡቲ ብቸኛው እና አስተማማኙ ከውጭው ዓለም የመገናኛ በር መሆን ቻለ።

ጅቡቲ የሚሰጠውን ሁለንተናዊ ጠቀሜታ በአስተማማኝ ለማስከበር ሲባልም መጀመሪያ ከቅኝ ገገርው ከፈረንሳይ መንግስታት እና ቀጥሎም ከጅቡቲ ፖለቲከኞች ጋር መግባባቱ፣ መደራደሩና ብሎም መሻኮቱ የሁልጊዜም ሥራ ሆነ። ግዛቱን ከሦስተኛ ወገን ጥቃት በተለይም ከሶማሊያ ተስፋፊነት እና ከፓን አረብ እሳቤ መከላከሉ የዘውትር ክትትል ጠየቀ። በተዛማጅ በግዛቱ የተነሳው የብሔረተኝነት ንቅናቄ በተለይም ወደ ሶማሊያ ያዘነበለ ፖለቲካ እና የኢትዮጵያን ጥገኝነት ከግምት በማስገባት በግዛቱ መሪዎች የተወሰዱ ፀረ ኢትዮጵያ እርምጃዎች አጠቃላይ ሂደቱን የተወሳሰበ አደረገ። በዚህ ሁሉ መኻል ግዛቱ ተመራጭ የኢኮኖሚና የደህንነት በር ሆኖ ዘለቀ።

የአገሪቱን ጥቅም የማስጠበቁ ጥረትም በነዚህ ወሳኝ ነጥቦች ዙሪያ የተመሠረተ ነበር። ነገር ግን ጅቡቲን ለዘለቄታው የኢትዮጵያ የጥቅም በር አድርጎ ለማቆየት የተከናወኑ ተከታታይ ጥረቶች እና ውጤቶቻቸው በሂደት እየተመናመኑ መጥተው በአሁኑ ወቅት አገሪቱ ሙሉ በሙሉ በግዛቱ በጎ ፈቃድ ላይ ጥገኛ ከሆነችበት ደረጃ ላይ ደርሳለች። በአንድ ወቅት ስለ





ኢትዮጵያዊነቱ በእርግጠኝነት ይታመንበት የነበረውን ግዛት በተገላቢጦሽ የአገሪቱን ኢኮኖሚያዊ ህልውና በተጸዕኖ ስር ለማዋል አቅም ማግኘት እና በዚህም መጠቀም ቻለ።

ይህ መጽሐፍ ጅቡቲን በተመለከተ የኢትዮጵያ መንግስታት ያደረጓቸውን የዲፕሎማሲ ትግሎች ለመዳሰስ ይሞክራል። ስለ ግዛቱ የነበውን የደገባኛል ጥያቄ እና ባለመብትነት እንደ ማዕከላዊ የትንታኔ ነጥብ በመውሰድ በሂደት የተከናወኑ ጥረቶችን ከነጥንካሬና ድክመቶቻቸው በመረጃ በማስደገፍ ለመተንተንም ተሞክሯል። ይህንን ለማድረግም ተከታታይ መንግስታት ከቅኝ ገዢዋ ከፈረንሳይ ጋር የደረሱባቸውን መግባባቶችና ይህም ያስከተለውን ውጤት፤ የጅቡቲ ግዛትን የውስጥ ፖለቲካ ጅምር እና ዕድገት፤ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ በተለይ የአፋር እና ኢሳ ጎሳዎች በትግሉ ውስጥ የተጫወቱትን ወሳኝ ሚና፤ እንዲሁም ከአፄ ኃይለ ሥላሴ ወዲህ ያሉ መንግስታት የተከተሏቸውን ፖሊሲዎች ጥንካሬና ድክመት ለመዳሰስ ጥረት ተደርጓል። ይህ መጽሐፍ በአመዛኙ የተመሠረተው ከኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በተገኙ መዛግብት ላይ ሲሆን፣ የታሪክ ፍሰቱም በአመዛኙ የማዕከላዊ መንግስታቱን እይታ ያንጸባርቃል። የመጽሐፉ ትንታኔና ድምዳሜ ግን የፀሃፊው የግል ግንዛቤ ውጤቶች ናቸው።

ከኢትዮጵያ ጎረቤቶች መካከል ለአገራችን ከሚሰጡት ሁለንተናዊ ጠቀሜታ አንፃር በቀደምትነት መታወቅ የሚገባው የጅቡቲ ጉዳይ መሆኑን ጸሐፊው ያምናል። በአገሪቱ ዘመናዊ ታሪክ ውስጥ - የግል ወደብ ይኑር አይኑር፣ ከተቀናት የጎረቤት መንግስታት ጋር የነበረው ግንኙነት የትኛውንም ገጽታ ይያዝ፣ የኢትዮጵያ መንግስታት ጥንካሬና ተሰሚነት ደረጃ ይለያይ ወዘተ - በአጠቃላይ ሂደቱ ውስጥ የጅቡቲ ወሳኝ ሚና ተመሳሳይ ሆኖ ዘልቋል። በኢትዮጵያ የቅርብ ጊዜ የዲፕሎማሲ እንቅስቃሴ ውስጥ በተለይ የጎረቤት አገሮችን ሚና ጠንቅቆ ማወቁ አስፈላጊ ነው። ተከታታይ መንግስታት በጅቡቲ ጉዳይ ላይ ስለያዙት አቋም፣ ስለተከተሏቸው ፖሊሲዎች፣ እና የአገሪቱን ጥቅም ለማስከበር ስለወሰዷቸው እርምጃዎች አበክሮ መመርመር ግን ቅድሚያ የሚሰጠው ተግባር መሆን ይገባዋል። ጅቡቲ ከማናቸውም በላይ የኢትዮጵያን ህልውና በእጇ የያዙ እንቅስቃሴዎች መነሻ ስለሆነች------

# ምዕራፍ ፩
# መግቢያ

ስለ ጅቡቲ በተወሳ ቁጥር ዳግማዊ ምንሊክ በኢትዮጵያ የፈረንሳይ ባለ ሙሉ ስልጣን ሚኒስትር ከሙሴ ላጋርድ ጋር በመጋቢት 12፣ 1889 (20 March 1897) የተፈራረሙት የአዲስ አበባው ስምምነት በቀደምትነት ይነሳል::[1] የዚህ ስምምነት ፋይዳ የግዛቱን ለፈረንሳይ ተላልፎ መስጠት ከማረጋገጥ ባሻገር፤ የድንበር ወሰንን እና የግዛት አለኝታ ጥያቄን በተጨባጭ ለማስረገጥ መሞከሩ ነው:: በተጨማሪም ስምምነቱ በተጠቀሰው የግዛት ክልል የማንኛውንም ሦስተኛ ወገን ጣልቃ ገብነት የሚከለክል ሲሆን በክልሉ የሚገኘውን የአሳል ሐይቅ የኢትዮጵያ ቋሚ ውርስ መሆንና የአገሪቱን ያልተገደበ ጨው የማምረት መብት ያረጋግጣል:: ይህ ስምምነት በ1891 እ.ኤ.አ. ምንሊክ ለአውሮፓ አገራት በላኩት ዘዋሪ ደብዳቤ ያስረገጡትን እስከ አሳል ሐይቅ ይደርስ የነበረውን የግዛታቸውን ድንበር አሳልፎ የሰጠ ነው::

የ1889ኙ ውል ኢትዮጵያ በጅቡቲ ላይ ለነበራት የግዛት አለኝታ ጥያቄ እንደ ህጋዊ ማረጋገጫ ተደርጎ ሲወሰድ ቆይቷል:: የአውሮፓ አገራት የስዊዝ ካናልን መከፈት ተከትሉ የአፍሪካ ቀንድን ከመቀራመታቸው እና የኢትዮጵያን ሉአላዊነት አደጋ ላይ ከመጣላቸው በፊት አብዛኛው የቀይ ባህር አከባቢ በኢትዮጵያ ቁጥጥር ስር የነበረ መሆኑን የሚያስረግጠው አፈሴላዊው አቋም የተለያዩ ቀደምት የታሪክ መረጃዎችን በዋቢነት በማንሳት የባለቤትነት መብትን ይጠይቃል::

[1] ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር (ውጉሚ)፤ አቃፊ -ፋይል፡- ጅቡቲ 52-D3፤ የኢትዮጵያና ፈረንሳይ ስምምነት፡ መጋቢት 12፣ 1889





በ5ኛው ክፍለ ዘመን አፄ ካሌብ የናግራን (የመን) ክርስቲያኖችን ለመርዳት ሲዘምቱ ሠራዊታቸው ከጅቡቲ በመነሳት በባብኤል መንደብ መሻገሩ፤ የአውሮፓውያን ተጓዦችን ዘገባ በመመርኮዝ የኢትዮጵያ ወሰን በሰሜን ምሥራቅና በምሥራቅ እስከ ቀይ ባህርና ኤደን ባህረ ሰላጤ እንዲሁም በደቡብ ምሥራቅ እስከ ሕንድ ውቅያኖስ መድረሱ በተደጋጋሚ የሚነሱ መከራከሪያዎች ናቸው:: በተጨማሪም በ16ኛው ክፍለ ዘመንና ከዚያም ወዲህ የኦቶማን ቱርክ መንግሥት የመስፋፋትና የመግዛት ፍላጎቱን ለማርካት ወደ አፍሪካ ቀንድ ከመምጣቱ በፊት ጅቡቲ የኢትዮጵያ ግዛት መሆንዋንና ወራሪው ኃይልም በኢትዮጵያ ወታደሮች በየጊዜው ከዚሁ ሥፍራ የተባረረ መሆኑ፤ እንዲሁም እስከ አፄ ምንሊክ ዘመነ መንግሥት ድረስ የታጁራና ሌሎችም የጅቡቲ ሱልጣኖች ለኢትዮጵያ መገበራቸው በመረጃነት ይቀርባሉ::[2]

በተጨማሪም አስተዳደራዊ መዋቅሮችንና የህዝቦችን አሰፋፈር ይዘት መሠረት በማድረግ የአሁኑ የጅቡቲ ግዛት በኢትዮጵያ ቁጥጥር ስር እንደነበር ይታሰባል::

[2] ውጉሚ፡- ሱማሌ 15-D1:: Also see Francisco Alvares, *The Prester John of the Indies.* Trans. Lord Stanley of Alderley (The Hakluyt Society, second series, nos. 104 and 105), p. 300; Daniel D. Kendie, "Towards Northeast African Cooperation: Resolving the Ethiopia-Somalia Disputes," *in Northeast African Studies,* Vol. 10, No. 2 (2003), 67-70. Merid Wolde-Aregay, "Southern Ethiopia and the Christian Kingdom 1508-1708, with Special Reference to the Galla Migration and Their Consequences," PhD Thesis in History (University of London, School of Oriental and African Studies, January 1971), pp.18-60. *ያዕቆብ ኃይለማርያም፣ አሰብ የማን ናት? የኢትዮጵያ የባህር በር ጥያቄ* (ንግድ ማተሚያ ቤት፡ አዲስ አበባ፣ 2004 ዓ.ም.)፣ ገፅ 27-31.

የግዛቱ ሰሜናዊ ክፍል በትግሬ ራሶች ሲተዳደር የተቀረው ደቡባዊው ክፍል ደግሞ የሸዋ ነገስታት ይዞታ መሆኑ በመንግስታዊው ክርክር እንደመረጃ ሲቀርብ ቆይቷል። የታጁራ ሸለቆ (Gulf of Tadjura) በሚል ስያሜ የሚታወቀው ሰሜናዊ ክፍል አዱሊስ (ዙላ)፣ ቤይሉል፣ አሰብ እና ሮሂያቶ የተሰኙ ቀጠናዎች ሲኖሩት በአብዛኛው ቀድሞ ሩሶ አሁን ደግሞ አፋር/ደንከል ተብለው የሚጠሩ ህዝቦች ሰፍረውበታል። ከአጠቃላይ የአፋር/ደንከል ህዝቦች ውስጥም ሦስት-አራተኛው በቋሚነት የሚኖሩት አዳል እና ሰርዶ በተሰኙ የኢትዮጵያ ክፍሎች ሲሆን እነሱም በአውሳና ራህየቶ ሱልጣኖች ይመራሉ። ይህ የአፋር ህዝቦች የመኖሪያ ቀጠና በተለምዶ "የአፋር ትሪያንግል" በመባል ይታወቃል። ከዘይላ በስተደቡብ እስከ ጋርዳፊያ ያለው ግዛት በበኩሉ የሶማሌ ህዝቦች ይኖሩበታል።

እስከ 1840 ባለው ጊዜ የአሁኑ የጅቡቲ ግዛት ከተወሰኑ የመካከለኛው ምስራቅ አረቦች በስተቀር በአብላጫው በአፋር/ደንከሎች የተያዘ እንደነበር ይታመናል። ነገር ግን ዱልሃንቴና ወሰንግሌ የተሰኙ የዳሮድ ሶማሌ ንዑስ ጎሳዎች ወደ ሰሜን አቅጣጫ ያካሄዱት የግዛት መስፋፋት የጅቡቲን የህዝብ መዋቅር ቀየረው። የሶማሌዎቹን ጫና ተከትሎ የግዛቱ ጎሳዎች ይዞታ ከመቀየሩም ባሻገር የዱልሃንቴና ወሰንግሌዎችን የኃይል እርምጃ መቋቋም ያቃታቸው የኢሳ ሶማሌዎች ወደ ጅቡቲና ኢትዮጵያ ምስራቃዊ ክፍሎች (በዋነኝነት ሐረር) እንዲሸሹ ገፋቸው። ሂደቱም በጅቡቲ የፖለቲካና ኢኮኖሚያዊ ትግል በደንከል/አፋር እና ኢሳ ሶማሌዎች መካከል የቁጥር የበላይነት ሽኩቻን አስከተለ። ከአጠቃላይ የኢሳ ህዝቦች መካከል ሁለት-ሶስተኛው ያክል የሚኖሩት በኢትዮጵያ ውስጥ ሲሆን የጎሳው መሪ (ኡጋዝ) ቋሚ መቀመጫም ድሬዳዋ ሆነ።[3]

[3] ውጉሚ፡- ቀይ ባህር 158-D22 6፤ ኢትዮጵያ በቀይ ባህር የጠረፍ ግዛቶች ላይ ስላላት የግዛት መብት ዙሪያ የቀረበ የጥናት ሪፖርት





የአሁኑ የጅቡቲ የህዝብ አወቃቀርና አሰፋፈር እንደሚያመለክተው የኢሳ ጎሳ አባላት የአጠቃላይ ቁጥሩን 35 ፐርሰንት አካባቢ የሚይዙ ሲሆን አፋር/ደንከሎቹ ደግሞ ወደ 20 ፐርሰንት አካባቢ ይሸፍናሉ። ኢሳዎች የግዛቱን አንድ-ሦስተኛ ክፍል በሚያካልለው ከታጁራ ሸለቆ በስተደቡብ እና ከአዲስ አበባ-ጅቡቲ የባቡር ሐዲድ ምስራቃዊ ክፍል ሰፍረዋል። የአፋር/ደንከል ጎሳዎች ደግሞ ከታጁራ ሸለቆ በስተሰሜንና ከባቡር ሐዲዱ በስተምዕራብ ባለው የጅቡቲ ሁለት-ሦስተኛ ክልል በቋሚነት ይኖራሉ። ከተቀረው የግዛቱ ነዋሪ ህዝቦች መካከል ገደቡርሲና ኢሳቅ የተሰኙት ሶማሌዎች ከሰሜን ሶማሊያ በቅርብ ዘመን እንደመጡ ይታመናል። እንዲሁም ፈረንሳዊያን፣ አረቦችና ጥቂት አውሮፓውያን በግዛቱ ሰፍረው ይገኛሉ።

ከሁለቱ ዋነኛ የግዛቱ ሕዝቦች መካከል ኢሳዎቹ ጠንካራ የሆነ በጎሳ አስተዳደር ላይ የተመሠረተ አደረጃጀት መመስረት ችለዋል። የኢሳ ማህበረሰብ በሦስት ጎሳ የተከፈለ ሲሆን ከነዚህም ሁለቱ እንደገና በንዑስ ጎሳዎች ይከፈላሉ። ከሦስቱ ጎሳዎች መካከል የአብጋል ጎሳ በአፍሪካ ቀንድ ከሚኖሩ ኢሳዎች ሦስት-አራተኛውን እንዲሁም በጅቡቲ ከሚኖሩት ሁለት-ሦስተኛውን ያህል ይሸፍናል።


አብጋሎች በአራት ንዑስ ጎሳ የሚከፈሉ ሲሆን እነሱም ዩኒስ-ሙሳ፣ ሳድ-ሙሳ፣ ማማሳን እና አርዌን ይሰኛሉ። ሁለተኛው ጎሳ - ዳሎል - የግዛቱን ኢሳዎችን አንድ-ሦስተኛ ሲሸፍን በተራው ፎርላባ፣ ሆሮኔ እና ዋላዶን በሚባሉ ሦስት ንዑስ ጎሳዎች ይከፋፈላል። ዋርዲክ የተባለው ሦስተኛው የኢሳ ጎሳ በአመዛኙ በሶማሌና አፋሮች የጋብቻ መተሳሰር የተፈጠረ እንደሆነ ይታመናል። አብጋሎች በተለይም የማማሳን ንዑስ ጎሳ ከቁጥር ብልጫቸው በመነሳት ግዛቱን የማስተዳደር ተፈጥሮአዊ መብት እንዳላቸው የሚያምኑ ሲሆን ዳሎሎች ደግሞ ዋነኛ የስልጣን ተቀናቃኝ ሆነው ኖረዋል። ዋርዲኮች በተራቸው የኢሳዎች መንፈሳዊ መሪ - ኡጋዝ - ከነሱ ጎሳ የሚመረጥ መሆኑን ለፍላጎቶቻቸው ማራመጃነት ይጠቀሙበታል።

[4] Peter J. Schraeder, "Ethnic Politics in Djibouti: From "Eye of the Hurricane' to 'Boiling Cauldron'", in *African Affairs*, Vol. 92, No. 367 (April 1993), pp. 204-206.

አፋሮችም በተመሳሳይ ለጎሳ ድርጅትና አባልነት ቅድሚያ የሚሰጡ ቢሆንም ከኢሳዎች በተለየ ግን ከባህላዊ የጎሳ መሪዎቻቸው - ሱልጣኖች - በተዋረድ በሚተላለፉ መመሪያዎች ላይ ይመረኮዛሉ። ከኢሳዎች በተቃራኒ የጎሳውን ሁለንተናዊ ሰብዕና በሚነኩ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ የሚያስተላልፉት ሱልጣኖቹ ናቸው። ለዚህም ዓላማ የሚቋቋም በንዑስ ጎሳ መሪዎችና ሌሎች ባላባቶች የተዋቀረ የአማካሪዎች ምክር ቤት ለሱልጣኖቹ የማማከር ድጋፍ ያደርጋል። ሌላው የአፋር/ደንከል ልዩ ባህሪይ ጎሳው በሁለት ማህበራዊ ክፍሎች መከፈሉ ነው። በዘልማድ በከፍተኛ ቦታዎች የሚኖሩ አፋሮች አሳሂመራ (ቀይ) ጎሳዎች ሲባሉ በዝቅተኛ አከባቢዎች የሚገኙት ደግሞ አዶሂመራ (ነጭ) ጎሳዎች ተብለው ይታወቃሉ።








Probable extent of the Ethiopian empire at the beginning of the sixteenth century.

በ16ኛው ክፍለዘመን መጀመሪያ የኢትዮጵያ ግምታዊ የግዛት ክልል[5]

5 Meried, p. 22




በ16ኛው ክፍለዘመን መጀመሪያ የኢትዮጵያ የደቡብ ምሥራቅ የግዛት ክልል[6]

በኢትዮጵያ መንግስት የተጠናቀሩ የጥናት ወረቀቶች ጅቡቲ ለፈረንሳይ ተላልፎ የተሰጠበትን አግባብ ከአጠቃላይ የ19ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ ዕውነታዎች አንፃር ለመተንተን ሙከራ ያደርጋሉ። እንግሊዝ፣ ጣሊያን እና ፈረንሳይ ያሳዩት የአፍሪካ ቀንድን በተለይም ኢትዮጵያን የመቀራመት ፍላጎት፤ የአገሪቷ የመከላከያ መዋቅር በሰሜን ከጣሊያን፣ በምዕራብ ከማህዲስቶች ለረጅም ጊዜ መፋጠጡ፤ ትልቁ ቅኝ የመገዛት አደጋ አድዋ ላይ በትልቅ መስዋዕትነት መቀልበሱ እና ይህ

[6] Merid, p. 43





ያስከተለው የወታደራዊ አቋም መከስመን ወዘተ የጠረፍ ክልሎችን በአስተማማኝ ለመከላከል አላስቻለም።
ስለሆነም እንግሊዝ ሶማሊላንድን፣ ፈረንሳይ ጅቡቲን እና ጣሊያን ቤናድር ሱማሌን በወረራና ባላባቶቹን በገንዘብ በመደለል መያዝ ቻሉ። እያፈጠጠ የመጣውን ሉአላዊነትን ለዘለቄታው የማጣት ዕውነታ በጊዜያዊነት ለመቅረፍ ብቸኛው አማራጭ ከነዚህ ተስፋፊ መንግስታት ጋር ዓለም አቀፍ ይዘት ያላቸው ስምምነቶችን መፈራረም እና በዚህም አማካይነት ለሀገሪቱ ህልውና ዋስትና ማበጀት ነበር።

በጅቡቲ የይገባኛል ጥያቄ ዙሪያ ኢትዮጵያ ስታራምደው የነበረውን ፖለቲካዊ አቋም መልክ ለማስያዝ የተቀናጀ ሙከራም መደረጉ አልቀረም። ለምሳሌ በሐምሌ 1957 የኢትዮጵያን ታሪካዊ የባለቤትነት መብት እንዲያጠና ለአንድ የታሪክ ባለሙያዎች ቡድን ኃላፊነት ተሰጥቶ ነበር። በጥናቱ ማጠቃለያ በቀረበው ሪፖርት እንደተብራራው በአውሮፓ የታተሙ ወደ 14 የሚጠጉ ጥንታዊ ካርታዎች በግልፅ እንደሚያመለክቱት ከ1500 እስከ 1850 ባሉት ጊዜያት ከዘይላ እስከ ሱዳን ወደብ (ፖርት ሱዳን) ያለው የቀይ ባህር ዳርቻ የኢትዮጵያ ሉአላዊ ግዛት አካል ነበር። በተጨማሪም የ1899ኙን አጠቃላይ ውል እና የድንበር ስምምነት በዋቢነት በማቅረብም ፈረንሳይ ግዛቱን ከኢትዮጵያ በስተቀር ለሌላ ሦስተኛ ወገን ላለማስተላለፍ የገባችውን የውዴታ ግዴታ እና ኢትዮጵያ በአሳል ሐይቅ ላይ ያስከበረችውን የባለርስትነት መብት ያስረግጣል።[7]

[7] ውጉሚ፡- ጅቡቲ ልዩ ልዩ ጉዳዮች 1፤ ኢትዮጵያ በቀይ ባህር ጠረፎች ላይ ስላላት መብት የቀረበ የጥናት ሪፖርት (በፐ. ፔትሪዲስ እና ጓደኞቻቸው ተከለማሪያም)፡ ጥቅምት 1961። ውጉሚ፡- ጅቡቲ 52-D3 26፤ የጥናት ሪፖርት፡ ኢ.ኤ.አ. የካቲት 26፤ 1966

[8] ውጉሚ፡- ጅቡቲ ልዩ ልዩ ጉዳዮች 1 ጥራዝ 2፤ በኢጣሊያን ወረራ ወቅት ንጉሰ ነገሥቱ በታውን ሸጠውት የነበረ ሲሆን ከነፃነት በኋላ መልሰው ገዝተውታል። ጅቡቲ ነፃነቷን ስትቀዳጅ በታውን የወረሰችው ቢሆንም በ1967 ደርግ ወደ ኢትዮጵያ ይዞታነት እንዲመለስ አድርጓል።

በአስገዳጅ ምክንያቶች የፈረንሳይ ቅኝ በሆነው ግዛት የኢትዮጵያን ልዩ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የተለያዩ ጥረቶች ሲደረጉ ቆይተዋል። በባቡር ሐዲዱ እና በወደቡ ላይ በተለይዩ ጊዜያት ከተገኙ የልዩ ተጠቃሚነት መብቶች በተጨማሪ በንጉሰ ዘመን ከፈረንሳይ መንግሥት በስጦታ የተገኘው 15,888 ካሬ ሜትር ቦታ እና ቪላ (በጅቡቲ ከተማ Plateau du Serpent በሚባለው ውድ ሠፈር ውስጥ የሚገኘው) ለቆንስላ ጽ/ቤት ከተፈቀደው ሁለት ተጨማሪ ቦታ ጋር የአገሪቱን የተለየ መብት ባለቤትነት ያረጋግጠለ።[8]

አፋምቦን ወደ ኢትዮጵያ ለማስመለስ የተደረጉ ስኬታማ እንቅስቃሴዎች እና በአሳል ሐይቅ የመጠቀም ቅ አካያ የጅቡቲ በር መብትን በዘላቂነት ማስከበሩ ይህንኑ ስለ ጅቡቲ የተደረገውን ትግል ስፋትና ጥልቀት ያመላክታል። ከሁሉም በላይ ኢትዮጵያ በ1897 እ.ኤ.አ. በአፍሪካ ምድር ለመጀመሪያ ጊዜ የከፈተችው የቆንስላ ጽ/ቤት የሚገኘው በጅቡቲ መሆኑ ለግዛቱ የተሰጠው ልዩ ትኩረት ዋነኛው አመላካች ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል።

ቀደምት የኢትዮጵያ መንግስታት ፈረንሳይ በሂደት ቅኝ ግዛቷን ስትለቅ እና የጅቡቲ ህዝብ የራሱን ዕድል የመወሰን መብቱን ሲተገብር ያለፈ ታሪኩን ከግንዛቤ በማስገባት ወደ እናት ሀገሩ በፈቃዱ ይመለሳል የሚል ፅኑ እምነት ነበራቸው። ይህም ኢኮኖሚያዊ፣ ስትራቴጂካዊ/ጂኦግራፊያዊ እና ማህበራዊ እሳቤዎችን ከግምት በማስገባት ነው። ጠቅላላ ስፋቱ 23,000 ስኩዌር ኪሎ ሜትር የሆነው እና እስከ 1980ቹ መጨረሻ ከ300,000 ያነሰ ህዝብ የሚኖርበት ጅቡቲ ሙሉ በሙሉ በኢትዮጵያ ምርትና አገልግሎት ላይ ጥገኛ መሆኑ፤ አጠቃላይ የወሰን ክልሉ ርዝመት 500 ኪሎ ሜትር ሆኖ ከዚሁ 400 ኪሎ ሜትሩ የሚዋሰነው ከኢትዮጵያ ጋር መሆኑ፤ የኢትዮጵያን ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ደህንነት ለማስጠበቅ ያለው ስትራቴጂካዊ ጠቀሜታ፤ የጅቡቲ ሁለት ዋነኛ ጎሳዎች - አፋርና ኢሳ - ተሪጥሮአዊ መገኛ እና መቀመጫ በኢትዮጵያ ውስጥ መሆኑ ወዘተ ለዚህ እምነት እንደ ማረጋገጫ ሲቀርቡ ቆይተዋል።





ከሁሉም በላይ ጅቡቲን ተፈላጊ ያደረገው ግን የግዛቱ መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ ለኢትዮጵያ የሚሰጠው ኢኮኖሚያዊና ስትራቴጅካዊ ጠቀሜታ ነው። የሃገሪቱ ዋነኛ ወደቦች የነበሩት አሰብና ምፅዋ በሰሜን በግብፃዊው የስዊዝ ካናል በደቡብ በጠባቡ ባብ ኤል ማንደብና በፔሪም (ማዩን) ደሴት ታንቀው የዓረብ ሐይቅ ተብሎ ሊጠራ በተቃረበው ቀይ ባሕር ውስጥ መገኘታቸው የጅቡቲን ወደብ አጠቃላይ አስፈላጊነት ያጎላዋል። ይህ ስትራቴጂካዊ ከበባ ከብሔራዊ ወደቦቹ ይልቅ ወደ ህንድ ውቅያኖስ በቀላሉ ለመድረስ ጅቡቲን የተሻለ አማራጭ ያደርጋል።

የኢትዮጵያን ወጪና ገቢ ትራንዚት ከማስተናገድ ረገድ እ.ኤ.አ. ከ1962 ጀምሮ ጅቡቲን መወዳደር የጀመረው የአሰብ ወደብ በሃያ ስድስት ሚሊዮን ብር ተሻሽሎ እና የነዳጅ ማጣሪያ ተተክሎለትም እንኳ የጅቡቲ ወደብ ድርሻ 49 ከመቶ፣ የአሰብ 27 ከመቶ እና የምፅዋ 18 ከመቶ ነበር። በ1970ቹ አጋማሽ በኋላ ደግሞ የጅቡቲ ወደብ ወደ 75 በመቶ የሚሆነውን የኢትዮጵያን ትራንዚት ማስተናገድ ችሎ ነበር። ከዚህ አንፃር የጅቡቲ ወደብ ሁለንተናዊ ጠቀሜታ ያለው ከመሆኑም ባሻገር የኢትዮጵያ ዋነኛ የጥቅም በር ሆኖ ቆይቷል፤ አሁንም ነው።[9]

ከዓለም አቀፋዊ እና አከባቢያዊ ጠቀሜታው አንፃርም ሲታይ ጅቡቲ የአውሮፓን የአፍሪካንና የእስያን አህጉሮች የሚያገናኝ፣ በቀይ ባህር፣ በኤደን ባህረ ሰላጤና በህንድ ውቅያኖስ መዳረሻ ስትራቴጂካዊ አቀማመጥ የያዘ በመሆኑ የዓለም የንግድ መተላለፊያ በር ነው። በተለይም የምዕራብ አገሮች ከሚጠቀሙበት ነዳጅ 70 ከመቶው ያህል የሚተላለፈው በቀይ ባህር ላይ በመሆኑ ይህ ዕውነታ የጅቡቲን ስትራቴጂካዊ ቁልፍነት ያጎላዋል።

---

[9] ውጉሚ፡- ጅቡቲ 49-D3 11፤ በጅቡቲ ጉዳይ የቀረበ የጥናት ሪፖርት፡ ታህሳሥ 27፣ 1967። ውጉሚ፡- ጅቡቲ 51-D3 2፤ በጅቡቲ ጉዳይ የቀረበ የጥናት ሪፖርት፡ ሰኔ 28፣ 1968። Seyoum Haregot, *The Bureaucratic Empire: Serving Emperor Haile Selassie* (Red Sea Press: Trenton, New Jersey, 2013), 168.

በዘመናዊ መልክ የተደራጀው የጅቡቲ ወደብም ከሚሰጠው የወደብ አገልግሎት በተጨማሪ ግዛቱ በአውሮፓ፣ ምሥራቅ አፍሪካ፣ መካከለኛው ምሥራቅ እና በህንድ መካከል ትራንስርት መረብ ለመዘርጋት የተመቸ ነው።[10] የግዛቱ መልክዓ ምድራዊ ሁኔታ ሲታይም በዝቅተኛ መሬት ላይ መገኘቱ፣ የታላቁ ስምጥ ሸለቆ አፍ መሆኑ እና በተራራ ያልተጋረደ መሆኑ ወደ መሐል ኢትዮጵያ ለመግባት ተመራጭ ያደርገዋል። ይህም በፀጥታ ረገድ ለኢትዮጵያ ህልውና ቁልፍ የሆነ አቀማመጥ እንዲይዝ ያስችለዋል። በተጨማሪም ግዛቱ በወደቡና በሐዲዱ አማካኝነት የኢትዮጵያ የንግድ መተላለፊያ በር በመሆኑ ተቀናቃኝ የሆነ መንግስት ጅቡቲን ቢይዝ በኢትዮጵያ ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ ለማሳደር ይችላል።

ተከታታይ የፖሊሲ አቅጣጫዎችሲነደፉና ሲተገበሩም ከነዚህ መሠረታዊ ዕወነታዎች በመነሳት ነበር። ሆኖም በዓለም የፖለቲካ ምህዳር እና በተለይም በአፍሪካ ቀንድ በተከሰቱ ተከታታይ ለውጦች ምክንያት በኢትዮጵያ በኩል ከወቅቱ ተጨባጭ ዕውነታዎች የተዛመዱ የፖሊሲ ማስተካከያዎች ሲደረጉ ቢቆዩም የቆየውን የግዛት አለኝታ ብሎም የልዩ ተጠቃሚነት መብት በዘላቂነት ማስጠበቅ አልተቻለም። ይልቁንም ትግሉ በሂደት ጅቡቲን በታላቋ ሶማሊያ ከመታቀፍ ወደመከላከሉ ምዕራፍ ተሸጋገረ። ብሎም የግዛቱን ህልውና ከኢትዮጵያ ዘላቂ ጥቅሞች አንፃር መቃኘት እና ማስጠበቅ አዲሱ የግንኙነት መርህ እየሆነ መጣ።

በተለይ የአፄ ኃይለ ሥላሴ እና የደርግ መንግስታት በእነኝህ መርሆዎች አተገባበር ዙርያ ወሳኝ የሆነ ሚና ለመጫወት ችለዋል። የዚህ ዋነኛ ነፀብራቅ ከሆኑት ጥረቶች

[10] T.N. Dupuy, *The Almanac of World Military Power* (Dunn Loring, Virginia, 1970), 199. Thomas A. Marks, "Djibouti: France's Strategic Toehold in Africa." In *African Affairs*, Vol. 73, No. 290 (Jan. 1974): 95. Peter Schwab, "Cold War on the Horn of Africa." In *African Affairs*, Vol. 77, No. 306 (Jan. 1978): 6.





መካከል ከቅኝ ገዥው የፈረንሳይ መንግስታት ጋር በየወቅቱ የተደረጉ የሁለትዮሽ ስምምነቶች፤ በጅቡቲ የውስጥ ፖለቲካ አወቃቀር ዙሪያ የተከናወኑ ቀጣይነት ያላቸው ጣልቃ ገብነቶች፤ የታላቋ ሶማሊያን የተስፋፊነት ዓላማ ለማክሸፍ የተደረጉ እልህ አስጨራሽ ትግሎች፤ የወደብ እና የባቡር መስመሩን በበላይነት ለመቆጣጠርና የኢትዮጵያ ሉዓላዊ የጥቅም በሮች መሆናቸውን ለማስረገጥ የተሠሩ ሥራዎች ይገኙባቸዋል።

ይህ መፅሐፍ ከ1940ቹ መጨረሻ አንስቶ ኢትዮጵያ በጅቡቲ ዙሪያ ስታራምድ የቆየቻቸውን ፖሊሲዎች ለመዳሰስ እና ለመተንተን ጥረት ያደርጋል። በዘመናዊው የሀገራችን ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ የዚህ ግዛት ሚና በእጅጉ ወሳኝ የነበረ መሆኑ ቢታወቅም ይህንን በተመለከተ የተደረገ ሁሉን ዓቀፍ የታሪክ ጥናት አይገኝም። ጅምር ጥረት ቢኖር እንኳ ስለ ባቡር ሐዲዱ አመሠራረት እና ስላስገኘው ኢኮኖሚያዊ ጥቅም በደምሳሳው ከመዘገብ የዘለለ አይደለም። በፈረንሳይኛ የተፃፉ መፅሐፍትና የምርምር ወረቀቶች በብዛት ቢኖሩም ለአብዛኛው ኢትዮጵያዊ ካላቸው ተደራሽነት አንፃር ፋይዳቸው እምብዛም ነው። ይህንን ክፍተት ከመሙላት አኳያ የዚህ ጥናት ዳራ ኢትዮጵያ በግዛቱ ላይ የተከተለቻቸውን ፖሊሲዎች እና ይህንኑ ለማስፈፀም የወሰደቻቸውን እርምጃዎች በተጨባጭ መረጃ በማስደገፍ መተንተን ነው።

እስከ 1983 ድረስ የምዕዋና አሰብ ወደቦች ባለቤት የነበረች ሀገር በጅቡቲ ጉዳይ የነበራት የማይናወጽ የባለቤትነት ስሜት ከምን የመነጨ ነበር፤ የባህር በር አልባ ከተሆነስ በኋላ የተከሰቱ ዕውነታዎች ተጨባጭ ገፅታ እንዴት ይመዘናል፤ በኢትዮጵያ እና በጅቡቲ መካከል የወደብና ባቡር መስመር አጠቃቀምን አስመልክቶ የተስተዋሉ ለውጦች መሠረታዊ መገለጫዎች ምንድን ናቸው፤ ተከታታይ የኢትዮጵያ መንግሥታት ሁለንተናዊ ጥቅምን ከማረጋገጥ አኳያ በጅቡቲ የውስጥ ጉዳይ ያደረጓቸው ጣልቃ ገብነቶች እስከ ምን ይደርሳሉ፤ በሁሉም አቅጣጫዎች የተገኙ ውጤቶች በሂደት ከታጡ ጥቅሞች ጋር ሲወዳደሩ አገሪቱ በጅቡቲ ላይ የተከተለቻቸው የፖሊሲ አቅጣጫዎች እንዴት ይገመገማሉ ወዘተ የዚህ መፅሐፍ መሠረታዊ ጥያቄዎች ናቸው። ኢትዮጵያ በታሪክ ሂደት በጅቡቲ ላይ የነበራትን የጥቅም

የበላይነት እያጣች መምጣቷ እና በተቃራኒው በግዛቱ ላይ ያላት ጥገኝነት እየጨመረ የመሄዱ አሳዛኝ እውነታ የአንባቢን ትኩረት እንደሚስብ ተስፋ አደርጋለሁ።








# ምዕራፍ ፪


# ጅቡቲን የማጣት መጀመሪያ

## 2.1. የፈረንሳይ ሶማሌ ግዛት ጅምር

በ1861 የስዊዝ ቦይ መከፈት አውሮፓውያን በቀይ ባህር ዳርቻዎች ቁልፍ የመተላለፊያ ግዛት እንዲይዙ መንገድ ጠረገ። እንግሊዝ በሜድትራኒያን እና ቀይ ባህሮች አከባቢ የመሠረተቻቸው ቅኝ ግዛቶች እና ይህንንም ተከትሎ ያረጋገጠችው የኢኮኖሚ/ፖለቲካ የጥቅም የበላይነት ለተቀናቃኟ ለፈረንሳይ የሚዋጥ አልነበረም። ስለሆነም በአዲሱ የዓለም የንግድ እንቅስቃሴ መሥመር አከባቢ ጥቅሟን ለማስከበር የሚያግዛት ተወዳዳሪ የቅኝ ግዛት መያዙ የግድ ሆነ። በአማራጭነትም ገገር የሆነው የባብ ኤል መንደብ ሰርጥ በፈረንሳይ መንግስት እይታ ውስጥ ገባ። ስፍራው ወደስዊዝ ካናል መዳረሻ ከመሆኑም ባሻገር በአውሮፓና በኢንዶቻይና መካከል ለሚመላለሱ የፈረንሳይ ንግድ መርከቦች የከሰል ድንጋይ ማቅረቢያ እንደሚሆን ታመነ።[11] ይህንንም የቅኝ ግዛት ፍላጎት ተግባራዊ ለማድረግ ፈረንሳይ የተለያየ ስልት ተጠቅማለች። እነዚህም ከኢትዮጵያ መሪዎች ስምምነት አግኝቻለሁ ከሚል ማጭበርበር እስከ የግዛት ባለቤትነት ጥያቄዋን ኢትዮጵያ እንድታውቅ እስከማስገደድ ይደርሳል።

ፈረንሳይ በቀይ ባህር ወደብ ለማግኘት ይፋዊ ሙከራ የጀመረችው እ.ኤ.አ. ከ1840 ጀምሮ ነበር። በዚሁ ዓመት መጀመሪያ ላይ ሶሳዩቱ ማንቶ በርዴሌዝ የተባለ ኩባንያ ሙሴ

[11] Virginia Thompson and Richard Adloff, *Djibouti and the Horn of Africa* (Stanford, 1968), 3-22. Kassim Shehim and James Searing, "Djibouti and the Question of Afar Nationalism." In African Affairs, Vol. 79, No. 315 (April 1980): 210-211.


ERITREA
YEM
Ash Shaykh Sa'id
Rehayto
Debaysima
Red Sea
Mayyūn
Moussa Ali
Sidiha Monghella
Fagal
Ālito
GREAT
Manda
Khor Angar
Dadda'to
RIFT
Dorra
VALLEY
Lofefle
Balho
Serdo
Obock
Deda'ī
ETHIOPIA
DENAKIL
Tadjoura
Gulf of Aden
Golfe de Tadjoura
Djibouti
DJIBOUTI
Yoboki
Āfambo
Loyada
Tokhoshi
Holhol
'Ali Sabīh
Dikhil
SOMALIA
HARERGE

ለኮምብ የተባለ ወኪሉ ወደ ቀይ ባህር በማቅናት "በኢትዮጵያ የባህር ድንበር በአስረኛውና በ16ኛው ማዕረግ መካከል" አንድ የንግድ ቦታ እንዲይዝ ትዕዛዝ ሰጠ። የፈረንሳይ መንግስትም ኩባንያው የሚይዘውን ቦታ መልሶ ሊገዛ፣ወጪውንም ሊተካ እና ለኩባንያው አንድ ለመጋዘን የሚሆን ቦታ ሊሰጥ መግባባት እንደነበር መረጃዎች ያመለክታሉ። ሙሴ ለኮምብ ከስፍራው ደርሶ ኤድ አኮዋያ የሚባል አከባቢ ላይ ከግለሰቦች በዘጠኝ ሺህ ዘጠኝ መቶ ፍራንክ (ወደ አንድ ሺህ ስምንት መቶ ብር) አርባ ሁለት ሊግ ካሬ (እርግጠኛ ያልሆነን ርቀት ለመለካት ያገለግል የነበረ፡ አንድ ሊግ 5 ኪሎ ሜትር ወይም 3 ማይል) ከሰሜን ወደ ደቡብ አሥራ አራት ሊግ ከወደቡ ወደ ውስጥ ሦስት ሊግ ጥልቀት ያለው ቦታ ገዛ።[12]

ይሁን እንጂ ምጽዋ የነበረው የፈረንሳይ ቆንሲል ግገርውን ውድቅ በማድረጉ መንግስት የለኮምብን መሬት ሳይገዛው ቀረ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ግን ቆንሲሉ ራሱ (ሙሴ ዱጉቲን) ቦታውን ከኩባንያው በሃያ አምስት ሺህ ፍራንክ ገዝቶ ለሌላ የፈረንሳይ ድርጅት በሃምሳ ሺህ ፍራንክ እ.ኤ.አ. በ1858 መልሶ ሸጠው። በዚህ መንገድም በጅቡቲ የፈረንሳይ ቅኝ ግዛት ተጠነሰሰ።

በተጨማሪም እ.ኤ.አ. በሰኔ 1843 የፈረንሳዩ ንጉሥ ሉዊ ፊሊፕ ወኪል ነኝ በሚል ሮሽ ደሪኩር (Rocket d'Hericourt) የተባለ ግለሰብ ከሸዋው ንጉሥ ሳህለ ሥላሴ ጋር የንግድና የወዳጅነት ስምምነት ይፈራረማል። በስምምነቱ አንቀጽ 6 መሠረት የሸዋው ንጉሥ የፈረንሳይ ዜጎች በግዛቱ ውስጥ ርስት እንዲገዙ የፈቀደ ሲሆን የፈረንሳይ ንጉሥ በበኩሉ ወደ ኢየሩሳሌም ለሚሄዱ ኢትዮጵያውያን ምዕመናን ጥበቃ ሊያደርግ ይስማማሉ።
የሚገርመው ነገር ይህን ስምምነት ሲፈራረሙ ፈረንሳይ

[12] ውጉሚ፡- ጅቡቲ፡ ልዩ ልዩ ጉዳዮች 1፤ ኢትዮጵያ በቀይ ባህር ጠረፎች ላይ ስላላት መብት የቀረበ የጥናት ሪፖርት (በፐ. ፔትሪዲስ እና ጓደኞቻቸው ተክለማሪያም)፡ ጥቅምት 1961። ውጉሚ፡- ጅቡቲ፡ 52-D3 26፤ የጥናት ሪፖርት፡ እ.ኤ.አ. የካቲት 26፣ 1966፣ ገጽ 20





በኢየሩሳሌም ምንም ዓይነት ሥልጣን ያልነበራት መሆኑ ነው። የስምምነቱ ዋነኛ ዓላማ በሸዋ መንግስት ቁጥጥር ሥር የነበሩ የጅቡቲ የጠረፍ ግዛቶችን ወደ ፈረንሳይ ለማዛወር ሕጋዊ መሠረት መፍጠር ነበር።

ከሸዋው ንጉሥ የተፈራረመውን ውል ለግዛቱ ባላባቶች በማሳየትም እ.ኤ.አ. ከ1945-1959 ባሉ ዓመታት ኮምብ (Combes)፣ ብሮኛ (Broguant)ና ላምበር (Lambert) የተባሉ የፈረንሳይ ዜጎች ኦቦክ እና ኢድ ላይ ቦታ ገዝተው ለፈረንሳይ መንግስት ይሸጣሉ። እነዚህ ግለሰቦች ከ1882-1884 ባሉ ዓመታት ከጅቡቲ ባላባቶች ቁራሽ መሬት ብቻ ሳይሆን የይዞታ ባለመብትነትንም ጭምር የሚያረጋግጥ ስምምነት ተፈራረሙ።

እ.ኤ.አ. በመጋቢት 1862 በአዳል የባህር ጠረፍ የሚገኙ ባላባቶች በኦቦክ የሚገኘውን የመርከብ ማረፊያና ከራስ አሊ እስከ ራስ ዱሜራ ያለውን ሜዳ በአስር ሺህ ብር፤ እ.ኤ.አ. በታህሳሥ 1884 ከራስ አሊ ጀምሮ እስከ ጉበት ካራብ ድረስ ላለው አገር ባላባት የሆነው አሕመድ ቤን ሞሐመድ በወር 180 ብር ለመጦሪያ እየተቀበለ በስሩ ያለውን አገር የፈረንሳይ ጥገኛ እንዲሆን ከፈረንሳዮች ጋር ስምምነት አደረጉ። በተከታታይም የጉባድ ባላባት አህመድ ሎይታ እና ከጉባት ካራብ እስከ እምባደ ዜይላ ያሉ የኢሳ ባላባቶች የፈረንሳይ ጥገኛ ለመሆን ፈቃደኛ ሆኑ። የፈረንሳይ መንግስትም በግል የተገዙትን ቦታዎች በአገዛዙ ሥር እንዲመዘገቡ ማድረግ ይጀምራል።[13]

ነገር ግን ከግዛቱ ባላባቶች ጋር በተናጠል የተደረጉ የግዢ ውሎች ህጋዊነታቸው የተሟላ እንዳልሆነ የተረዱት ፈረንሳዮች ከኢትዮጵያ መሪዎች ዘላቂ የባለቤትነት ማረጋገጫ ለማግኘት

[13] ዝኒ ከማሁ። ውጉሚ፡- ቀይ ባህር 158-D22 6፤ ኢትዮጵያ በቀይ ባህር የጠረፍ ግዛቶች ላይ ስላላት የግዛት መብት ዙሪያ የቀረበ የጥናት ሪፖርት
[14] ባህሩ ዘውዴ፣ *የኢትዮጵያ ታሪክ ከ1847 እስከ 1983* (አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ፣ 1999ዓ.ም.)፣ ገፅ 23-26፣ 42-44፣ 53-64፣ 80-88.

ተንቀሳቀሱ። በእርግጥም እ.ኤ.አ. እስከ ጥቅምት 1883 ድረስ በኦቦክ የባህር ዳርቻ ተገድቦ የነበረው ይዞታ በዓመት ከ62,000 የፈረንሳይ ፍራንክ የማይበልጥ በጀት ያለውና ሁለት ፈረንሳዊ ነጋዴዎች ብቻ የሚኖሩበት ነበር። ከኢትዮጵያ የተፈለገውን ማረጋገጫ ለማግኘትም ፈረንሳዮቹ ብዙ አልተቸገሩም። አጠቃላይ ሂደቱም በቀጣዮቹ ሁለት ዓመታት ውስጥ ተጠናቀቀ።

እ.ኤ.አ. ከ1845-1885 በነበሩ ወቅቶች ኢትዮጵያ ምስራቃዊ ጠረፏን ብቻ ሳይሆን አጠቃላይ የቀይ ባህር ይዞታዎቿን ከአውሮፓውያን ቅኝ ለመከላከል የምትችልበት አቅም አልነበራትም። ጊዜው አገሪቱ ከ1740 እስከ 1840 ከቆየው የዘመነ መሳፍንት የእርስ በርስ መቆራቆስ እየተላቀቀች የነበረበት፤ ነገር ግን ወዲያወኑ እስከ ምዕተ-ዓመቱ መገባደጃ ወደዘለቀ የፖለቲካ ሽኩቻ የተሸጋገረችበት ነበር። በአፄ ቴዎድሮስ፣ ዮሃንስ እና ምንሊክ ዘመናት የተደረጉ የሥልጣን ይገባኛል ትግሎች ለዚህ ዋነኛ አመላካች ተደርገው ሊወሰዱ ይችላሉ። በተጓዳኝ ደግሞ እጅግ የጠነከረ ወታደራዊ አቅም የነበራቸው ተስፋፊ ኃይሎች የአገሪቱን ነፃነትና ሉዓላዊነት የፈተነ ተደጋጋሚ ወረራ እያደረጉ ነበር።[15]

እንግሊዞች በ1860/61 እስከ መቅደላ አምባ መድረስ ቻሉ፤ በ1860ቹ መጨረሻ ግብፃውያን ተከታታይ ወረራ ፈፀሙ፤ በ1880/81 ደርቡሾች/መሐዲስቶች እስከ ጎንደር ዘለቁ፤ ጣሊያኖች በበኩላቸው አድዋ ላይ እስከተሸነፉበት ድረስ የአገሪቱን ህልውና በእጅጉ የፈተነ የቅኝ መግዛት ጥረት አደረጉ። ምንም እንኳን ወረራዎቹ በከባድ መስዋዕትነት ሊከሽፉ ቢችሉም የተገኙት ድሎች ስትራቴጂካዊ ፋይዳቸው ትልቅ የሆኑ የዳር አገር ግዛቶችን በአውሮፓውያን ከመያዝ አላዳኑም። ፈረንሳይ ከኢትዮጵያ ጅቡቲን በቅኝ የመያዝ ማረጋገጫ ስትሻ የአፄ ምንሊክ መንግስት ይህንን ለመቃወም ብሎም እንዳይሆን ለመከላከል የሚያስችል አቅም አልነበረውም።

[15] ውጉሚ፡- ቀይ ባህር 158-D22 6፤ ኢትዮጵያ በቀይ ባህር የጠረፍ ግዛቶች ላይ ስላላት የግዛት መብት ዙሪያ የቀረበ የጥናት ሪፖርት





በኢትዮጵያ በኩል የነበረው አቅም አልባነት አፄ ምንሊክ ለፈረንሳዩ ፕሬዚደንት ሳድ ካርኖ እ.እ.አ. ጥቅምት 30፣ 1890 በላኩት የተማጽኖ መልዕክት ተንጸባርቋል። ፈረንሳይ እንደ መያገር ስትጠቀምበት ስለነበረው በጅቡቲ በኩል ወደ ኢትዮጵያ እንዲገባ ስለፈቀደችው የጦር መሳሪያ ምስጋናቸውን ከገለፁ በኋላ፡-

> …አሁን የጠረፉን ግዛት ከያዛችሁና ጎረቤታችን መሆናችሁን ካረጋገጣችሁ ዘንድ ሁሉንም የባህር ጠረፍ እንዳትይዙ ይልቁንም የተወሰነ መተላለፊያ ነጥብ እንድትተዉልን እንጠይቃችኋለን። ይህንንም መተላለፊያ ቀጠና ማስተዳደር እስክንችል ወደ ሦስተኛ ወገን ይዞታ አታስተላልፉብን…።

ሲሉ ጠይቀው ነበር። ከአምስት ወራት በኋላ በሚያዝያ 1883 (April 1991) ለፈረንሳዩ ፕሬዚደንት በላኩት ደብዳቤ ደግሞ በጉዳዩ ዙሪያ የኢትዮጵያን አቋም እና የግዛት ድንበሯን ዳርቻ ጠቅሰው ተመሳሳይ ወደባህር የመተላለፊያ በር የማግኘት መብቷ እንዲከበር ጠየቁ።

> ከዚህ ቀደም የኢትዮጵያ የግዛት ዳርቻ ከባህሩ ይደርስ ነበር። አስፈላጊው አቅም ስላልነበረን … የጠረፍ ግዛቶቻችን በአረቦች እጅ ወደቀ። አሁንም የባህር ዳርቻ ግዛታችንን በኃይል የማስመለስ እቅድ የለንም። ነገር ግን ክርስቲያን የሆናችሁ ወንድሞቻችን የባህር ጠረፍ ግዛታችንን እንደምትመልሱልን ካልሆነም ቋሚ የባህር መዳረሻ በር እንደምትሰጡን እናምናለን። … ጥንታዊው የአገራችን ግዛትም ከሐምቦስ ወደ ምስራቅ አቅጣጫ እስከ አሳል ባህር፤ ከዚያም ከጥንት ጀምሮ ገባራችን የሆነውን የሞሐመድ አንፈሪን ግዛት ወደኛ በመተው እስከ አራፋል ይደርሳል።[16]

[16] ዝኒ ከማሁ

ነገር ግን ከኢትዮጵያ የጅቡቲ ህጋዊ ቅኝ ገገር ስለመሆንዋ መተማመኛ ለፈለገችው ፈረንሳይ ይህ የምንሊክ አቋም በቂ አልነበረም። በተደጋጋሚ በጅቡቲ ይዞታዋ በኩል የጦር መሳሪያ መተላለፏን እንደ መደራደሪያና መያዣ ስተጠቀመችበት ለፈረንሳይ ይህንን እውቅና ማግኘቱ አልከበዳትም። ከስድስት ዓመታት በኋላ ከኢትዮጵያ የተገኘው እውቅና ቅድመ ሁኔታ ነበረው። ፈረንሳይ አምና ከተቀበለቻቸው ቅድመ ሁኔታዎች መካከል ዋና ዋናዎቹ የጅቡቲን ግዛት ከኢትዮጵያ ማግኘቷን፤ ግዛቱን በቅኝነት ስትይዝ ለመልቀቅ ባሰበች ጊዜ ለኢትዮጵያ ልትመልስ መስማማቷን፤ እና ግዛቱንና የወደፊት ዕጣ ፈንታውን የሚመለከቱ ጉዳዮች በሙሉ የኢትዮጵያና ፈረንሳይ መንግስታት ብቻ ኃላፊነቶች መሆናቸውን የሚገልጹ አንቀጾች ይገኙባቸዋል። የጅቡቲ ግዛትንም በሚመለከት ሁለቱ አገሮች በጥር እና መጋቢት 1889 (January and March 1897) የተፈራረሟቸው ስምምነቶች እነዚህን ከላይ ተጠቀሱ ግዴታዎችና መግባባቶች የሚያንጸባርቁ ናቸው።[17]

ለአርባ ዓመታት የተደረገው በቀይ ባህር ጠረፍ ቅኝ ግዛት የመፍጠር ጥረት በመጨረሻ ውጤት አግኝቶ እ.ኤ.አ. በሰኔ 22፣ 1885 የፈረንሳይ ምክር ቤት ስለ አዲሱ የፈረንሳይ ግዛት አደረጃጀት የቀረበለትን ሃሳብ ያጸድቃል። በነሐሴ ወርም የፈረንሳይ መንግስት በአዋጅ "የፈረንሳይ ሱማሌ ግዛትና አከባቢዎቿ" የሚል መዋቅር በማቋቋም የጅቡቲ ግዛትን ሕጋዊ ሰውነት አረጋገጠ። በተለይም እ.ኤ.አ. በየካቲት 1889 ፈረንሳይና እንግሊዝ በፈረንሳይ ሱማሌና በእንግሊዝ ሱማሌ መካከል ያለውን ድንበር ለመከለል ያደረጉት ስምምነት ስለ ግዛቱ መፈጠር ዓለም አቀፋዊ ማረጋገጫ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል። ታላቋ ብሪታንያ ፈረንሳይ በታጁራና በኦቦክ የያዘችውን አገር የፈረንሳይ ግዛት


17 ዝኒ ከማሁ። ስለስምምነቶቹ ዝርዝር እና እንድምታ ቀጣይ ምዕራፎችን ተመልከት።

18 Shehim and Searing, 210-211.






ነው ብላ በማወቋ ምክንያትም ፈረንሳይ ከ1885 ጀምሮ በቀይ ባህር ምሥራቃዊ ጠረፍ የቅኝ ግዛት እንዳላት በይፋ አሳወቀች። በእንግሊዝና ፈረንሳይ የወሰን ስምምነት እንደሚያስረዳው አዲሱ የፈረንሳይ ሱማሌ ጠቅላላ ክልል 250 ሜትር ርዝመት እና ከ5-20 ኪሎ ሜትር ስፋት ነበረው። እ.ኤ.አ. በ1896 ታጁራን፣ ኦቦክን እና ጅቡቲን ያካተተው የፈረንሳይ ሱማሌ ግዛት (Côte Français des Somalis) በይፋ ተመሠረተ።[18]





የጅቡቲ ሡልጣኔቶችን አቀማመጥ የሚያሳይ ንድፍ

18 Shehim and Searing, 210-211.




የጅቡቲ ሡልጣኔቶችን አቀማመጥ የሚያሳይ ንድፍ




እ.ኤ.አ. በ1886 የፈረንሳይ ሱማሌ ግዛት የድንበር ክልል (በቀይ የተመለከተው





## 2.2. የድንበር መካለል

አፄ ምንሊክ በጥቅምት 1883 ለፈረንሳዩ ፕሬዚደንት ለሙሴ ሳድ ካርኖ በጻፉት ደብዳቤ "በቀይ ባህር ያለውን የባህሩን ጠረፍ፡ ፈረንሳይ መያዟን በምንቀበልበት በአሁኑ ጊዜ መብታችን ታውቆ አንድ ነጥብ ሊኖረን እንደሚገባ እናስታውቃለን:: ይህንንም ለማግኘት የምንደሰት ስንሆን በምንም ምክንያት የቀይ ባህር ጠረፋችን ለሌላ ሦስተኛ መንግስት እንዳይተላለፍ፡ እያስጠነቀቅን ነው" ሲሉ አስታወቁ:: ዳግመኛም በሚያዝያ 1883 (10 April 1891) የግዛታቸውን ክልል ለማሳወቅ ለአውሮፓ መንግስታት በላኩት ዘዋሪ ደብዳቤ የቀይ ባህር ጠረፍ፡ ቀድሞ የኢትዮጵያ ግዛት እንደነበር፣ አገሪቱ በደከመችበት ወቅት እንደተነጠቀች እና ቅኝ ገዢዎቹ "የክርስቲያን መንግስታት" የባህር ድንበሩን ይመልሳሉ ብለው እንጠሚጠብቁ አስታወቁ:: በፈረንሳይና በኢትዮጵያ መካከል ስለነበረው የድንበር ወሰን ሲገልጹም "ከሐምቦስ አንስቶ ያሰልን [አሳል] ባህር ጨምሮ የጥንቱ ዜጋችንን የመሐመድ ሐንፋሬን ግዛት ሁሉ ይዞ በባህር ዳር ዳር እየሄደ አልፋሌ ይደርሳል" ብለው ነበር::[19]

ፈረንሳይ የጅቡቲ ግዛቷን ለማስፋት ለአፄ ምንሊክ የፈቀደችውን በወደቡ በነፃ የመጠቀም መብት እንደ ውለታና ማስፈራሪያ መጠቀም ጀመረች:: በተለይ ኢትዮጵያ የተጋረጠባትን የቅኝ ገዢዎች የመስፋፋት አደጋ ለመቋቋም በብርቱ የምትፈልገው የጦር መሣሪያ ማስገቢያ የሆነውን ብቸኛ የባህር በር ላለማጣት ምንሊክ የተጠየቁትን ሊያደርጉ እንደሚችሉ በፈረንሳይ ዘንድ ግምት የተወሰደ ይመስላል:: ስለዚህም ከባህር ወደቡ አንስቶ ወደ ውስጥ ከሃምሳ እስከ ሰባ አምስት ኪሎ ሜትር ጥልቀት ያለው መሬት እንዲኖራቸው መወትወት ጀመሩ::

ሙሴ ላጋርድ ይህንኑ አስመልክቶ ለሐረሩ ገዢ ለልዑል ራስ መኮንን ባቀረበው ጥያቄ ለወደቡ መብት ውለታ ኢትዮጵያ በበኩልዋ የፈረንሳይና የእንግሊዝ ሱማሌ ወሰን የመጨረሻ

[19] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 34–38




እ.ኤ.አ. በ1886 የፈረንሳይ ሱማሌ ግዛት የድንበር ክልል (በቀይ የተመለከተው)

ነጥብ ከባይዱ ወደ ራሂሌ እንዲመጣ እና ጉባድ በከፊልና የአውሳ ሱልጣን ግዛት በሙሉ ለፈረንሳይ እንዲሆን አመለከተ። ፈረንሳይ በበኩልዋ የጠየቀችው ከታጁራ፣ አቦክና ከጅቡቲ ወደብ ጀርባ የሚገኘው የኢትዮጵያ መሬት በልዩ አጠራር "የውስጥ ክፍለ ሀገር" እንዲባልና ይህ ክፍለ ሀገር ከፈረንሳይ የባህር ጠረፍ ጋር የተያያዘ ሆኖ ይዞታው ግን የተለየ እንዲሆን፤ በዚሁ "የውስጥ ክፍለ ሀገር" ውስጥ የሚገኝ የኢትዮጵያ መንግስትና ዜጎች መብትና ጥቅም በተለይ የተጠበቀና የተከበረ እንዲሆን፤ ከዚህ "የውስጥ ክፍለ ሀገር" ፈረንሳይ መሬት ቆርሳ ለሌላ የውጭ መንግስት ሳትሰጥ እና ግዛቱን ለቃ በምትሄድበት ጊዜ ይህንኑ መሬት ለኢትዮጵያ መልሳ ልታስረክብ ግዴታ ልትገባ እንደምትፈልግ ሙሴ ላጋርድ አስታወቀ።

ይህን ጥያቄ ራስ መኮንን መጀመሪያ በብርቱ የተቃወሙት ቢሆንም እምቢታው በወደቡ በኩል መሣሪያ እንዳይገባ ሊያስከለክል ይችላል በሚል ፍራቻ ጉዳዩን ለንጉሠ ነገሥቱ አስተላለፉ። አፄ ምንሊክም በሃሳቡ በመስማማት በመጋቢት 12፣ 1889 (20 March 1897) ከሙሴ ላጋርድ ጋር ስምምነት ተፈራረሙ። በዚህም መሠረት የባህር ጠረፉ ከእንግሊዝ ሶማሊያ ሰሜናዊ ቀበሌ ከጃሌሎ በመነሳት በራሃሌ በኩል የዳጋን ተራራ አቋርጦ በጉባድ፣ በፎሮሌ፣ በአቤ ሐይቅ፣ በሜርጋዶ፣ በአሊ ሐይቅ ዳርቻ፣ በዳይሞሌ፣ በኢታጋ በኩል አድርጎ በራሄይቶ በማለፍ ዱሜራ ይደርሳል። እንዲሁም ስምምነት በተደረገበት ክልል ሦስተኛ ወገን ጣልቃ እንዳይገባበት እና የአሳል ሐይቅ የኢትዮጵያ መንግስት ርስት ሆኖ ኢትዮጵያ ዘላቂ ጨው የማምረት መብት እንዳለት ተረጋገጠ። በመጋቢት 1889 ስምምነት መሠረትም ፈረንሳይ ተጨማሪ 12,000 ኪሎ ሜትር መሬት ከኢትዮጵያ አገኘች።[20]

---


[20] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 41-49። ውጉሚ፦ ጅቡቲ 52-D3፤ የኢትዮጵያና ፈረንሳይ ስምምነት፡ መጋቢት 12፣ 1889

[21] ውጉሚ፦ ጅቡቲ 52-D3 21፤ Franco-Ethiopian Boundary Commission Agreement on Djibouti Frontier: Addis Ababa, 6 May 1953፤ የኢትዮጵያ መንግሥት ያቀረበው የወሰን ክለላ ሥነ ሥርዓት ንድፍ ፕሮቶኮል፡ ግንቦት 1945






በኢትዮጵያ እና በፈረንሳይ መንግሥታት የጋራ ኮሚሽን ሚያዝያ 28፣ 1945 ዓ.ም. (6 May 1953) ይፋ የሆነው የድንበር መካለል አፈፃፀም መርሐ ግብር (Procès-verbal) በአፍሪካ ቀንድ የአንድ ተጨማሪ ሉአላዊ ግዛት የመፈጠር ሂደትን በተጨባጭ ያበሰረ ክስተት ተደርጎ ሊወሰድ ይቻላል። ከሃምሣ ሰባት ዓመታት በፊት የተደረገው ስምምነት በግዛት ይገባኛል ጥያቄ ዙሪያ የመደራደሪያ ክፍተት ቢኖረውም እንኳ የኋለኛው የኢትዮጵያን መብት አሳልፎ የሠጠና ለፈረንሳይ ሱማሌ ግዛት ዕውን መሆን ህጋዊ ሰውነትን ያላበሰ ነው።[21]




የመጋቢት 12፣ 1889 የድንበር ስምምነት ንድፍ ካርታ




የመጋቢት 12፣ 1889 የድንበር ስምምነት ንድፍ ካርታ

ከጣሊያን የአምስት ዓመታት ወረራ ነፃ ተወጥቶ ሉዐላዊ ቁመናን መልሶ ለመገንባት በሚሞከርበት፤ የመንግሥት ሁለንተናዊ መዋቅር ከገጠመው በእንግሊዝ የመታፈን አደጋ ለማምለጥ በሚንፈራገጥበት አስቸጋሪ ወቅት እና የኢትዮጵያን የግዛት አንድነት ጠብቆ ማቆየት የጊዜው አንገብጋቢ አጀንዳ በነበረበት ሁኔታ በ19ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ የተደረጉ የድንበር ስምምነቶችን በነበሩበት ማስቀጠሉ የስኬት አካል ተደርጎ ቢወሰድ ብዙም አያጨቃጭቅም። ኢትዮጵያ ከፈረንሳይ ጋር በጅቡቲ ድንበር ጉዳይ ያደረገችው የ1945ቱ ውል ከዚህ የታሪክ ዕውነታ አንፃር መታየቱ አግባብ ቢሆንም ከግዛቱ ሁለንተናዊ ጠቀሜታ በመነሳት ሲገመገም ግን በሂደት የታየው የባለቤትነት መብትን ለዘለቄታው አሳልፎ የመስጠቱ ሁለተኛው ምዕራፍ ተደርጎ ሊወሰድ ይቻላል።

ከዚህ በፊት ሁለቱ መንግሥታት በ1937 በድንበር ጉዳይ የመግባቢያ ፕሮቶኮል የፈረሙ ሲሆን በሰኔ 1939 ገቢር የሆነ ማስታወሻ ተለዋውጠዋል። በነኝህ ጊዜያት በተደረሱ ሰነዶች በመጀመሪያ ከጃሌሎ (ኢትዮጵያ፣ እንግሊዝ ሱማሌ እና ፈረንሳይ ሱማሌ መገናኛ ነጥብ) እስከ ዲክር-ኮማ ቀጥሎም ከዲክር-ኮማ እስከ ዳዳቶ (ኢትዮጵያ፣ ጅቡቲ እና ኤርትራ መገናኛ ነጥብ) ያለው ድንበር ተከለለ። የድርድሩ ዋነኛ ነጥብ ፈረንሳይ እስከ ኤርትራ ድንበር መዳረሻ ብቻ ለመከለል ያቀረበችው አስገዳጅ ቅድመ ሁኔታ ነበር። የመከለል ሂደቱንም የሚከታተል የጋራ ኮሚሽን ተቋቋመ።[22]

የሚያዝያ 1945ቱን ስምምነት ተከትሎ በኢትዮጵያ በኩል የታየው ለጉዳዩ አፋጣኝ ዕልባት የመስጠት ፍላጎት ከዘልማዳዊው እሳቤ በተሻራረ ግፊቱ በተለይ የአንድ ወገን እንደነበር ያመላክታል። ለምሳሌ በወቅቱ የተላለፈ አንድ መመሪያ ከጃሌሎ እስከ ዳዳቶ ያሉትን የድንበር ምልክቶች የማስቀመጡ ተግበር ቢበዛ በአሥራ አምስት ቀናት ውስጥ መጠናቀቅ

[22] ውጉሚ፡- ኬንያ 64-D4 11፤ የ1955-56 የድንበር ጥናት ሪፖርት





እንዳለበት ሲያሳስብ፤ የተለየ ምክንያት ከሌለ በስተቀር በወቅቱ ከኢትዮጵያ ጋር በፌደሬሽን የተቀላቀለችው ኤርትራ ከጅቡቲ ጋር የነበራት ድንበር ጣሊያን እ.ኤ.አ. በ1935 ከፈረንሳይ ጋር በተናጠል በተፈራረመችው የድንበር ውል መሠረት መቀበሉ እምብዛም ችግር እንደማያስከትል ይከራከራል።[23]

ይህም በመጀመሪያ አከባቢ የኤርትራን እና የጅቡቲን ድንበር በአዲስ መልክ ስለመከለል ኢትዮጵያ ስታራምደው የነበረውን አቋም ሙሉ በሙሉ የቀየረ ነበር። የቀደመው አቋም የድንበር መስመሩ ከዳዶቶ ተነስቶ በቀጥታ መስመር ከራስ ዱሜራ በስተደቡብ በሙሉየሌ (Mouloule) ትይዩ እንዲሆን ነበር። በሂደት የተስተዋለው መለሳለስ ኤርትራን ከማስመለስ ትግሉ አንፃር የፈረንሳይን ሁለንተናዊ ድጋፍ ከስሌት በማስገባት እንደሆነ መገመት አያዳግትም። በተጨማሪም ጅቡቲን ለዘለቄታው የኢትዮጵያ አካል የማድረጉ እሳቤ በፈረንሳይ በጎ ፈቃድ ላይ ብቻ የተመሠረተ ተደርጎ መወሰዱም የመለሳለሱ ምክንያት ሊሆን ይችላል። በተከታታይ በኢትዮጵያ ባለሥልጣናት መካከል የተደረጉ የደብዳቤ ልውውጦች የንጉስ ነገስቱ መንግስት የድንበር መከለሉን ሥራ በአፋጣኝ ለመጨረስ የነበረውን ቁርጠኝነት የሚያንፀባርቁ ሲሆን ይህም መሆኑ ለአገሪቱ የኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ እንደሚኖረው አበክረው ያስገነዝባሉ።[24]

ይልቁንም በጊዜው የኢትዮጵያ አጠቃላይ ጥረት ያተኮረው አፋምቦ የተሰኘውን ስትራተጂካዊ አከባቢ ማስመለሱ ላይ ነበር። ከ1945ቱ የጋራ የድንበር ኮሚሽኑ ውል በኋላ ይህ ጉዳይ ከንጉስ ነገሥቱ ጀምሮ ያሉትን አካላት ቀጥተኛ ተሳትፎ የጠየቀ አስቸኳይ ሃገራዊ አጀንዳ ሆነ። በዚህ ስምምነት መሠረት ፈረንሳይ አፋምቦን በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ለኢትዮጵያ ለመመለስ በጎ ፈቃድ ብታሳይም እስከ ጥር 1946 ድረስ ግን ተግባራዊ አላደረገችውም። ይህም በሁለቱ መንግስታት መካከል አዲስ የዲፕሎማሲ ትግልን አስከተለ።

[23] ውጉሚ፡- ጅቡቲ 52-D3 21፤ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ለሀገር አስተዳደር ሚኒስቴር፡ ግንቦት 12፣ 1945፤ የሀገር አስተዳደር ሚኒስቴር ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፡ ግንቦት 24፣ 1945

[24] ዝኒ ከማሁ

በንጉሰ ነገስቱ ትዕዛዝ በፓሪስ ስለጉዳዩ እየተነጋገሩ የነበሩት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ጸሐፊ ትእዛዝ አክሊሉ ሐብተወልድ የላኩት ሪፖርት ስለ አጠቃላይ ሁኔታው የተሻለ ሥዕል ይሰጣል። ፈረንሳይ አፋምቦን በመውረር ከጅቡቲ ግዛቷ የቀላቀለችው እ.ኤ.አ. በ1944 ሲሆን ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ኢትዮጵያ ለውዝግቡ ሠላማዊ ዕልባት ስትሻ ቆይታለች። ሆኖም በተከታታይ በተደረጉ የድንበር መካለል ንግግሮች በሙሉ ፈረንሳይ የአፋምቦን ወደ ኢትዮጵያ መመለስ ከተቀረው የጋራ ወሰን ክለላ መጠናቀቅ ጋር በማቆራኘት በመያዣነት ስትገለገልበት እንደነበር ሪፖርቱ ያትታል።[25]

አክሊሉ በፓሪስ ቆይታቸው ለአሥር ዓመታት ያህል ያለመፍትሄ የዘለቀውን ችግር በሠላማዊ መንገድ ለመቅረፍ በተደረገው ጥረት የመንግሥታቸው ትዕግስት መሟጠጡን እና ካስፈለገም ኢትዮጵያ አፋምቦን በኃይል የማስመለስ አማራጭን ለመከተል እንደምትገደድ ለፈረንሳይ ባለሥልጣናት ገልፀዋል። ይልቁንም በነኚህ ጊዜያት አገራቸው የፈረንሳይ ጥቅምና ተዕዕኖ በኢትዮጵያ እንዲስፋፋ ከመጠን ያለፈ በጎ ፍቃድ ማሳየቷን እና በተለዋጭ ኢትዮጵያ ለጠየቀችው የአፋምቦ መመለስ የፈረንሳይ ምላሽ አፍራሽ መሆኑን አብራርተዋል።

እንደ አክሊሉ መከራከሪያ ከጣሊያን ወረራ በፊት በምድር ባቡሩ ብቻ ይገለፅ የነበረው የፈረንሳይ ጥቅም ከነፃነት በኋላ በሊሴ ትምህርት ቤት፣ በፓስተር ኢንስቲትዩት፣ በአርኪዮሎጂ ጥናት ዘርፍ፣ የኢትዮጵያን የፍታሐ ብሔር ህግ በማዘጋጀት ወዘተ የተሰጣቸው የልዩ ተጠቃሚነት መብት በአፋምቦ ዙሪያ ለተነሳው ጥያቄ አፋጣኝ መፍትሄ እንዲሰጡ ያስገድዳቸዋል። በመጨረሻም የፈረንሳይን ቸልተኝነት እና ከተፈራረመቻቸው ውሎች ማፈግፈግ በመረጃ በማስደገፍ በማብራራት እና ስለ አፋምቦ የመንግሥታቸውን ቁርጥ አቋም በመግለፅ ፈረንሳይ በኃይል የያዘችውን ግዛት በአስቸኳይ እንድትመልስ ማሳመን ቻሉ።

[25] ውጉሚ፡- ጅቡቲ 52-D3 21፤ አክሊሉ ሐብተወልድ ለጃንሆይ፡ እ.ኤ.አ 7 ህዳር 1953 (ጥቅምት 1946 ዓ.ም.)






የፓሪሱን ንግግር ተከትሎ ሁለቱ መንግሥታት በጥር 7፣ 1946 ዓ.ም. (16 January 1954) አዲስ አበባ ላይ በተፈራረሙት የፕሮቶኮል ስምምነት እና ባወጡት የጋራ መግለጫ ላለፉት አሥር ዓመታት ሲከናወን የነበረው የኢትዮጵያ እና ጅቡቲ የጋራ የድንበር ኮሚሽን ሥራ በስኬት መጠናቀቁን እና አፋምቦም በስድስት ሳምንታት ውስጥ ሙሉ በሙሉ ለኢትዮጵያ እንደሚመለስ በይፋ ተገለፀ።[26] በተያያዥም ሁለቱ ተደራዳሪዎች የአጠቃላይ ድንበሩን አቀማመጥ (የኤርትራ-ጅቡቲን ድንበር ጨምሮ) ለመወሰን (delemitation) ከስምምነት ተደረሰ። የሚመለሰውን መሬት ጉዳይ እና የድንበሩን አጠቃላይ መካለል የሚከታተል የጋራ ኮሚሽን ለማቋቋም በተወሰነውም መሠረት ኢትዮጵያ አቶ አበበ ገብረፃድቅን ሙሉ ስልጣን በመስጠት በተለይ የአፋምቦን መመለስ ጉዳይ እንዲያስፈፅሙ ሾመች።

ሁለቱም ወገኖች አፋምቦን የመረካከቢያው ቀን እሁድ የካቲት 20፣ 1946 ዓ.ም. (28 February 1954) እንዲሆን ቢስማሙም የተለያዩ እንቅፋቶች አተገባበሩን መፈታተናቸው አልቀረም። የመጀመሪያው ተቀማጭነታቸውን በፓሪስ ያደረጉ የጅቡቲ ተወላጆች ያስነሱት ተቃውሞ ሲሆን የዚህን አሉታዊ ውጤት በመፍራት ኢትዮጵያ ያቀረበችው ከቀነ ገደቡ በፊት አፋምቦን የመረከብ ጥያቄ በፈረንሳይ ተቀባይነት ማጣቱም ለመንግሥት ባለሥልጣናት ፈታኝ ነበር። በተለይም ፈረንሳይ ለቅኝ ግዛቶቿ በሙሉ በሰጠችው አዲስ የውስጥ አስተዳደር መብት (Loi-Cadre) በመጠቀም ሁለት ዋና የጅቡቲ ፖለቲከኞች - ሴናተር ሐሰን ጉሌድ አፕቲዶን እና የዩንየን ፍራንሴዝ ምክር ቤት አባሉ ማህሙድ ካሚል - የአከባቢው ነዋሪዎች ፍላጎት

[26] ውጉሚ፡- ጅቡቲ 52-D3 21፤ የአዲስ አበባው የፕሮቶኮል ስምምነት እና የጋራ መግለጫ፡ እ.ኤ.አ. 16 January 1954፤ ብላታ ዳዊት ዕቁበእግዚ (ምክትል የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር) በኢትዮጵያ የፈረንሳይ አምባሳደር ሩ (Ambassador Roux)፡ እ.ኤ.አ. 26 January 1954

ሳይጠየቅ የአፋምቦ ለኢትዮጵያ መመለስ አግባብ አይደለም በማለት ለፈራንሳይ ምክር ቤት ክስ ማቅረባቸው ጉዳዩን አስቸጋሪ አድርጎት ነበር።[27]




የኢትዮጵያና ጅቡቲ ድንበር (ምንጭ፡ ውጉማ ፈረንሳይ ሶማሌ 4 8)

[27] ውጉማ፡- ጅቡቲ 52-D3 21፤ ቆንስል ምንዳ ሚካኤል (ጅቡቲ) ለአክሊሉ ሐብተወልድ፡ ጥር 27፣ 1946፤ ብላታ ዳዊት ዕቁበእግዚ ለኮሎኔል ክፍሌ እርገቱ (የአገር አስተዳደር ሚኒስትር)፡ የካቲት 18፣ 1946፤ ብላታ ዳዊት ዕቁበእግዚ ለአሥራት ዘለቀ (በፈረንሳይ የኢትዮጵያ ጉዳይ ፈፃሚ)፡ የካቲት 24፣ 1946፤ አሥራት ዘለቀ ለጃንሆይ፡ የካቲት 27፣ 1946





በስተመጨረሻ የኢትዮጵያ መንግስት ባሳሰበው መሠረት የፈረንሳይ ምክር ቤት ስምምነቱ በተያዘለት የጊዜ ገደብ እንዲከናወን በመወሰኑ አፋምቦ እንዲመለስ ሆነ። የጋራ ኮሚሽኑ መሐንዲሶችም ከጃሊሎ እስከ ቀይ ባህር ድረስ ያለውን የኢትዮ-ጅቡቲ የድንበር ምልክቶችን ትክክለኛ አቀማመጥ (coordinates) በጥር 1948 አጠናቀቁ። በዚህ መካከል ግን የድንበር መለያ ምልክቶቹ ዝርዝር (geodesic and topography fiches) የተጠናቀረው በአንድ ግልባጭ የነበረ መሆኑና ይህንኑ ጥቅል ሰነድ ህጋዊ የድንበር ካርታውን ለመስራት ኃላፊነት ወስዶ የነበረው የፈረንሳይ ቡድን በውሰት ወስዶት የተወሰነውን ክፍል ለኢትዮጵያ ሳይመልስ መቅረቱ የዚህ ድርድር ያልተቋጨ ክፍል ሆኖ ቀረ።[28]

## 2.3. የጅቡቲ የውስጥ ፖለቲካ ጅምር

እስከ ሁለተኛው የዓለም ጦርነት ፍፃሜ ድረስ የግዛቱ ህዝብ በአስተዳደራዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ምንም ዓይነት ተሳትፎ አልነበረውም። ከቅኝ ገገርው እገዳም ባሻገር የአፋርና ኢሳ ጎሳዎች ንቃተ ህሊና ያለመዳበሩና ፍላጎት ማጣት ለፖለቲካዊ እንቅስቃሴ አለመታየት እንደምክንያት ይጠቀሳል። ፖለቲከኞች ቢኖሩ እንኳን ከመጤዎቹ የፈረንሳይና አረብ ሰፋሪዎች የተውጣጡ ነበሩ። ፈረንሳይ በ1938/39 (እ.ኤ.አ. 1946) የመጀመሪያውን የተወካዮች ምክር ቤት መቋቋም ስትፈቅድም ወንበሮቹን መያዝ የቻሉት እነዚሁ መጤ ፖለቲከኞች ሆኑ። ከዚህ ጋር በተያያዘ በሂደት በጅቡቲ ለተከሰተው ፖለቲካዊ መነቃቃት ሁለት አካባቢያዊ ክስተቶች አስተዋጽኦ እንዳበረከቱ ይታመናል። እነሱም በጋማል አብዱል ናስር መሪነት በግብፅ የተነሳው አብዮት እና በአልጄሪያ ከፈረንሳይ ቅኝ ለመላቀቅ የተደረገው የረጅም ጊዜ

[28] ውጉማ፡- ጅቡቲ 52-D3 21፤ የአገር ግዛት ሚኒስቴር ለወጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፡ መጋቢት 15፣ 1948። ከነዚህ ሰነዶች (fiches) መካከል ከምልክት 1-22 ያሉት በሂደት ለኢትዮጵያ የተመለሱ ቢሆን ከምልክት 23-89 ያሉት ግን ስለመመለሳቸው የሚገልጽ መረጃ አልተገኘም።




የኢትዮጵያና ጅቡቲ ድንበር (ምንጭ፡ ውጉሚ ፈረንሳይ ሶማሌ 4 8)

ጦርነት ናቸው። የመጀመሪያው የጅቡቲን የብሔረተኝነት ስሜት ለመቀስቀስ የረዳ ሲሆን ሁለተኛው የፈረንሳይን ቅኝ ገዢነት ማስወገድ እንደሚቻል መልዕክት አስተላለፈ። በተጨማሪም ከ1950ቹ በኋላ በእንግሊዝ እና ጣሊያን የሶማሊያ ግዛቶች የተቀጣጠለው የፓን ሶማሌ የፖለቲካ ንቅናቄ በተለይ የጅቡቲ ኢሳዎችን ለትግል ያነሳሳ ሌላኛው ኃይል ነበር። በዚህ ረገድ አፋሮቹ ተሳትፎ ዘግይቶ የመጣና የተቀናጀ አልነበረም።[29]

በሰኔ 1949 ፈረንሳይ ለቅኝ ግዛቶቿ የፈቀደችው የውስጥ አስተዳደር መብት (Loi-Cadre) ኢትዮጵያ በጅቡቲ ላይ ለረጅም ጊዜ ስታራምድ ለቆየችው የግዛት አለኝታ ጥያቄ መደናቀፍ ሁለተኛው ምክንያት ሆነ። ቀድሞ የነበረው የግዛቱ ምክር ቤት (Conseil Représentatif) ስለግዛቱ ሁኔታ የቀረቡለትን ጉዳዮች መርምሮ ከአስተያየት ጋር ለአገረ ገዢው የመመለስ ድርሻ ቢኖረውም የመጨረሻውን ውሳኔ የማስተላለፉ ስልጣን ግን የባህር ማዶ ግዛቶች ሚኒስቴር (France d' outremer) ነበር። ይህ ምክር ቤት 25 አባላት የነበሩት ሲሆን ከነዚህ 12ቱ ፈረንሳዮች የተቀሩት የአገር ተወላጆች ናቸው።[30]

በአዲሱ ህግ መሠረት የተቋቋመው ምክር ቤት (Assemblie Territoriale de la C.F.S.) ግን ከቀድሞው የበለጠ

[29] Shehim and Searing, 211-212. Thompson and Adloff, 61-71. Saadia Touval, *Somali Nationalism* (Cambridge, 1963), 123-131; David D. Laitin, "Somali Territorial Claims in International Perspective," in *Africa Today*, Vol. 23 (April-June 1976), 29-38. Mohamed Kadamy, "Djibouti: Between War and Peace," in *Review of African Political Economy*, Vol. 23, No. 70 (Dec. 1996), 513-515. Nancy A. Shilling, "Problems of Political Development in a Ministate: The French Territory of the Afars and the Issas," in *The Journal of Developing Areas*, Vol. 7, No. 4 (Jul. 1973), 619-620.

[30] ውጉማ:- ፈረንሳይ ሱማሌ 1 776፤ ቆንስል ምንዳ ሚካኤል (ጅቡቲ) ለአዘሉስ ሐብተወልድ፡ ሰኔ 27 እና ሐምሌ 1፤ 1949





ሥልጣን እንዲኖረው የተፈቀደ ሲሆን፤ ከፈረንሳዮችና ያገር ተወላጆች የሚመረጡ 30 አባላት ይኖሩታል። በተጨማሪም ከነዚሁ የምክር ቤት አባላት መሐከል ወይም ከውጭ የተውጣጡ የሚኒስትር ዓይነት ሥልጣን የሚኖራቸው ስድስት ያገር ተወላጆች ተመርጠው የሚኒስትሮች ምክር ቤት (Conseil du gouvernement) ያቋቁማሉ። ፈረንሳዊው አገረ ገዥም የካቢኔው ፕሬዚደንት ወደመሆን ሲሸጋገሩ ከስድስቱ መካከል አንዱ የምክትል ፕሬዚደንትነት ሥልጣን ይዞ ፕሬዝደንቱ በሌሉበት ተክተቸው ይሠራል። የዚህ ህግ መሠረታዊው ልዩነት ሁለቱ ምክር ቤቶች ጅቡቲን በተመለከተ ማናቸውንም ጉዳዮች የመወሰን ሙሉ ሥልጣን ማግኘታቸው ነው።

እ.ኤ.አ. ሰኔ 23፣ 1957 በተደረገው የምክር ቤት አባላት ምርጫ ሁለት ቡድኖች ዕጩዎቻቸውን አቀረቡ። በሐሰን ጉሌድ አፕቲዶን የሚመራው አንጃ አሥራ ሦስት ከሶማሌ እና ከደንከል ጎሳዎች የተውጣጡና አምስት ፈረንሳዊያን የሚገኙበት ተወዳዳሪዎችን ሲያቀርብ፤ በማህሙድ ሐርቢ የሚመራው ተቀናቃኝ ቡድን ደግሞ አምስት ፈረንሳዊያን፣ ሦስት አረቦች እና አሥር ሶማሌዎችን ለውድድር አሰለፈ። ኢትዮጵያን ጨምሮ በአብዛኛው ታዛቢ ዘንድ የሐርቢ ፖለቲካ የጋማል አብዱል ናስርን ፓን-አረብ ፍልስፍና ወደ ግዛቱ ለማስገባት ስለሚጥር ተቀባይነት አያገኝም በሚል የማሸነፍ ቅድሚያ ግምት ለምዕራብ ዘመሙ የአፕቲዶን ቡድን ሰጥተው ነበር። ሁሉንም ባስገረመ መንገድ ግን ማህሙድ ሐርቢ ማሸነፋቸው ይፋ ሆነ።

የውስጥ አስተዳደር መብቱ ሲፈቀድ ስድስት ያገር ተወላጆች የሚኖሩት የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይቋቋማል የሚለው ደንብ የተወሰነ ማሻሻያ ተደርጎበት ከሠላሳው የምክር ቤት አባላት የተውጣጡ ስምንት ሚኒስትሮች ያሉት ካቢኔ እ.ኤ.አ. በሐምሌ 23፣ 1957 ተመረጠ። ማህሙድ ሐርቢ በከፍተኛ

ድምፅ የምክትል ፕሬዚደንትነቱን ቦታ ሲያገኝ አጠቃላይ የካቢኔ ተዋጽኦው ሦስት የኢሳ ጎሳ አባላትን፣ ሁለት ደንከል (አፋር)፣ አንድ ሐበሬወል፣ አንድ ፈረንሳዊ እና አንድ አረብ ያካተተ ነበር። የአፋር ጎሳ ተወካዮቹ የተሰጣቸው የሥራ ድርሻ እምብዛም ወሳኝ ያልነበሩት የጤና እና የእርሻ ሚኒስትርነት መሆኑ በስብጥሩ የነበራቸውን ዝቅተኛ ሚና ያመላክታል። ከምክር ቤቱ አባላትም ስድስቱን ፈረንሳዊያን ሳይጨምር አብላጫውን ወንበር የያዙት የኢሳ፣ ሱማሌና አረብ ዝርያ ያላቸው ግለሰቦች ነበሩ። ይህ አወቃቀር በጅቡቲ የውስጥ ፖለቲካ የሱማሌ-አረብ ጥምረትን የበላይነት የሚያንፀባርቅ ሲሆን በተለይ የኢትዮጵያን ቀጣይ የፖሊሲ አቅጣጫ ለዘለቄታው ከመቅረፅ አንፃር ትልቁን አስተዋፅኦ አበርክቷል።[31]

በጅቡቲ ይህን የመሰለ ለውጥ እየተከናወነ በነበረበት ወሳኝ ወቅት የኢትዮጵያ መንግስት ባለስልጣናት ግንዛቤ ከሂደቱ ጋር የሚመጣጠን ነው ብሎ ለመገመት ያዳግታል። ከውስጥ አስተዳደር መብቱ መሰጠት እና ከምርጫው ጋር በተገናኘ የተያዘው አቋም በአጭሩ የፈረንሳይ ሶማሌ (ጅቡቲ) ራሱን ችሎ ለመተዳደር የሚችልበት ደረጃ ላይ አለመድረሱን ያትታል። ይልቁንም ፈረንሳዮች ምርጫ እንዲደረግ መፍቀዳቸው ለቅኝ አገሮቻቸው የናሽናሊዝም መንፈስ ማረጋጊያ ካቀዱት ፖሊሲ የመነጨ ስለመሆኑ ይከራከራል። በኢትዮጵያ ግምት የፈረንሳዮች ዋነኛ አጀንዳ ጎረቤት የሆነው በጣሊያን ሞግዚትነት የሚተዳደረው ሱማሌ በቅርቡ ሙሉ ነፃነት የሚያገኝ በመሆኑ ይህ በጅቡቲ ሊያስከትል የሚችለውን ፖለቲካዊ መነቃቃት የማለዘብ ጥረት ተደርጎ ተወስዷል።[32]

[31] ውጉሚ፡- ፈረንሳይ ሱማሌ 1 776፤ ቆንስል ምንዳ ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፡ ሐምሌ 25 እና ነሐሴ 16፣ 1949፤ ስለ ጅቡቲ የምክር ቤት እና የካቢኔ ምርጫ የተዘጋጀ ሪፖርት፡ ነሐሴ 29፣ 1949

[32] ውጉሚ፡- ፈረንሳይ ሱማሌ 1 776፤ አክሊሉ ሀብተወልድ ለቆንስል ምንዳ ምካኤል፡ ሐምሌ 12፣ 1949





የተመረጡ የካቢኔ አባላትን አገር የማስተዳደር ብቃት በእጅጉ ያናናቀው የኢትዮጵያ ባለሥልጣናት ወቅታዊ ትንታኔ ትኩረቱን ያደረገው በጊዜው ታላቋ ሱማሌን የማቋቋም አጀንዳ ቡበርቱ ይቃወሙ የነበሩት የጅቡቲ ገገር (Mr. Petitbon) ወደ ፓሪስ የመጠራታቸው እና ያለመመለሳቸው ጉዳይ ላይ ነበር። በተጨማሪም እምነት ተጥሎባቸው የነበሩት ሐሰን ጉሌድ እና አጋሮቻቸው በሽንፈታቸው ማግስት ወደ ፈረንሳይ አቅንተው ያቀረቡት የተጭበረበረናልና የምርጫው ይደገም ክስ ሂደትንም መከታተል ሌላው የትኩረት አቅጣጫ ተደርጎ በስፋት የመስተናገድ ዕድል ተችሮታል። የኢትዮጵያን መሃሊ የፖሊሲ አቅጣጫ ከወሰኑ አጋጣሚዎች መካከል አንዱ ይህ በሱማሌ-አረብ ጥምረት እና የበላይነት ላይ እያደገ የመጣው ጥርጣሬ ነው።[33]

የማህሙድ ሐርቢ ወደ ታላቋ ሶማሊያ እና ግብፅ ያደላ የፖለቲካ መሥመር በኢትዮጵያ እና በቅኝ ገዢው የፈረንሳይ መንግሥት ላይ ከፍተኛ ስጋት ማስከተሉ አልቀረም። ሁለቱ አካላት በመቀናጀት ያደረጉት እንቅስቃሴም ሐርቢን ከሥልጣኑ ማስወገድ አስቻለ። በተደጋጋሚ የተደረገበት የመግደል ሙከራ በጅቡቲ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ውስጥ እንዳይሳተፍ ከደረሰበት መገለል ጋር ተደማምሮ ግዛቱን ለቆ እንዲሰደድ አደረገው።[34] ይህም ሆኖ የሐርቢን ግቦት ተከትሎ የግዛቱን ፖለቲካ ይመሩ የነበሩት እንደነ አህመድ ዲኒ፣ ሴናተር ካሚል (አፋር)፣ አሊ አሬፍ እና ሐሰን ጉሌድ (ኢሳ) ያሉት መሪዎች በሂደት የብሔረተኝነት ስሜት ማዳበራቸው እና የጅቡቲን አፋጣኝ ነፃነት መሻታቸው አጠቃላይ የግዛቱ ጉዳይ ከኢትዮጵያ ፍላጎትና ቁጥጥር እየወጣ መምጣቱን አመላካች ሆነ።

[33] ውጉሚ፡- ፈረንሳይ ሱማሌ 1 776፤ አክሊሉ ለቆንስል ምንዳ፡ ነሐሴ 30፣ 1949

[34] ውጉሚ፡- ፈረንሳይ ሱማሌ 1 776፤ ቆንስል ምንዳ ሚካኤል (ጅቡቲ) ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር። በጅቡቲ ፖለቲካና በሐርቢ ፀረ-ፈረንሳይ እንቅስቃሴ ዙሪያ የቀረበ ሪፖርት፡ ጥር 2፣ 1951፤ ጅቡቲ ቆንስል ለ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር። ሐርቢን ስለመግደል የታቀደ የኢትዮ-ፈረንሳይ ውጥን፡ መጋቢት 24፣ 1951

በኢትዮጵያ ወገን ብቸኛው መዕናኛ የነበረው የጅቡቲ ብሔረተኝነት በሁለት ዕንፍ መቆሙ ነበር። አብላጫው የደንከል (አፋር) ፖለቲከኞች እና ሐሰን ጉሌድን የመሳሰሉ ለዘብተኛ የኢሳ ተወላጆች በሂደት ሉዓላዊ አገር የመመስረት ምኞት ያንፀባረቁ ሲሆን በተለይም የተቀሩት ወገኖች የሚያራምዱትን ከአዲሲቱ ሶማሊያ ጋር የመዋሐድ ሐሳብ በጥብቅ ይቃወሙ ነበር።[35]

## 2.4. የታላቋ ሱማሌ ህልም፣ የግብፅ ምኞት እና የቀዝቃዛው ጦርነት ተዕዕኖ

የሁለተኛው የዓለም ጦርነት ፍፃሜን ተከትሎ በአፍሪካ ቀንድ የተለያዩ ኃይሎች የግልና የወል ጥቅሞቻቸውን ለማራመድ ከመቼውም ጊዜ በላይ መሰባሰብ ጀመሩ። የእንግሊዝ ታላቋ ሱማሌን የመፍጠር ውጥን፣ የአሜሪካ እና የሶቭየት ህብረት አከባቢውን በበላይነት የመቆጣጠር እሽቅድምድም፣ የግብፅ ፓን-አረብ ፍልስፍናና የአፍሪካ ቀንድን በተዕዕኖዋ ሥር የማዋል ተስፋ፣ የጣሊያን ሱማሌ እና የእንግሊዝ ሱማሌ በ1952 ነፃ መውጣትና መዋሃድ ተከትሎ ማራመድ የተጀመረው በክልሉ የሚገኙ የሶማሊኛ ተናጋሪ አከባቢዎችን የማዋሐድ እንቅስቃሴ (Somaliazation) ወዘተ የዘርፈ ብዙው እና ውስብስቡ ችግር ዋነኛ መንስኤዎች ነበሩ።[36] የነዚህ ክስተቶች ድምር ውጤት ኢትዮጵያ በጅቡቲ ላይ የተከተለቻቸውን ተለዋዋጭ ፖሊሲዎች ከመወሰን አንፃር መሠረታዊ ሚና ከማበርከታቸውም ባሻገር ግዛቷንም ለዘለቄታው ለማጣት ሦስተኛው ምክንያት ተደርጎ ሊወሰድ ይቻላል።

[35] ውጉሚ፡- ፈረንሳይ ሱማሌ 1 776፤ ቆንስል ምንዳ ለንጉሰ ነገስቱና ለልጅ እንዳልካቸው መኮንን (ውጉሚ ረዳት ሚኒስትር)። በጅቡቲ ፖለቲካ ላይ የቀረበ ሪፖርት፡ ታህሳሥ 16 እና መጋቢት 8፣ 1950፤ ውጉሚ፡- ፈረንሳይ ሱማሌ 1 776-2፤ ስለ ጅቡቲ ፖለቲከኞች አመለካከት የቀረበ ማስታወሻ፡ ግንቦት 4፣ 1950፤ ውጉሚ፡- ፈረንሳይ ሱማሌ 1 776-2፤ ጅቡቲ ቆንስላ ለ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፡ ሰኔ 15፣ 1952

[36] Laitin, 29-38





ከቀዝቃዛው ጦርነት መገለጫ ባህርያት መካከል አንዱ የተዕዕኖ ክልሎችን የመፍጠር (Spheres of Influence) ጥረት ሲሆን የአፍሪካ ቀንድ ይህ እንቅስቃሴ በጉልህ ከተስተዋለባቸው የዓለማችን ክፍሎች ዋነኛው ነበር። አሜሪካንን የሚያካትተው የምዕራባውያን ጥምረት በክልሉ የኮሚኒስት ርዕዮተ ዓለምን መስፋፋት ለመገደብ ያለመ መርህ ሲያራምድ፤ የራሺያ እና ግብፅ ቡድን በተቃራኒው የፓን-አረብ ዕንሰ ሐሳብን የተመረኮዘ ግራ ዘመም ፖሊሲ በስፋት መተግበር ጀመረ። ታላቋ ሱማሌን የመመስረቱን እቅድ ሁለቱም ጎራዎች በአመዛኙ የሚስማሙበት ቢሆንም በአተገባበሩ እና ዓላማው ዙሪያ ግን ከስትራቴጂካዊ ፍላጎታቸው የሚመነጭ ተቃራኒ አተያይ ነበራቸው።

ከዚህም አንፃር የአረቡን ዓለም ጥቅም ወደ አፍሪካ ቀንድ ብሎም ወደ መካከለኛው አፍሪካ ክፍል ለማስፋፋት የሚያልመው ግብፅ መራሹ እንቅስቃሴ ጠንካራ የሆነ እስላማዊ የሶማሊያ መንግሥት መመስረትን ይደግፋል። ምዕራባውያኑ በበኩላቸው የታላቋ ሱማሌን መርህ አከባቢውን ከኮሚኒስት መስፋፋት ለመከላከል በሚያችል መልኩ ብቻ በደምሳሳው የሚደራጅ የህብረት መንግሥት እንዲሆን ይመኛሉ። ከኒለኞቹ ወገን ፈረንሳይ የዚህ ዕቅድ ብቸኛ ተቀናቃኝ ሆና ቀረበች። ይህም የጅቡቲ ግዛቷን ላለማጣት ከነበራት ፍላጎት ይመነጫል።

በዚህ ውስብስብ ሂደት ኢትዮጵያ የያዘቻቸው አቋሞች እና የወሰደቻቸው እርምጃዎች ጅቡቲን ለዘለቄታው የህልውናዋ አካል የማድረጉን ጥረት በብርቱ የፈተነ ሆነ። የታሪክ ዑደቱ አገሪቱን የሁለቱም ጎራዎች ተቀናቃኝ ሲያደርጋት በተለዋጩ

[37] ውጉሚ፡- ሱማሌ 5 8-1B፤ ይልማ ደሬሳ (ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር) ለንጉሰ ነገስቱ። ከአሜሪካ እና እንግሊዝ አምባሳደሮች ጋር በጉዳዩ ዙሪያ ስላካሄዱት ውይይት ያቀረቡት ሪፖርት፡ ጥር 7፣ 1951። የአሜሪካ እና እንግሊዝ የጋራ እቅድ (The Anglo-American Demarche)፡ እ.ኤ.አ. ጥር 12፣ 1959. በተጨማሪም John H. Spencer, *Ethiopia, the Horn of Africa and US Policy*. Published by Institute for Foreign Policy Analysis (Cambridge, Massachusetts, September 1977), 27-30 ተመልከት።

ደግሞ ዕድሏን ከፈረንሳይ በጎ ፈቃድ እንድታቆራኝ አስገድዷታል። የአፄ ኃይለ ሥላሴ መንግስት አሜሪካ እና እንግሊዝ በጥር 1951 በጣምራ ይፋ ያደረጉትን የእንግሊዝ ሱማሌ እና የጣሊያን ሱማሌን አስቸኳይ ውህደት እቅድ (demarche) በብርቱ የተቃወመው ሲሆን ውጥኑ የታላቋ ሱማሌ መመስረትን ዕውን ያደርጋል ከሚል ፍራቻ በመነሳት የሁለቱንም መንግስታት እርምጃ አደገኛነት በአፅንኦት አሳስቧል።[37] በተመሳሳይ መንገድም ግብፅ እና የአረብ ሊግ የአምስቱን የሶማሌ ግዛቶች ውህደት [እንግሊዝ ሱማሌ፣ ጣሊያን ሱማሌ፣ ፈረንሳይ ሱማሌ፣ኦጋዴን እና ሰሜን ምሥራቅ ኬንያ (NFD, North Frontire District)] በመደገፍ ለተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ያቀረቡት ሐሳብም ለኢትዮጵያ አስደንጋጭ ነበር።[38]

በሰኔ 1952 (1 July 1960) የእንግሊዝ እና ጣሊያን ግዛቶችን በማጣመር ሶማሊያ ነፃ አገር ሆና ስትቋቋም ይህንኑ የግዛት ማስፋፋት ምኞት ቀዳሚ አጀንዳ በማድረግ መንቀሳቀስ ጀመረች። የታላቋ ሱማሌ መመስረት ህልም በህገ መንግስቷ አንቀጽ 6 ህጋዊ ዕውቅና የተሠጠው ከመሆኑም ባሻገር የአገሪቱ ሰንደቅ ዓላማ ባለ አምሥት ቅስት ኮከብ እንዲኖረው መደረጉም የዚሁ እሳቤ ይፋዊ መገለጫ ተደርጎ ተወሰደ።[39] ተከታታይ የሶማሊያ መሪዎችና የፖለቲካ ፓርቲዎችም የዚህን አጀንዳ ተግባራዊነት የህልውናቸው እና የሥልጣናቸው መሠረት አደረጉት። ይህም ከኬንያ እና በተለይም ከኢትዮጵያ ጋር ለቀጥተኛ ግጭት ሲዳርጋቸው በጅቡቲ የውስጥ ጉዳይም ጣልቃ እንዲገቡ በር ከፈተላቸው።

[38] ውጉሜ፡- ፈረንሳይ ሱማሌ 1 776፤ የኢትዮጵያ ኤምባሲ (ግብፅ) ለደልማ ደራሳ። ስለ ግብፅ እና አረብ ሊግ ማመልከቻ፡ መጋቢት 16፣ 1951

[39] ውጉሜ፡- ሱማሊ 12-D1፤ በኢትዮጵያና ሶማሊያ መካከል ስላለው ግንኙነት የተደረገ ጥናት ሪፖርት፡ ቀን የለውም። Said Yusuf Abdi, "Independence for the Afars and Issas: Complex Background: Uncertain Future," in *Africa Today*, Vol.24, No. 1 (Jan.-Mar. 1977), 61-67.





በ1955 መጨረሻ አካባቢ የተጀመረው በጅቡቲ የሶማሊያ መንግሥት ኦፊሴላዊ ጣልቃ ገብነት ዋነኛ መጠቀሚያ አድርጎ ይገለገልበት የነበረው ለዓላማው ማስፈፀሚያ የመሠረተውን "የፈረንሳይ ሶማሌ ነፃ አውጭ ግንባር" (Front de Liberation de la Cote des Somalis) ነበር። ግንባሩ ጅቡቲን ወደ አዲሲቷ ሶማሊያ ከመቀላቀል የበረታ ምኞት በመነጨም ለተከታታይ ዓመታት ጠንካራ እና በከፊል የተሳካ ትግል ማድረግ ቻለ። በተለይም የቅኝ ግዛቶችን ነፃ አወጣጥ ሂደት እንዲከታተል በተቋቋመው የአፍሪካ አንድነት ድርጅት የነፃ አውጭ ኮሚቴ ውስጥ በዚህ ግንባር ሽፋን በመጠቀም ሶማሊያ ያደረገችው እንቅስቃሴ የአብዛኛውን አባላት ድጋፍ አስገኝቶላታል። የጅቡቲ ግዛት እንደሚገባትም ለማሳመን ከጫፍ ደርሳ ነበር።[40]

የኢትዮጵያ ባለሥልጣናት ሴራውን ለመረዳት እና ለማክሸፍ የዘገዩ ቢሆንም በኋላ ባደረጉት ያላሰለሰ ጥረት የጅቡቲን ወደ ሶማሊያ መቀላቀል አስቀሩ። በዚህም ሂደት ትግሉን ከኢትዮጵያ ፍላጎቶች እና ብሔራዊ ጥቅሞች እንፃር ለመምራት እንዲያስችል የታሰበ "የጅቡቲ ነፃ አውጭ ንቅናቄ" (Le Mouvement de Liberation de Djibouti) የተሰኘ ተቀናቃኝ አንጃ በመስከረም 1957 አቋቋሙ። መቀመጫውን በድሬዳዋ (ከተወሰነ ጊዜ በኋላ በተጨማሪ በአሳይታ) ያደረገው ይህ ድርጅት ከመነሻው ደካማ የነበረ ቢሆንም በሶማሊያ የሚደገፈውን ግንባር ተሰሚነት ለመቀልበስ ተገቢውን ድርሻ ተወጥቷል። ዋነኛ ችግር የነበረው ግን የጅቡቲ ጉዳይ ከኢትዮጵያ ቁጥጥር ማፈትለኩና ግዛቱንም ወደራሷ የማጠቃለል ምኞቷም በሂደት መንጠፉ ነበር። የሶማሊያን የግዛት ይገባኛል ጥያቄ በብርቱ ለምትቃወመው ኢትዮጵያ ተመሳሳይ ጥያቄ ማንሳቱ አዋጭ አለመሆኑ በስፋት እየታመነበት መጣ። ጅቡቲን ለዘለቄታው የማጣቱ ሌላው እውነታ ከዚህ ይመነጫል።[41]

[40] ውጉሜ፡- ጅቡቲ 57-D3 1B፤ አብዱላሂ አርደዩ (የግንባሩ ዋና ፀሐፊ) ለአአድ ነፃ አውጭ ኮሚቴ፡ እ.ኤ.አ. 14 የካቲት 1964። ውጉሜ፡- ጅቡቲ 57-D3 1B እና አአድ 1963፤ አምባሳደር መንግስቱ ደስታ (በአአድ የነፃ አውጭ ኮሚቴ የኢትዮጵያ ልዑክ መሪ) ለክቡር ክተማ ይፍሩ (የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዴኤታ) - ስለ አአድ ነፃ አውጭ ኮሚቴ ስብሰባ ሪፖርት፡ ሰኔ 16፣ 1956

የወቅቱ ክስተቶች በጅቡቲ የፖለቲካ ህይወት ላይ የየራሳቸውን አሻራ ትተው አልፈዋል። ግዛቱ የውስጥ አስተዳደር መብት ባገኘ ማግሥት ወሳኙን የሥልጣን እርከን የተቆናጠጡት የኢሳ-ሱማሌ ተወላጆች የግብፅ ውጥን አቀንቃኞች መሆናቸውና ለታላቋ ሱማሌ ውጥን ዕውን መሆን ያሳዩት በጎ ፈቃድ የዚህ ዋነኛው መገለጫ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል። በተለይም ምክትል ፕሬዚደንቱ ማህሙድ ሐርቢ ይህንን ለማሳካት በመካከለኛው ምሥራቅ፣ በግብፅ እና በሱማሊያ ያደረጋቸው እንቅስቃሴዎች ለኢትዮጵያ ባለሥልጣናት አስደንጋጭ ነበሩ። ከሁሉም በላይ ከግብፁ መሪ ጋማል አብዱል ናስር ጋር መገናኘቱና ለዓላማው ማስፈፀሚያ የሞራል እና የገንዘብ ድጋፍ ማግኘቱ በተለየ ክትትል ውስጥ እንዲወድቅ አደረገው።[42]

በጅቡቲ ፖለቲካ ውስጥ እየታየ የመጣው የፓን-ሱማሌ/ ፓን-አረብ አመለካከት የፈረንሳይ መንግስትንም ያሳሰበ በመሆኑ ከኢትዮጵያ እሳቤ ጋር የተጣጣመ ፖሊሲ እንዲከተል ተገፋፋ። በሂደትም ሁለቱም መንግሥታት የደንከል (አፋር) ጎሳ የበላይነትን የሚያረጋግጥ መርህ በስፋት ወደማስፈፀሙ አዘነበሉ። ፈረንሳዮች ይህን ሲያደርጉ በግዛቱ ያላቸውን የበላይነት መብት በዘለቄታው ለማስጠበቅ በማሰብ ሲሆን ኢትዮጵያ ደግሞ የታላቁ ሱማሌን እቅድ ከማክሸፍ ባሻገር ፈረንሳይ ግዛቱን ለቃ በምትሄድበት ወቅት አሳልፋ ትሰጣኛለች ከሚል እሳቤ በመነሳትም ነበር። የሁለቱ አገራት ጥምረት እስከ መጨረሻው ቢዘልቅም ከየወቅቱ ነባራዊ ዕውነታ በመነሳት መሠረታዊ ለውጦችን አስተናግዷል።

በግዛቱ ኦፊሴላዊ ስያሜ ዙሪያ የተነሳው ውዝግብ እና ፍፃሜው የኢትዮጵያና ፈረንሳይን ጥምረት መሠረታዊ መርሆዎች ከሚያመለክቱ ክስተቶች መካከል በዋነኛነት ይጠቀሳል። ሐምሌ 1959 የተጠናቀቀውን ህዝበ ውሳኔ ተከትሎ ፈረንሳይ "የአፋርና ኢሳ ግዛት" የሚል መጠሪያ በህጋዊነት እንደምትጠቀም አስታወቀች። ምንም እንኳን ኢትዮጵያ ጅቡቲ የሚለውን ስም ብትመርጥም አዲሱ መጠሪያ የቀድሞውን "ፈረንሳይ ሱማሌ" የሚሽር በመሆኑ በፀጋ መቀበሏን ገለጸች። የሁለቱም ዓላማ የነበረው ሶማሊያን ከጅቡቲ ጉዳይ ማግለል ሲሆን በተለይ ኢትዮጵያ ከጉዳዩ ጋር በተያያዘ የሞቃዲሾው መንግሥት ለአፍሪካ አንድነት ድርጅት (አአድ) እና ለተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ያቀረበውን አቤቱታ ማክሸፍ ችላለች።[43]

ይህ ማለት ግን ፈረንሳዮች የራሳቸውን ጥቅም ለማስጠበቅ የተናጠል ጥረት አላደረጉም ማለት አይደለም። እንዳንድ ጊዜ የኢትዮጵያን ፍላጎት በቀጥታ በመፃረር ሲንቀሳቀሱ ይስተዋሉ ነበር። በተለይ በጅቡቲና በኢትዮጵያ የሚገኙትን አፋሮች በበላይነት የሚመሩትን ሱልጣን አሊሚራን ለመስበክ ያደርጉት የነበረው ጥረት ከኢትዮጵያ ባለሥልጣናት ጋር ለግጭት ከዳረጋቸው አጋጣሚዎች ይመደባል። ለምሳሌ በ1952 አጋማሽ አከባቢ የጅቡቲ ደንከል የፖለቲካ መሪዎችን ወደ ግለሰቡ ዘንድ በመላክ ከጅቡቲ ነፃነት በማግበር አፋሮችን በሙሉ ወደ አዲሱ አስተዳደር እንዲቀላቀሉ በስፋት ይሰብኩ ነበር። በተጨማሪም በኢትዮጵያ በሚገኙት የአፋርና ኢሳ ጎሳዎች መካከል በግጦሽና በውሃ ይዞታ ሳቢያ ግጭት እንዲነሳ በስውር መንቀሳቀሳቸው በመረጃ መታወቁ ሌላው አፍራሽ ድርጊት ነበር። ለፈረንሳዮች ማስጠንቀቂያ እንዲሆን በማለት የጎሳ ችግሩን ለመቅረፍ በሚል ሰበብ የኢትዮጵያ ወታደሮች ወደ ጅቡቲ እንዲገቡ ተደረገ።[44] እነኚህ አጋጣሚዎች ጅቡቲን በተመለከተ በፈረንሳይ በጎ ፈቃድ ላይ ሙሉ በሙሉ ላለመተማመን መንገድ ከፈቱ።

[41] ውጉሚ፡- ጅቡቲ 54-D3 16፤ በጅቡቲ ጉዳይ የተደረገ የከፍተኛ ባለሥልጣናት ምክክር ቃለ ጉባኤ፡ ነሐሴ 25፣ 1956

[42] ውጉሚ፡- ፈረንሳይ ሱማሌ 1 776፤ የኢትዮጵያ ኤምባሲ (ግብፅ) ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፡ ሚያዝያ 8፣ 1951። ውጉሚ፡- ፈረንሳይ ሱማሌ 1 776-2፤ ቆንስል ፍጡር አብርሃ (ታዒዝ-የመን) ለንጉሰ ነገሥቱ፡ ግንቦት 19፣ 1951፤ ፍጡር ለደይልማ ደሬሳ፡ ግንቦት 20፣ 1951





[43] ውጉሚ፡- ሱማሌ 20-D1፤ ውጉሚ ፈረንሳይ ሱማሌ 5 8-1B

[44] ውጉሚ፡- ፈረንሳይ ሱማሌ 1 776–2፤ ጅቡቲ ቆንስላ ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፡ ግንቦት 16፣1952፤ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ለጅቡቲ ቆንስላ፡ ሰኔ 29፣ 1952

# ምዕራፍ ፫

# የኢትዮጵያ ፖሊሲዎች ዳሰሳ

## 3.1. የአፄ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት

ሰኔ 1949 በጅቡቲ የተካሄደውን ምርጫ ተከትሎ ኢትዮጵያ በግዛቱ የወደፊት ሁኔታ ላይ የምትከተላቸውን የፖሊሲ አቅጣጫዎችን በስፋት መዳሰስ ጀመረች። ከውስጥ አስተዳደር መብቱ መሰጠት ጋር በተያያዘ ወደ ሥልጣን የመጣው የሐርቢ ወገን ያራምድ የነበረው አቋም በፍፁም ተቀባይነት አልነበረውም። በምርጫው ሂደት በአንፃራዊነት የተሻለ መርህ ይከተል የነበረውን የሐሰን ጉሌድና መሐመድ ካሚል ወገን በገንዘብ ለመደገፍ ጥረት አለመደረጉም ስህተት እንደነበር ከግንዛቤ የገባው ወዲያውኑ ነበር። በግዛቱ ሊቀለበስ የማይችል የታሪክ ዑደት ቢጀመርም ያለፈውን ስህተት ለማረም ያለመ የኢትዮጵያ ቀጥተኛ ጣልቃ ገብነት ተግባራዊ መሆን ጀመረ። ተሸናፊው ፓርቲ ለፈረንሳይ መንግስት ያቀረበውን የምርጫ መጭበርበር ክስ ተከትሎ የንጉሰ ነገስቱ መንግስት ለጉሌድ ጥረቶች መሳካት የገንዘብ ድጋፍ ከማድረግም ባሻገር በፓሪስ የሚገኘው አምባሳደር ምርጫው የሚሰረዝበትን መንገድ ፈረንሳዮች እንዲያጤኑ በተዘዋዋሪ ግፊት እንዲያደርግ ታዘዘ።[45]

በጊዜው ጥረቱ የተጠበቀውን ውጤት ባያስገኝም በተለዋጩ ግን አጋጣሚው በሐሰን ጉሌድ እና በኢትዮጵያ መካከል የጋራ ጥቅምን መሠረት ያደረገ ወዳጅነት ለመመስረት አስቻለ። ፈረንሳይ ሁሉንም ቅኝ ግዛቶቿን በተመለከተ በሐምሌ

[45] ውጉሚ፡- ፈረንሳይ ሱማሌ 1 776፤ ስለጉዳዩ በከፍተኛ ባለስልጣናት የተካሄደ የድርጊት መርሐ ግብር፡ መጋቢት 25፣ 1950፤ ጋሻው ዘለቀ (ውጉሚ ምክትል ሚኒስትር) ለአምባሳደር አካለወርቅ ሀብተወልድ (ፓሪስ)፡ ሚያዝያ 17፣ 1950፤ ቆንስል ምንዳ ለ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፡ ግንቦት 14፣ 1950





1950 እንዲደረግ የፈቀደችውን ባለ ሦስት አማራጭ ህዝበ ውሳኔ ተከትሎ በጅቡቲ የታዩ ለውጦች በኢትዮጵያና በጉሌድ መካከል የነበረውን ትስስር ይበልጥ አጠበቀ። አጠቃላይ ህዝበ ውሳኔው ቅኝ ግዛቶቹ ከፈረንሳይ ጋር በፌደሬሽን መዋሐድን፣ በሥራ ላይ ያለውን የውስጥ አስተዳደር መብት ማስቀጠል ወይንም እንደ አንድ አውራጃ መቆጠርን ይመርጡ እንደሆን ይጠይቅ ነበር። በዚህ መሐል ከፈረንሳይ እና በጉሌድ ከሚመራው ፓርቲ ፍላጎት በተቃራኒው ምክትል ፕሬዚደንቱ ሞሐመድ ሐርቢ አፋጣኝ ነፃነት እንዲሰጥ ማሳሰቡ የፖለቲካ ሞትን አስከተለበት።

በህዝበ ውሳኔው ማግስት በመስከረም 1951 በተደረገው የምክር ቤት ምርጫ የሐሰን ጉሌድ ፓርቲ (Parti de defense des Interits économiques et sociaux du territoire, D.I.E.S.T) ከሠላሳ ሁለቱ ወንበር ሃያ አምስቱን ማሸነፍ ሲችል የሐርቢ ወገን ሰባት አማካሪዎችን ብቻ ማስመረጥ ቻለ። የምርጫውን ሂደት በአንክሮ ሲከታተሉ እና አስፈላጊውን የገንዘብ ድጋፍ ሲሰጡ ለነበሩት የኢትዮጵያ ባለስልጣናት የተገኘው ውጤት ከበቂ በላይ ነበር። ላለፉት ሁለት ዓመታት ያህል የጅቡቲን የውስጥ ፖለቲካ ተቆጣጥረውት የነበሩ ኃይሎች ለዘለቄታው ተሰናብተው በምትካቸው የኢትዮጵያን ወዳጅነት የሚሹ ቡድኖች ወደ ስልጣን መጡ። በተከታታይ መሪዎች የነበሩት አህመድ ዲኒ እና አሊ አሬፍ (ደንከሎች) ምንም እንኳን ለጅቡቲ ነፃነትን የሚሹ ብሔረተኞች ቢሆኑም ከኢትዮጵያ ጋር በትብብር የመሥራት ፍላጎትም ነበራቸው። ይህንን በዘላቂነት ማስጠበቁና በሂደትም ወደ ኢትዮጵያ የመቀላቀሉን እሳቤ እንዲቀበሉ የማሳመኑ ሥራ ቀጣዩ የቤት ሥራ ተደርጎ ተወሰደ።[46]

[46] ውጉሚ፡- ፈረንሳይ ሱማሌ 1 776፤ ቆንስል ምንዳ ለይልማ ደሬሳ (ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር) - ስለ ምርጫው አጠቃላይ ሪፖርት፡ ህዳር 19፣ 1951። ውጉሚ፡- ፈረንሳይ ሱማሌ 1 776-2፤ ቆንስል ምንዳ ለውጉሚ - ሪፖርት በጅቡቲ የካቢኔ ምርጫ ዙርያ፡ ግንቦት ፲7፣1951

የዚህ አነስተኛ ጅምር ተከታይ የሆኑ የፖ.ሊ.ሲ. ውሳኔዎች አገሪቱ በጅቡቲ ጉዳይ ላይ የራሷን ጥቅም ለማራመድ የነበራትን ቁርጠኝነት የሚያመላክቱ ነበሩ:: የጅቡቲን የጎሳ ፖለቲካ በተዕዕኖ ሥር ማዋል ግዛቱን ወደ ኢትዮጵያ የመቀላቀሉ ምኞት ማስፈጸሚያ አንዱ ውጥን ነበር:: የጅቡቲ ሁለቱ ዋነኛ ጎሳዎች በዋነኝነት የሚገኙት በኢትዮጵያ የድንበር ክልል ውስጥ መሆኑ ለዚህ እቅድ መጠንሰስ አስተዋዕዖ አበርክቷል:: ስለዚህም ቋሚ ተቀማጭነቱ በድሬዳዋ የሆነውን የኢሳዎች ኡጋዝ (ንጉስ) በመጠቀም የጅቡቲ ወገኖቹ ወደ ኢትዮጵያ ያዘነበለ ፖለቲካ እንዲያራምዱ ጥረቶች መደረግ ጀመሩ:: በተመሳሳይም የደንከል ጎሳ አባላትን በመቀስቀስ ወደ እናት ሀገራቸው በፈቃዳቸው እንዲቀላቀሉ ይሰበኩ ነበር:: ይሁን እንጂ በጅቡቲ የሚገኙት ኢሳዎች በወቅቱ ከነበራቸው የሥልጣን ተጠቃሚነት በመነጨ፣ ደንከሎቹም የፖለቲካ ንቃተ ህሊናቸው የኢትዮጵያ ባለስልጣናት በፈለጉት መጠን ሊሆን ባለመቻሉ የእቅዱ ተፈፃሚነት አመርቂ አልሆነም:: ከዚህም የተነሳ ኢትዮጵያ ወሰብሰብ ያለና የረጅም ጊዜ ግብ ያለው ፖ.ሊ.ሲ. እንድትነድፍ ተገደደች::

ከነዚህ በተጨማሪ በህዳር 2፣ 1951 (12 November 1959) ኢትዮጵያ ከፈረንሳይ መንግስት ጋር ስለ ምድር ባቡር እና ነፃ የወደብ ተጠቃሚነት መብት የተፈራረመችው ስምምነት ጅቡቲን ላለማጣት ከተከናወኑ ጥረቶች በወሳኝነቱ ይጠቀሳል::[47] ስምምነቱ በጅቡቲ እያደገ የመጣውን የብሔረተኝነት ስሜት እና ነፃ የመሆን ፍላጎት ከግምት በማስገባት የተከናወነ ነበር:: በተለይም በኢትዮጵያ በኩል የነበረው ግንዛቤ እርግጥ እየሆነ የመጣውን የፈረንሳይ ከጅቡቲ መውጣት ተከትሎ ሊነሱ የሚችሉ የጥቅም ተቀናቃኝነት ጥያቄዎችን ከወዲሁ የመከላከል አስፈላጊነት ነው:: ሆኖም ስምምነቱ ግብዕና ሱማሊያን ጨምሮ ከሁሉም የጅቡቲ የፖለቲካ ፓርቲዎች ተቃውሞ አስከተለ:: በኢትዮጵያ በኩል ለዚህ ውል የተሰጠው ትኩረት አገሪቱ በግዛቱ ጉዳይ በቀጣይነት ለተከተለቻቸው የፖ.ሊ.ሲ. አቅጣጫዎች እንደመሠረታዊ አመላካች ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል::

[47] ስለ ወደቡ እና የባቡር መስመሩ ተከታይ ምዕራፎችን ተመልከት





በነሐሴ 1952 ስለ ጅቡቲ የተነደፈው ፖ.ሊ.ሲ. ከላይ የተዘረዘሩትን ተጨባጭ ዕውነታዎች ከግንዛቤ ያስገባ ነበር:: እንደ ጥናቱ አቀራረብ በግዛቱ ጉዳይ የኢትዮጵያ ዋነኛ አጀንዳ ጅቡቲ የታላቋ ሶማሊያ አካል እንዳትሆን መከላከል ሲሆን ይህንንም የመፈፀሚያው መንገድ በህዳር 1951 የተፈረመው የምድር ባቡር ውል እንደሆነ ያመለክታል:: ከሁሉም በላይ እነኚህ ጥቅሞች ሊጠበቁ የሚችሉት ጅቡቲ ነፃነቷን እስካላገኘች ድረስ ብቻ ስለመሆኑ ይከራከራል::

ነገር ግን ባለፉት ዓመታት በግዛቱ የተስተዋለ የብሔረተኝነት ስሜትና የነፃነት ፍላጎት እና በፍጥነት የሚለዋወጠውን የፈረንሳይን አቋም በመንተራስ ሂደቱ ሲገመገም ኢትዮጵያ ወደደችም ጠላች ጅቡቲ በቅርቡ ነፃ መውጣቷ አይቀሬ እንደነበር በአንክሮ ተስተውሏል:: የፖ.ሊ.ሲ. ጥናቱ በተለይም ኢትዮጵያ ቀደም ባሉ ወቅቶች ስትከተለው የነበረው ፈረንሳዮች ሲለቁ በጅቡቲ በሚገኙ 40,000 ደንከሎች (አፋሮች) አነሳሽነት ግዛቱ በፍላጎት ወደሷ ያዘነብላል የሚለውን ዕምነት በብርቱ ያጣጥላል:: ይልቁንም ጅቡቲ ወደ ታላቋ ሶማሊያ ህብረት መደባለቅን የሚፈልግበት ሰፊ ዕድል እንዳለ ያመላክታል:: ይህ ከሆነ ደግሞ በምድር ባቡር ውል ድርድር ሂደት በጅቡቲ ወደብ ለኢትዮጵያ የተሰጠውን ቀዳሚ የተጠቃሚነት መብት (preferential right) ነፃው የጅቡቲ መንግስት እንዲያጸድቅ የሚያስገድደው ነገር አይኖርም::[48]

የፖ.ሊ.ሲ. መመሪያው በተለይ ፈረንሳዮች በሁኔታዎች ተገደው ለጅቡቲ ነፃነት በሚሰጡበት ጊዜ ኢትዮጵያ የጥቁር ህዝብ ነፃነት ተቃዋሚ መስላ መታየት እንደሌለባት አበክሮ ያሳስባል:: ከላይ ከተዘረዘሩት ውስብስብ ችግሮችን ለመወጣት ኢትዮጵያ ልትከተላቸው የሚገቡ የተግባር አማራጮችንም ያስቀምጣል:: ከነዚህም መካከል ዋና ዋናዎቹ ሀ) በጅቡቲ ህዝብ የሚመርጣቸውን መሪዎች በጎ ፈቃድ መፈለግ፣ ከነርሱ የሚጠበቀውን የኢትዮጵያን ቀዳሚ የተጠቃሚነት መብት

[48] ውጉማ፡- ጅቡቲ 57-D3 1-A፤ ስለ ጅቡቲ የተዘጋጀ መመሪያ፡ ነሐሴ 11፣ 1952

ለዘለቄታው እንዲያስከብሩ ማድረግ እና የውጭ ፖለቲካቸው ወደ ሶማሌ ኅብረት እንዳያመራ የሚያስፈልጋቸውን የቁሳቁስና የሞራል እርዳታ ለማቅረብ የኢትዮጵያን ዝግጁነት ማስገንዘብ፤ ለ) ጎን ለጎን በግዛቱ ያለውን የደንከል (አፋር) "ማይኖሪቲ" ፓርቲ በማስጠር ማጠንከር፤ ሐ) ግዛቱ ነፃ በሚሆንበት ጊዜ ደግሞ የኢትዮጵያን ፍላጎት በግዛቱ የሚያሰርፁና የፖለቲካ አስተያየትን በተፅዕኖ ሥር ሊያውሉ የሚችሉ የንግድ ቤቶችን ማደራጀትና ለኢትዮጵያ ፕሮፓጋንዳ ማስረጫ እንዲሆኑ ማድረግ፤ መ) የኢትዮጵያ ቀዳሚ የተጠቃሚነት መብትና ማንኛውም የሃገሪቱ ጥቅም በተነካ ጊዜ በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ ያለውን የባቡር ሐዲድ አቅጣጫ ለመቀየር (divert) የሚቻል መሆኑን የጅቡቲ መሪዎች እንዲገነዘቡ ማድረግና ይህንንም ለማድረግ ጥናቱን ሶማሊያ ነፃነቷን ከማግኘቷ በፊት ማጠናቀቅ ወዘተ ናቸው።

ከዚህ የፖሊሲ ውሳኔ ማጠናቀቂያ የተቀመጠው ሐሳብ በወቅቱ የነበረውን አስቸጋሪ አከባቢያዊ የፖለቲካ ምህዳር ያንፀባርቃል። መመሪያው በተለይ ያሳሰበው በሃገሪቱ ባለሥልጣናት ዘንድ የሚታመነው በጅቡቲ ያለው የደንከል የቁጥር ሳይሆን የሥልጣን "ማይኖሪቲ" ወደ ኢትዮጵያ ይጠቅለል የሚለውን አመለካከት አደገኝነት ነው። ለዚህም የተሠጠው ምክንያት በሚገኙበት ግዛት ያልተደሰቱ ነዋሪ "ማይኖሪቲዎች" ጎሳቸው የፖለቲካ ሥልጣን የበላይ (majority) ወደሆነበት ክፍል ይጠቅለሉ የሚለውን ዕንሰ ሐሳብ መቀበል በግልባጩ ሲታይ ተመልሶ ኢትዮጵያ ስለ ኦጋዴን ያላትን የራሷን ክርክር የሚያፈርስ መሆኑ ነው። እንዲያውም ይህ ሐሳብ ፈረንሳዮች በስውር የሚገፋፉትን በኢትዮጵያ የሚገኙትን የአፋርና ኢሳ ጎሳዎችን የማጋጨት ዕቅድ ተግባራዊ ለማድረግ ስለሚያስችል በጥንቃቄ መታየት እንዳለበት በአንክሮ ያሳስባል።

ለአጠቃላይ ተልዕኮው አፈፃፀም ይረዳ ዘንድም ጠንካራ ቆንስል መመደብ እንደሚያስፈልግና የግዛቱን ጉዳይ በቀጣይነት መከታተል እንደሚገባ በቀረበው ሐሳብ መሠረትም በጅቡቲ ጉዳይ ላይ ወሳኝ ሚና የተጫወቱት ሻለቃ ደመቀ ረታና አቶ አሰፋ ገብረ ማርያም ተከታታይ ቆንስል ሆነው ተሾሙ።





የእንግሊዝና ጣሊያን ሱማሌዎች ተዋህደው በሰኔ 1952 ነፃነታቸውን ሲቀዳጁ በጅቡቲ ግዛትም በኩል የፖለቲካ ትኩሳቱ መፋፋም ጀመረ። የኢሳና ገደቡርሲ ጎሳዎች በስደት ቻይና የሚገኘውን የሞሐመድ ሐርቢን የቀደመ አቋም በመቀስቀስ ከታላቋ ሶማሊያ የመቀላቀል ፍላጎታቸውን ሲገልፁ ደንከሎች በተቃራኒው አፋጣኝ ነፃነትን አለበለዚያም ከኢትዮጵያ ጋር የመዋሃድ አጀንዳ ማራመድ ጀመሩ። በሂደትም የደንከል የጎሳ መሪዎችና ፖለቲከኞች በተደጋጋሚ ወደ አዲስ አበባ እንዲመጡ ተደርጎ ከንጉሰ ነገስቱና ከሌሎች ባለሥልጣናት በመገናኘት ፍላጎታቸውን እና ታማኝነታቸውን ገለፁ።[49]

በዚህ ሁሉ ውጥንቅጥ መሐል ግን ኢትዮጵያ ስለ ጅቡቲ የወደፊት ዕጣ ፈንታ መልስ የፈለገችው ከፈረንሳይ መንግስት ነበር። በአፍሪካ ቀንድ እየተካሄደ በነበረው ፈጣን ለውጥ ከኢትዮጵያ ባልተናነሰ አጣብቂኝ ውስጥ እየገቡ የመጡት ፈረንሳዮች በጅቡቲ ለገጠማቸው ፈተና የራሳቸውን አማራጭ መፈለጋቸው አልቀረም። የካቢኔው ምክትል ፕሬዚደንት አሊ አሬፍና ሴናተር ሐሰን ጉሌድ አፋጣኝ ነፃነት እንዲሰጣቸው በማሳሰብ ተደጋጋሚ ንግግር ሲያደርጉ በዝምታ መታለፋቸው ሳያንስ የፈረንሳይ ጠቅላይ ሚኒስትር ሙሴ ሚቼል ደብሬ (Michel Debre) እ.ኤ.አ. ነሐሴ 18፣ 1960 ለአሊ አሬፍ በላኩት ቴሌግራም መንግስታቸው ለጅቡቲ ተጨማሪ የውስጥ አስተዳደር መብት የመፍቀድ ዕቅድ እንዳለው ማሳወቁ ለኢትዮጵያ ይበልጥ አሳሳቢው ጉዳይ ሆነ።[50]

---

[49] ውጉሚ፡- ፈረንሳይ ሱማሌ 1 778፤ ቆንስል ሻለቃ ደመቀ ረታ (ጅቡቲ) ለጃንሆይ እና ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር - ስለ ጅቡቲ ጎሳዎች የፖለቲካ አቋም፡ መስከረም 12 እና 19፤ ጥቅምት 2 እና 3፣ 1953

[50] ውጉሚ፡- ፈረንሳይ ሱማሌ 1 778፤ ጠቅላይ ሚኒስትር ሚቼል ደብሬ ለምክትል ፕሬዚደንት አሊ አሬፍ፡ እ.ኤ.አ ነሐሴ 18፣ 1960

የሚቼል ቴሌግራም ይፋ እንደሆነ የኢትዮጵያ መንግስት መጀመሪያ ፓሪስ በሚገኘው አምባሳደሩ ቀጥሎም በጠቅላይ ሚኒስትር አክሊሉ በኩል ከፈረንሳይ መንግስት ማብራሪያ ጠየቀ። በሁለቱም ጊዜያት የተነሳው ዋነኛ ነጥብ ጀኔራል ቻርለስ ደጎል ለአፄ ኃይለ ሥላሴ የገቡት ፈረንሳይ ከጅቡቲ ለቃ አትወጣም ይህን ካደረገችም ግዛቱን ለኢትዮጵያ ብቻ ታስረክባለች የሚለው የተስፋ ቃል ነበር። ለዚህ ጥያቄ የፈረንሳይ መሪዎች ይፋዊ መልስ የቀደመ ቃላቸውን አለመሻራቸው ሲሆን የጠቅላይ ሚኒስትራቸው መልዕክት የጅቡቲ ሱማሌዎችን ጥያቄ ለማስታገስ ያለመ እንደነበር አስረድተዋል። ሆኖም በዚህ ያልረኩት አክሊሉ ሐብተወልድ በፓሪስ ከፈረንሳይ ባለሥልጣናት ጋር ባደረጉት ድርድር በጅቡቲ የወደፊት ዕጣ ፈንታ ተጨባጭ ዋስትና እንዲሰጣቸው አጥብቀው ተከራከሩ።

ኢትዮጵያ በህዳር 1951 ስለ ምድር ባቡር ጉዳይ አዲስ ስምምነት የተፈራረመችውና በጅቡቲ ወደብ ላይም ሆነ በባቡር መስመሩ ላይ ከፍ ያለ ገንዘብ ለማውጣት የወሰነችው ግዛቱ በፈረንሳይ ይዞታነት ይቀጥላል ከሚል ግንዛቤ በመነሳት እንደነበር ጸሐፊ ትእዛዝ አክሊሉ ገልፀዋል። በንግግራቸው ፍፃሜም የፈረንሳይ መንግስት እየሰጠ ካለው የተስፋ ቃል ባሻገር ከኢትዮጵያ ጋር በመቀናጀት ሊያከናውናቸው የሚገቡ አጀንዳዎችን በማቅረብ ተቀባይነት እንዲያገኙ አደረጉ።

እነዚህም ሀ) በፈረንሳይ ሱማሌ በቁጥር የሚበዙት ደንከሌዎች እንደሆኑ በማስመሰል ምርጫ በሚደረግበት ጊዜ በዚሁ መጠን በፓርላማው ውስጥ ተወካዮቻቸው እንዲበዙ ማድረግ፤ ለ) በጅቡቲ ያሉ ሱማሌዎችና በኢትዮጵያ መካከል ያለው ጥርጣሬና ያለመግባባት ተቀርፎ በኢኮኖሚና በፖለቲካ ጉዳዮች የሚቀራረቡበትና የሚስማሙበትን ዘዴ እየፈለጉ እንዲሠሩ አዲስ አበባ ላለው የፈረንሳይ አምባሳደር እና ለጅቡቲ ባለሥልጣኖች ትዕዛዝ እንዲሰጥ፤ ሐ) በጅቡቲ የሱማሌ ቁጥር **ይበዛል ለማሰኘት** ከቀድሞው የእንግሊዝ ሱማሌ ግዛት (ሰሜን ሱማሊያ) ሱማሊዎች ወደ ግዛቱ በብዛት እየገቡ በመሆኑ ይህ እንዲታገድ እንዲደረግ፤ መ) በጠቅላላው ስለ ታላቋ ሱማሊና ስለ ጅቡቲ ጉዳይ በፖለቲካውና በጸጥታው ዘርፍ ሁለቱ አገሮች ተባብረው መሥራት ስላለባቸው ይህ ትዕዛዝ ለሚመለከታቸው ሃላፊዎች እንዲሰጥ ወዘተ የጋራ ስምምነት ተደረሰ።





አክሊሉ ከፕሬዚደንት ደጎል ጋር ባደረጉት ንግግርም ስለ ጅቡቲ የፈረንሳይ ፖለቲካ የተቆረጠና ዘላቂ የሆነ አመራር ካልያዘ - ኢትዮጵያም ካላወቀችው - በየጊዜው ችግር የሚፈጥርና በኢኮኖሚም በኩል መዋዕለ ንዋይ ለማፍሰስ የሚያዳግት መሆኑን ገለፁላቸው። ፕሬዚደንቱም ታላቋ ሱማሊያ የሚለውን ሐሳብ ፈረንሳይ መቼም እንደማትቀበል ከማረጋገጣቸውም ባሻገር ሃገራቸው ጅቡቲን መቼም የማትለቅ መሆንዋን በድጋሚ አረጋገጡ። ይህ የፈረንሳይ ማረጋገጫ የኢትዮጵያ መንግስት በነሐሴ 1952 ያረቀቀውን የፖሊሲ መመሪያ ሙሉ በሙሉ ለመተግበር የሚያስችል መሠረት ጣለ።[51]

ከሰኔ 1955 ጀምሮ በጅቡቲ ጉዳይ ላይ ለንጉሡ ነገሥቱ የቀረቡ ተጨማሪ ማስታወሻዎች በአፍሪካ እየተስተዋለ ከመጣው የብሔረተኝነት ስሜት እና ፈረንሳይ ከገባችበት አጣብቂኝ አንፃር ኢትዮጵያ በግዛቱ ለምታራምደው የይገባኛል ጥያቄ አፋጣኝ እልባት ማበጃት እንደሚጠበቅባት ያሳስባሉ።[52] በተለይ ግንቦት 1955 የተፈረመው የአፍሪካ መሪዎች ቃል ኪዳን ኮሎኒያሊዝምን የሚቃወምና ቅኝ ገገርዎች ከአህጉሪቱ በአፋጣኝ

---

[51] ውጉሚ፡- ፈረንሳይ ሱማሌ 1 778፤ አምባሳደር አካለ ወርቅ ሐብተ ወልድ (ፓሪስ) ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፡ መስከረም 7፣ 1953፤ በጸሐፊ ትእዛዝ አክሊሉ ሐብተ ወልድ የፓሪስ ቆይታ ዙሪያ የቀረበ ሪፖርት፡ ጥቅምት 10፣ 1953

[52] ውጉሚ፡- ጅቡቲ 52-D3 17፤ ለግርማዊ ንጉሰ ነገስት የቀረበ ማስታወሻ፡ ሰኔ 12፣ 1955። ውጉሚ፡- ጅቡቲ 52-D3 18፤ ለግርማዊ ንጉሰ ነገስት የቀረበ ማስታወሻ፡ ሰኔ 22፣ 1955። ውጉሚ፡- ጅቡቲ 52-D3 17፤ ማስታወሻ በጅቡቲ ጉዳይ፡ መስከረም 8፣ 1956

እንዲለቁ የሚያስገድድ በመሆኑ ኢትዮጵያ ቀጥተኛ አቋም መያዝ ይጠበቅባታል። ኢትዮጵያ የአአድ ዋነኛ መስራችና አባል ከመሆኗም በላይ የመሪነት ኃላፊነትም ስለተጣለባት ጅቡቲን ነፃ ለማውጣት በሚደረጉት ንግግሮች በተለይም 24 አባላትን ባቀፈው የተመድ ነፃ አውጭ ኮሚቴ የግዛቱ ጉዳይ ቀረቦ ድምፅ በሚሰጥበት ጊዜ ኃላፊነቷን ለመወጣት ስትል ከአፍሪካውያን ጋር ለመሰለፍ እንደምትገደድ እነዚህ ማስታወሻዎች ይከራከራሉ።

በተጨማሪም በወቅቱ በአፍሪካ ከታየው ፖለቲካዊ ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ "የለውጥ ነፋስ" አንፃር በአቅኚነትም ሆነ በሞግዚትነት አህጉሩን ለማስተዳደር የረጅም ጊዜ ፕላን የነበራቸው የባዕድ መንግስታት ሀሳባቸውን እንዲለውጡ እየተገደዱ መሆኑን የጥናት ሪፖርቶቹ በዋቢነት ይጠቅሱ ነበር። ስለዚህም አልጀሪያን በጦርነት፣ የምዕራብ አፍሪካ ግዛቶቿን በፈቃድዋ የለቀቀችው ፈረንሳይ ስለ ጅቡቲ የተለየ ትግል ታደርጋለች ተብሎ እንደማይገመት ይከራከራሉ። ስለዚህም የቀረበው አመንክዮ ፈረንሳይ ከጅቡቲ ወደብ ታገኝ የነበረው ጥቅምና አገልግሎት ዘመን እየሻረው መሄዱን፣ የቴክኖሎጂና የጦር መሳሪያ መራቀቅ በየሥፍራው ይቋቋም የነበረውን ስትራቴጂካዊ የጦር ሠፈር አስፈላጊነት መቀነሱን እና በተጨማሪም የማዳጋስካርና የኢንዶቻይና ነፃ መውጣት ጅቡቲ ለፈረንሳይ መረጋገጫ እርካብ የመሆንዋን ዋጋ ማስቀረቱ ነው።[53]

ጅቡቲን ወደ ኢትዮጵያ የመቀላቀሉን ዓላማ ለማሳካት ያመች ዘንድ ማስታወሻዎቹ በአፋጣኝ መተግበር ይኖርባቸዋል በማለት ካሳሰቧቸው ነጥቦች መካከል ዋነኛው በንጉሡ ነገሥቱና በቻርለስ ደጎል መካከል ያለውን ወዳጅነት በመጠቀም የፈረንሳዩን መሪ የተስፋ ቃል በፅሑፍ የማስፈር አስፈላጊነትን ነበር። አፄ ኃይለ ሥላሴ በጥቅምት 1956 አሜሪካን ለመጎብኘት ሲሄዱ

[53] Daniel Bon and Karen Mingst, "French Intervention in Africa: Dependency or Decolonization," in *Africa Today*, Vol. 27, No. 2 (1980), ገ-20.





በፓሪስ በሚኖራቸው ቆይታ ጄኔራል ደጎልን በድጋሚ በማነጋገር አስፈላጊውን የፅሑፍ መረጃ ለማግኘት እንዲሞክሩ ተጠይቀው ነበር። እንዲሁም የኢትዮጵያ ተፅዕኖ በጅቡቲ በሰፊው እንዲሠርግ የግዛቱን አስተዳደር ድጋፍ ማግኘቱ አንገብጋቢ እንደሆነ በማስገንዘብ ለዚህም ዓላማ ከግብ መድረስ ይረዳ ዘንድ ለጅቡቲ አስተዳዳሪዎች ከፓሪስ የተብራራ ትእዛዝ እንዲደርሳቸው ንጉሠ ነገሥቱ እንዲሞክሩ ተጠየቁ።

በተጨማሪም ከጅቡቲ ቆንስላ የተላከውን ማሳሰቢያ በመንተራስ የጅቡቲ ጥናት ክፍል ያቀረበው ተጨማሪ ማስታወሻ ፈረንሳይ በፈቃዷም ይሁን ተገዳ ጅቡቲን ለቃ እስክትሄድ ግዛቱን ባለመፈለግ እሳቤ ለመቆየት የተገባው ቃል ጠቀሜታና ሊያስከትል የሚችለው ጉዳት በአፋጣኝ እንዲጤን አሳሰበ። ከፈረንሳይ የፅሑፍ ማረጋገጫ ማግኘቱም ይሁን የቀደመውን መግባባት መቀየሩ ያልተቻለ ቢሆንም የወቅቱ ሁኔታ ኢትዮጵያ የራሷን አማራጭ መከተልና ይህንንም በፍጥነት መተግበር እንደሚኖርባት በባለሥልጣናቱ ዘንድ በሰፊው እየታመነበት መጣ።

ከዚህ አንፃር የመጀመሪያው ሥራ ተደርጎ የተወሰደው እና የተተገበረው የጅቡቲን የፖለቲካ መሪዎች በአካል ማነጋገርና ስለ ወደፊት ዕቅዳቸው ግልፅ ውይይት ማድረግ ነበር። አብዛኛው የደንከል ተወካዮች እስከ ዘይላ ወደብ የሚደርሰው ክልል የነሱ ርስት መሆኑን ከመግለፅም ባሻገር ፍላጎታቸው በጅቡቲ ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ የመሪነቱን ሚና መጫወት እንደሚሹ ገለፁ። ኢትዮጵያም ይህንኑ ከመተግበርና የውስጥ አስተዳደር መብታቸውን ከማጠንከር አንፃር እንድታግዛቸው አሳሰቡ። በተለይ የደንከል የፖለቲካና የጎሳ መሪዎች የሆኑትን ኢብራሂም ሡልጣንን እና ሐሰን ሐንፍሬን ወደ አዲስ አበባ በመጥራት የተደረጉ የሐሳብ ልውውጦች (ምንም እንኳን በጅቡቲ አስተዳደር ከፍተኛ ተቃውሞ ቢያስከትልም) ከኢትዮጵያ ስትራቴጂ አንፃር ተጨባጭ ውጤት አስገኝተዋል። በተፃራሪው ለረጅም ጊዜ አቋሙ ነፃነት ይሁን ወይም ከሶማሊያ መቀላቀል ሊወስን ያልቻለውን ሴናተር ሐሰን ጉሌድን በመጥራትም በአፋጣኝ ከአንድ ምርጫ እንዲደርስ

በተጠየቀው መሠረት የወቅቱ ብቸኛ አማራጩ የጅቡቲ የውስጥ አስተዳደር መብት የተጠናከረ ሆኖ ግን በፈረንሳይ አስተዳደር ሥር ለመቀጠል እንደሚፈልግ አስታወቀ::[54]

ከፖለቲካ ፓርቲና ከጎሳ መሪዎቹ ከተገኘው መተማመኛ በተጨማሪ ግን የደንከሉን ወገን ነጥሎ በገንዘብና በሞራል የመደገፉ አማራጭ በስፋት ተግባራዊ ተደረገ:: እስከ ነሐሴ 1955 ድረስ የገንዘብ ድጋፉ በቆንስል አሰፋ እና በደንከል ተወካዮች ጣምራ ፊርማ ይከናወን ነበር:: በኋላ ግን የዚህ ድርጊት መታወቅ ሊያስከትል የሚችለውን ችግር ከግንዛቤ በማስገባት በጸሐፊ ትእዛዝ አክሊሉ መመሪያ ልገሳው በሦስተኛ ወገን በኩል በስውር እንዲከናወን ተወሰነ::[55]

በኢትዮጵያ የሚገኙ አፋሮችን ታሳቢ ያደረገ መሠረተ ልማት መዘርጋት፣ በቋንቋቸው የፕሮፓጋንዳ ቅስቀሳ ማድረግ እና የጅቡቲ ፖለቲከኞችን በስብከት ወጣቶቹን ደግሞ በትምህርት ዕድል ለመሳብ ለኢትዮጵያ ጥቅሞች ታማኝ የሆነ ክፍል መፍጠር ወዘተ በተጨማሪ ከታቀዱ የድርጊት መርሐ ግብሮች መካከል ይጠቀሳሉ:: ለዚህም ሲባል አፄ ኃይለ ሥላሴ በሐምሌ 1956 ለ20 ጅቡቲያውያን የነፃ ትምህርት ዕድል ፈቀዱ::[56]

ሌላው እንቅስቃሴ በጅቡቲ የደንከሎች የቁጥር የበላይነት እንዲረጋገጥና በቀጣይነት በሚደረጉ የጅቡቲ ምርጫዎች

---

[54] ውጉሚ:- ፈረንሳይ ሱማሌ 1 778፤ ሻለቃ ደመቀ ረታ ለጃንሆይና ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፡ ጥቅምት 3፣ 10፣ 16፣ 17፣ 24፣ 1953፤ አምባሳደር አካለ ወርቅ (ፓሪስ) ለጸሐፊ ትእዛዝ አክሊሉ ከሐሰን ጉሌድ ጋር ስላደረጉት ውይይት፡ ህዳር 16፣ 1953

[55] ውጉሚ:- ጅቡቲ 19-D1 21፤ ማስታወሻ ለቆንስል አሰፋ፡ ነሐሴ 14፣ 1955

[56] ውጉሚ:- ጅቡቲ 19-D1 5፤ ውጉሚ ለጅቡቲ ቆንስላ፡ ሐምሌ 21፣ 1956





አብላጫውን መቀመጫ እንዲያገኙ ይረዳ ዘንድ በኢትዮጵያ የሚገኙት የአፋር ጎሳ አባላት በብዛት ወደ ግዛቱ እንዲገቡ ማድረግ ነበር:: "ፕሮጀክት ኦሬንጅ" (project orange) ተብሎ የተሰየመው ይህ ፕላን ደንከሎችን በብዛት ወደ ጅቡቲ ማስረግ፣ በቋሚነት ማስፈር እና የከፊል አርሶ አደር ህይወት እንዲመሠርቱ ማድረግን ያካትታል:: ይህ በተለይ የሶማሊያ መንግሥት የኢሳና ሌሎች የሶማሌ ጎሳ አባላትን ከሰሜን ሶማሊያ (ሶማሊላንድ) ወደ ጅቡቲ በማስረግ የፖለቲካ ሂደቱን በራሱ በተፅዕኖ ስር ለማዋል የሚያደርገውን እንቅስቃሴ ለማክሸፍ ከማሰብ የመነጨ ነበር::[57]

የዚህ ጥረት ፍሬ በህዳር 11፣ 1956 በተጠናቀቀው የጅቡቲ ምክር ቤት አባላት ምርጫ በተግባር ታየ:: ኢትዮጵያ በገንዘብ የደገፈቻቸው የደንከል ፓርቲ አባላት በሙሉ ማሸነፍ የቻሉ ሲሆን 32 መቀመጫ ካለው ምክር ቤት 16ቱን ደንከሎች (አፋር) መቆጣጠራቸው ትልቅ ስኬት ተደርጎ ተወሰደ:: በተለይ በይበልጥ ትኩረት ተሠጥቶት የነበረው 'Parti de L'Union Democratique Afar" የተሠኘው ፓርቲ ሙሉ በሙሉ ውጤታማ መሆኑ ባለሥልጣናቱን አስደሰተ:: ከተቀረው መቀመጫ ኢሳዎች፣ ሐበሬወሎችና ገደቡርሲዎች በጥምረት አስራ አንዱን ሲያገኙ፤ ፈረንሳዮች አራት እና ዓረቦች አንድ ተወካይ ብቻ ማስመረጥ ቻሉ:: በዚህ አጠቃላይ ስኬት መካከል የአሊ አሬፍ በድጋሚ መመረጥ ለኢትዮጵያውያኑ ብዙም የሚያሳስብ አልነበረም::[58]

በምርጫው ሂደትም የኢትዮጵያ ባለሥልጣናት አብሮዋቸው ይሰሩ የነበሩት ሐሰን ሐንፈሬና ኢብራሂም ሡልጣን የተባሉ የደንከል ፖለቲከኞች ከተቃዋሚዎች በመሰለፋቸው (የመጀመሪያው በመሸነፉ አኩርፎ ሁለተኛው ሃሳቡን ቀይሮ)

---

[57] አምባሳደር ፍትጉ ታደሰ (በውጭ ጉዳይ የጅቡቲ ጥናት ቡድን አባል እና በጅቡቲ የኢትዮጵያ አምባሳደር):: Seyoum Haregot, 166.

[58] ውጉሚ:- ጅቡቲ 52-D3 26፤ በጅቡቲ የምክር ቤት ምርጫ ዙሪያ የቀረበ ሪፖርት፡ ህዳር 11፣ 1956:: ውጉሚ:- ጅቡቲ 52-D3 10፤ ቆንስል አሰፋ (ጅቡቲ) ለአቶ በፍቃዱ ታደሰ (ውጉሚ ረዳት ሚኒስትር)፡ ታህሣስ 16፣ 1956

የተከሰቱትንም ችግሮች በቸልታ ለማለፍ መርጠዋል። ሆኖም እነኚህ ግለሰቦች ደጃዝማች አሊ ሚራህና ፊታውራሪ ያዩ ከተባሉ የጎሳ መሪዎች ጋር በመሆን የታላቁ አፋል መንግሥትን ለማቋቋም መስማማታቸው እና በኢትዮጵያ፣ በጅቡቲና በኤርትራ የሚገኙትን የአፋር ተወላጆች በመሰበክ ይህንን ዓላማ ለማሳካት ካልሆነም ከሶማሊያ ጋር በፌደሬሽን ለመቀላቀል ፍላጎት ማሳየታቸው በቀላሉ የሚታለፍ አልነበረም። ጄነራል ደጎል መንግስታቸው ከጅቡቲ የመልቀቅ ሐሳብ እንደሌለው ለጸሐፊ ትእዛዝ አክሊሉ በድጋሚ ማረጋገጣቸው፤ በተጓዳኝ ደግሞ የታላቁ አፋል ሐሳብን ማራመድ መጀመራቸው መጪው ጊዜ ለኢትዮጵያ አዳጋች እንደሚሆን አመላካች ተደርጎ ተወሰደ።[59]

ከዚህ ጋር በተያያዘ ኢትዮጵያ ለምታራምደው የይገባኛል ጥያቄ ተጨማሪ አደጋ እየፈጠረ የመጣው የተ.መ.ድ. ውሳኔ ቁጥር 1514 XX ነበር። ውሳኔው ነፃነታቸውን ያላገኙ አገሮች ሁሉ በፍጥነት ነፃ እንዲወጡ የሚያሳስብ ሲሆን በተለይ አፈፃፀሙን እንዲከታተል የተቋቋመው 24 አባላት ያሉት ኮሚቴ ባቀረበው የአተገባበር ማሳሰቢያ መሠረት ነፃነታቸውን ያላገኙት አገራት ህዝበ ውሳኔ (plebiscite) በማድረግ ከሚፈልጉት መንግሥት ጋር ሊቀላቀሉ ይችላሉ ማለቱ ወትሮውንም አስቸጋሪ የነበረውን ጉዳይ ይበልጥ አወሳሰበው። የጅቡቲ ጉዳይ በጥር ወር 1956 ለጠቅላላ ጉባኤው ስብሰባ ለውይይት እንዲቀርብ መወሰኑ በኢትዮጵያ በኩል አፋጣኝ ውሳኔን የሚሻ ሆነ።

ከዚህ ቀደም አገሪቱ ስለ ጅቡቲ የምትከተለው በዝግታ ላይ የተመሠረተ ያለመገፋፋት ወይም በይፋ ለመከራከር

[59] ዝኒ ከማሁ፤ ማስታወሻ ለጸሐፊ ትእዛዝ አክሊሉ ሐብተ ወልድ፡ ታህሣስ 25፣ 1956። ውጉሚ፦ ጅቡቲ 52-D3 6፤ ለክተማ ይፍሩ (ውጉሚ ደኤታ) የቀረበ ማስታወሻ፡ ሰኔ 20፣ 1956። ውጉሚ፦ ጅቡቲ ልዩ ልዩ ፋይሎች 1 3፤ በ"ብሎክ አፋል" ዙሪያ የቀረበ ማስታወሻ፡ የካቲት 9፣ 1957። ውጉሚ፦ ጅቡቲ ሪፖርት 10 824-2፤ በፈረንሳይ የብሎክ አፋር ፖሊሲና እንቅስቃሴ ዙሪያ የቀረበ ሪፖርት፡ ሰኔ 8፣ 1958





ያለመሞከር አካሄድ እና የፈረንሳይ መንግሥት አወቃም ይሁን ተገዶ ግዛቱን ሲለቅ ኢትዮጵያ በቦታው ትተካለች የሚለው ፖሊሲ ጊዜው እንዳለፈበት በስፋት ታመነበት። ይልቁንም አገሪቱ ስለ ጅቡቲ ያላትን የባለቤትነት ጥያቄ ለአፍሪካም ሆነ ለመላው ዓለም በግልፅ ማሳወቅ እንዳለባት ከግንዛቤ ተደረሰ። በተ.መ.ድ. ስለ ግዛቱ የወደፊት ዕጣ ፈንታ የማይቀረው ንግግር ሲደረግ በደፈናው የይገባኛል ጥያቄ ማንሳቱ ፋይዳ ቢስ መሆኑ ግልፅ ነበር። ይልቁንም የግዛቱን ጎሳዎች በኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጥቅሞች የመሳቡ አቀባጫ ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባ ተገመተ። አሁንም ቢሆን ግን ይህንን ለማሳካት የፈረንሳይ በጎ ፈቃድና ተባባሪነት እጅግ አስፈላጊ እንደሆነ በጉዳዩ ላይ የተደረጉ ንግግሮችና ውሳኔዎች ያመለክታሉ።[60] በኢትዮጵያ በኩል ለታየው መነሳሳት አንዱ ምክንያት የሶማሊያ መንግሥት የግዛት ማስፋፋት አጀንዳውን በጥልቀት ማራመዱና በሂደቱም ያገኛቸው አንፃራዊ ስኬቶች ናቸው።

የአ.አ.ድ. የነፃ አውጭ ኮሚቴ በጅቡቲ ጉዳይ ያደረጋቸው ተከታታይ ስብሰባዎች፤ የሶማሊያ መንግሥት ስለ ጅቡቲ ነፃነት ያቀረባቸው መከራከሪያዎችና ለዚሁ እንዲያግዘው ባቋቋመው የጅቡቲ ነፃ አውጭ ግንባር አማካኝነት የኮሚቴ አባላቱን አስተሳሰብ በተዕዕኖ ሥር ማዋሉ እና የነፃ አውጭ ኮሚቴው በኢትዮጵያ፣ ሶማሊያና ጅቡቲ በአካል በመገኘት ችግሩን ለማጤን መወሰኑ በኢትዮጵያ በኩል ሌላ የፖሊሲ ውዝግብ አስነሳ። ይህን ተከትሎ ንጉሠ ነገሥቱ በፈረንሳይ መንግሥት ላይ ከነበራቸው ዕምነት በመነሳት የአ.አ.ድ. ነፃ አውጭ ኮሚቴን ወደ ኢትዮጵያ መምጣት ተቃወሙ። ቆንስል አሰፋን ጨምሮ አብዛኛው የውጭ ጉዳይ ሰዎች ግን ባልተጨበጠ ተስፋ ላይ በመንተራስ ኮሚቴውን አለመቀበል ትልቅ ጥፋት እንደሚያስከትል ተከራከሩ። ይልቁንስ

[60] ውጉሚ፦ ጅቡቲ 52-D3 17፤ በጅቡቲ ጉዳይ ለጃንሆይ የቀረበ የውሳኔ ሐሳብ፡ ጥር 1956። ውጉሚ፦ ጅቡቲ 57-D3 5፤ አምባሳደር ተስፋዬ ገብረ እግዚእ (በተመድ ባለ ሙሉ ሥልጣን መልዕክተኛ) ለዮዲት እምሩ (ውጉሚ ረዳት ሚኒስትር)፡ ግንቦት 19፣ 1956

ኢትዮጵያም እንደ ሶማሊያ ያለ የራሷን ፍላጎት ሊያስፈፅም የሚችል እና ለሚመጣው ኮሚቴ ይህንን በአግባቡ የሚያስረዳ አንድ የጅቡቲ ነፃ አውጭ ግንባር መመሥረት እንዳለባት በአንክሮ አሳሰቡ::[61]

በንጉሡ ትትንችነት ስለ ጉዳዩ ለፈረንሳይ መንግስት የቀረበው የድጋፍ ጥያቄ ፈረንሳይ በማንኛውም መንገድ ለአፍሪካው ኮሚቴ ዕውቅና እንደማትሰጥና እንደማታስተናግደው በማሳወቋ ከሸፈ:: ይህንንም ተከትሎ በጅቡቲ ጉዳይ ላይ ኢትዮጵያ ስትከተለው የነበረው ፖሊሲ የተሳሳተ እንደነበር በሁሉም ዘንድ ግንዛቤ ተፈጠረ:: በአስቸኳይም ከደንከሎችና ኢሳዎች የተውጣጣ የጅቡቲ ነፃ አውጭ ግንባር በድሬዳዋ እንዲቋቋም እና ለአ.አ.ድ. ነፃ አውጭ ኮሚቴ ልዑካን አቀባበል ዝግጅት እንዲጀመር ተወሰነ:: ደንከሎችን ለማስደሰት በማሰብም በኢትዮጵያ የሚገኘው የአውሳ አውራጃ ግዛት መቀመጫ ከባቲ ወደ አሳይታ እንዲዛወር ተደረገ::

በጅቡቲ ድንበር አከባቢ የሚከናወኑ የመሠረተ ልማት ግንባታዎችን በተመለከተ ከአሳይታ እስከ አፋምቦ ያለውን መንገድ እንዲሠራ በመከላከያ ሚኒስቴር ለምድር ጦር መሐንዲሶች ቡድን፤ የሥራና መገናኛ ሚኒስቴር የውሃ ጉድጓዶችን እንዲቆፍር፤ ትምህርት ሚኒስቴር ትምህርት ቤቶችን ለመገንባትና የአስር ደንከሌዎችንና አስር ኢሳዎችን ነፃ የትምህርት ዕድል እንዲያስፈፅም፤ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር አሥር ክሊኒኮችንና አንድ ጤና ጣቢያ እንዲገነባ፤ የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በጅቡቲ ከተማ አንድ የንግድ ማህበር እንዲያቋቁም ወዘተ ኃላፊነት ተሰጣቸው::[62] እንደሚገመተውም እነዚህ ውሳኔዎች ፈረንሳይን አላስደሰቱም::

በፈረንሳይ መንግሥት አቋም ላይ ያደረው ቀየሚታ የጅቡቲ ገገርዎች ከኢትዮጵያ ወደ ግዛቱ የሚገቡ ሁሉ የፈቃድ ወረቀት እንዲኖራቸው በመደንገጋቸው ይበልጥ

[61] Belete Belachew, *Black Ethiopia: a Glimpse into African Diplomacy.* (Tsehai Publishers: Los Angeles, 2014), pp. 122-124.





ተባባሰ:: የኢትዮጵያን ፖሊሲ ከማስፈፀምም አንፃር ብርቱ እንቅስቃሴ ሲያደርጉ የቆዩት ቆንስል አሰፋ ገብረ ምርያም ከሥልጣን እንዲነሱ መጠየቃቸውም ሌላው እየተበላሸ ለመጣው የሁለትዮሽ ግንኙነት አመላካች ሆነ:: የኢትዮጵያ መንግሥት ይህንኑ በማስመልከት ፓሪስ በሚገኘው አምባሳደሩ በኩል ያቀረበው አቤቱታ በእምቢታ መጠናቀቁን ተከትሎ ኢትዮጵያም ቆንስሏን ላለማንሳት ወሰነች::[63] ከፈረንሳይ ፈቃድና ዕውቅና ውጭ ኢትዮጵያ የጅቡቲ ነፃ አውጭ ንቅናቄን በሐምሌ 1957 ያቋቋመች ሲሆን በኤርትራ፣ በኢትዮጵያ እና በጅቡቲ ያሉ የደንከል ባላባቶችን በማማከር እና የኢሳ ጎሳ መሪዎችን በመያዝ የተ.መ.ድ. እና የአ.አ.ድ. የነፃ አውጭ ኮሚቴዎች ጉብኝትን ተከትሎ አፍጥጠው የመጡ አደጋዎችን በጊዜያዊነት መቀልበስ ተቻለ:: እነኚህ ጥረቶች በተለይ የሶማሊያን የይገባኛል ትግል ከማክሸፍ አንፃር ተጨባጭ ውጤት አስገኝተዋል::[64]

ነገር ግን ችግሩን ለመቅረፍ የተነደፈው እና የተተገበረው የኢትዮጵያ አካሄድ ከህጸፅ የፀዳ ነበር ማለት አይቻልም:: ኢትዮጵያ ለተ.መ.ድ. ኮሚቴ ለምታቀርበው ማስታወሻ ዝግጅት በሚደረግበት ወቅት በተለይ በአ.አ.ድ. ነፃ አውጭ ኮሚቴ ስብሰባዎች ላይ ከተስተዋለው የፖሊሲ አለመጣጣም በመነሳት አፋጣኝ ማሻሻያ ማድረግ እንደሚያስፈልግ ታመነበት::

[62] ውጉማ፡- ጅቡቲ 57-D3 1-B፤ በከፍተኛ ደረጃ የተደረገ የባለሥልጣናት ውይይት እና ውሳኔ ሪፖርት፡ ነሐሴ 7፣ 1956:: ውጉማ፡- ጅቡቲ 57-D3 5፤ ስለ ድሬዳዋው የጅቡቲ ነፃ አውጭ ግንባር አመሠራረት ለከተማ ይፍሩ የቀረበ ማስታወሻ፡ ነሐሴ 7፣ 1956፤ሻለቃ ደመቀ ረታ (ውጉማ. የጅቡቲ ጥናት ክፍል) ለከተማ ይፍሩ፡ ህዳር 8፣ 1957፤ ስለ አአድ ነፃ አውጭ ኮሚቴ ጉብኝት፡ ነሐሴ 30፣ 1956፤ መስከረም 7-21 እና ከጥቅምት 5-30፣1957 ያሉትን ሪፖርቶች ተመልከት:: ውጉማ፡- ጅቡቲ 55-D3 ጥራዝ 3፤ በጅቡቲ ጠረፍ ስለሚከናወኑ የመሠረተ ልማት ሥራዎች፡ ህዳር 12፣ 1957፤ ታህሣስ 13፣ 1957

[63] ውጉማ፡- ጅቡቲ 55-D3 ጥራዝ 3፤ አምባሳደር ብ. ጀነራል መኮንን ደነቀ (ፓሪስ) ለጸሐፊ ትእዛዝ አክሊሉ፡ ህዳር 9፣ 1957፤ አምባሳደር መኮንን ደነቀ ለከተማ ይፍሩ፡ታህሣስ 13፣ 1957

የጅቡቲ ነፃ አውጭ ንቅናቄ ይመራበት የነበረው ግዛቱ ነፃ እንዲወጣና ከኢትዮጵያ ጋር እንዲቀላቀል የሚለው አቋም በአ.አ.ድ. ኮሚቴ ተቀባይነት አለማግኘቱ ለፖሊሲ ማሻሻያው አስፈላጊነት ዋነኛው ምክንያት ተደርጎ ቀረበ። የአፍሪካውያኑ እና የአንዳንድ ኢትዮጵያውያን ዲፕሎማቶች መከራከሪያ የነበረው ንቅናቄው በኢትዮጵያ የተቋቋመና የሚመራ እንጂ በጅቡቲ ሕዝብ ሃሳብና ፍላጎት ላይ የተመሠረተ አለመሆኑ ነው። ይህም በንቅናቄው ተአማኒነት ዙርያ ጥርጣሬ ከማስነሳቱም በላይ የኢትዮጵያ መንግሥት የድንበር ማስፋፋት ዓላማ ያለው ስለሚያስመስል መቀላቀል የሚለው ሃሳብ ለጊዜው እንዲቀር ተመከረበት። ሁለተኛው መከራከሪያ ነጥብ በጎሳ መመሳሰል ላይ የተመሠረተው ጅቡቲን የማስመለስ ጥያቄ በአጋዴን ሶማሌዎች ዙርያ ካለው ውዝግብ አንፃር ለኢትዮጵያ የማያዋጣ መሆኑ ነው።

ሦስተኛውና ዋናው ነጥብ ግን ኢትዮጵያ ከፈረንሳይ መንግስት ጋር ያለት ቁርኝትና ይህ በጅቡቲ ጉዳይ ላይ ያስከተለው መወሳሰብ ነው። የጅቡቲ ነፃ አውጭ ንቅናቄ በአ.አ.ድ. ነፃ አውጭ ንዑስ ኮሚቴ ፊት ቀርቦ ባደረጋቸው ማብራሪያዎች ሁሉ በፈረንሳይ ላይ ምንም ዓይነት የተቃውሞ ስሜት አለማንፀባረቁ በአፍሪካውያኑ ዘንድ ትዝብትን አሳድሮ ነበር። በተለይ ነፃነትን ይፈልጉ እንደሆነ ለቀረበላቸው ጥያቄ የንቅናቄው መሪ አህመድ ቡርሃን እንዲሰጡ የተመከሩት "አዎ ነፃነት እንፈልጋለን፣ ነገር ግን የኢኮኖሚያችን ዋስትናም እንዲረጋገጥልን እንፈልጋለን" የሚለው አካሄድ ደካማነታቸውን እና ጥገኝነታቸውን አጉልቶ አሳየ። በዚህ መንገድ መቀጠሉ የሚያስከትለውን አደጋ የተገነዘቡት የኢትዮጵያ ዲፕሎማቶች አፋጣኝ የፖሊሲ ማሻሻያ ይደረግ ዘንድ መወትወቱን ገፉበት። የኢትዮጵያን እና የፈረንሳይን ግንኙነት የሚነካ ቢሆንም እንኳን ንቅናቄው ለወደፊቱ የፈረንሳይ ቅኝ ገገርነትን ተቃዋሚነቱን የሚገልፅበት መንገድ መቀየስ እንዳለበት ተመከረ።[65]

ከዚህ ጋር በተያያዘ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ አቶ ከተማ ይፍሩ ሰኔ 1፣ 1958 ስለ ጅቡቲ ጠቅላላ ሁኔታ በኒውዮርክ ለተ.መ.ድ. የቅኝ ግዛት አስወጋጅ ኮሚቴ የሰጡት ማብራሪያ ኢትዮጵያ በግዛቱ ላይ ያላትን የማይናወፅ የባለቤትነት ጥያቄ ያንፀባረቀ ነበር። በደምሳሳው የአውሮፓውያንን ቅኝ ገገርነትን የኮነነው ማብራሪያ የፈረንሳይ በጅቡቲ መገኘት ኢትዮጵያን የጎዳ እና ከታሪካዊ የግዛት ድንበሯ የለየ መሆኑን መረጃ በመጥቀስ ይተነትናል። ይልቁንም ፈረንሳዮች ከመምጣታቸው በፊት ጅቡቲ የኢትዮጵያ ሉዓላዊ ክልል እንደነበረ፣ የግዛቱ መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ ከታላቁ የስምጥ ሸለቆና ከአዋሽ ተፋሰስ ጋር የተቆራኘ መሆኑ የኢትዮጵያ አካል መሆኑን እንደሚያመላክት፣ ከኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ዕውነታ አንፃር ጅቡቲ በኢትየጵያ ላይ ጥገኛ መሆኑን እና ከዘመናዊው ዓለም የንግድ ግንኙነት መርህ አኳያም የኢትዮጵያን ምሥራቃዊ፣ መካከለኛና ደቡባዊ ክፍል ከተቀረው ዓለም የሚያስተሳስረው ዋነኛ ወደብ መገኛ መሆኑ ወዘተ ለሃገሪቱ የግዛት አለኝታ ጥያቄ እንደ መከራከሪያ ሆነው የቀረቡ ምክንያቶች ነበሩ።[66]

[64] ውጉሚ፦ ጅቡቲ 56-D3 1፤ የጅቡቲ ነፃ አውጭ ንቅናቄን ለማቋቋም ሲባል ለደንከል የጎሳ መሪዎች የተደረገ የገንዘብ ልገሳ፡ ሚያዝያ 28፣ 1957፤ የጅቡቲ ነፃ አውጭ ንቅናቄን ስለማቋቋም፡ ሐምሌ 9 እና 10፣ 1957። ውጉሚ፦ ጅቡቲ 52-D3 26፤ የጅቡቲ ነፃ አውጭ ንቅናቄን ስለማቋቋም የቀረበ ፕላን፡ ግንቦት 18፣ 1957። ውጉሚ፦ ጅቡቲ 51-D3 4፤ ስለ ተመድ ነፃ አውጭ ኮሚቴ ልዑካን አቀባበል፡ ሰኔ 4፣ 1957። ውጉሚ፦ ሶማሌ 15-D1 1፤ የሶማሊያን ውጥን ስለማክሸፍ፡ ሰኔ 9፣ 1957። ውጉሚ፦ ጅቡቲ ሪፖርት 10 824-1፤ የአፋር ባላባቶችን ስለማሳመን፡ ሰኔ 19፣ 1957። ውጉሚ፦ ጅቡቲ 56-D3 8፤ በተመድ ኮሚቴ ጉብኝት ዙሪያ የቀረበ ሪፖርት፡ ሰኔ 3፣ 1958። Belete, p. 124-125.

[65] ውጉሚ፦ ጅቡቲ 52-D3 26፤ በጅቡቲ ነፃ አውጭ ንቅናቄ ዙርያ የፖሊሲ ወረቀት፡ ግንቦት 18፣ 1957

[66] ውጉሚ፦ ጅቡቲ 57-D3 8፤ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ከተማ ይፍሩ ንግግር፡ ሰኔ 1፣ 1958

ጄነራል ቻርለስ ደጎል በነሐሴ 1958 ጅቡቲና ኢትዮጵያን በጎበኙበት ወቅት የተከሰቱት ኩነቶች ይህንን ሁሉ ውዥንብር ይፋ አወጡ። የግዛቱንም መፃኢ ዕድል ለዘለቄታው የወሰነ ክስተት ፈጠሩ። የፕሬዚደንቱ ጉብኝት ይፋ ከሆነበት ከሐምሌ 1958 ጀምሮ በሁለት ጎራ በመከፈል የኢሳው ወገን ለግዛቱ በአፋጣኝ ነፃነት እንዲሰጥ ሲጠይቅ ደንከሉ ደግሞ በአሊ አሬፍ የሚመራውን የውስጥ አስተዳደር በመደገፍ አሁን ያለው ሥርዓት ለተወሰነ ጊዜ እንዲቀጥል መወትወት ጀመረ። የነዚህ ህዝባዊ ጥቅናቄዎች መጀመር ከግዛቱ መፃኢ ዕድል አንፃር ለኢትዮጵያ ባለስልጣናት አሳሳቢ ሆነ። ሆኖም ከቆንስላው ጽ/ቤት የጅቡቲ የፖለቲካ ፓርቲዎችን በገንዘብ ኃይል በመደለል በደጎል ጉብኝት ወቅት የኢትዮጵያን ፍላጎት በሚያንፀባርቅ መልኩ እንዲንቀሳቀሱ ለማድረግ የቀረበው ሃሳብ ተቀባይነት አላገኘም።[67]

ፕሬዚደንት ደጎል ጅቡቲ ሲደርሱ የገጠማቸው ህዝባዊ ተቃውሞና የነፃነት ጥያቄ ኢትዮጵያን ጨምሮ ሁሉንም ያስደነገጠ ነበር። በኢሳዎች መሪነት የተቀነባበረው ሠልፍ ከቁጥጥር ውጭ በመሆኑ የህይወት መጥፋት እና ከፍተኛ የንብረት ውድመት አስከተለ። ፖለቲካዊ ትኩሳቱ ያሳሰባቸው የፈረንሳዩ መሪና የጅቡቲ ገዥ ለተሰበሰበው ህዝብ የጠየቀው ነፃነት በአፋጣኝ እንደሚፈፀምለት ቃል መግባታቸው ሌላ የታሪክ ምዕራፍ ከፈተ። ቀጥሎም ጄነራል ደጎል በተገኙበት

[67] ውጉሚ፡- ጅቡቲ ሪፖርት 10 825፤ ቆንስል ቀኛዝማች አስፋው ሀብተ ማርያም (ጅቡቲ) ለከተማ ይፍሩ፤ ዶ/ር ተስፋዬ ገብረግዚ (ውጉሚ ደኤታ) ለቆንስል ቀኛዝማች አስፋው፡ ሐምሌ 18 እና 25፣ 1958፤ ቆንስል ቀኛዝማች አስፋው ለውጉሚ፡ ነሐሴ 17፣ 1958፤ በጄነራል ደጎል የጅቡቲ ጉብኝት ወቅት ስለተከሰተው ረብሽ ሪፖርት፡ ጳጉሜ 4፣ 1958. I.M. Lewis and Harold G. Marcus, "After the Referendum: Prospects in the Horn", Africa Report (April 1967), 37-41. I.M. Lewis, "The Referendum in French Somaliland", *The World Today* (July 1967), 308-314. Shehim and Searing, 214-214.





የፈረንሳይ የሚኒስትሮች ምክር ቤት መስከረም 11፣ 1959 ባደረገው ስብሰባ የጅቡቲ ህዝብ እ.ኤ.አ. ከሐምሌ 1፣ 1967 በፊት በሪፈረንደም የሚስማማውን አስተዳደር ይመርጥ ዘንድ ውሳኔ አስተላለፈ። በስተመጨረሻም ህዝበ-ውሳኔው መጋቢት 10፣ 1959 እንዲደረግ ቀን ቀጠሮ ተያዘለት። ይህንንም ተከትሎ ፀረ-ኢትዮጵያ እንቅስቃሴዎች በጅቡቲ እና በተለይም በሶማሊያ ተበራከቱ።



የጅቡቲ ህዝብ ነፃነት ለመጠየቅ ካደረጋቸው ሰልፎች አንዱ[68]

[68] "New Trouble for French Colony on Red Sea", *MERIP Reports*, No. 45 (March 1976), 23.



የጅቡቲ ህዝብ ነፃነት ለመጠየቅ ካደረጋቸው ሰልፎች አንዱ[68]

ክስተቱ የንጉሰ ነገስቱ መንግስት የሚኒስትሮች ምክር ቤት አገሪቱ ጅቡቲን በተመለከተ ስለምትከተለው ፖሊሲ የተብራራ የውሳኔ መግለጫ እንዲሰጥ አስገደደ:: አንደኛው የውሳኔው ፍሬ ነገር ኢትዮጵያ በጅቡቲ ጉዳይ ትክክለኛ የሆነ የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መርህ (self determination) የማትቃወም መሆንዋን ማሳወቅ ነበር:: ሁለተኛው ነጥብ ደግሞ ጅቡቲ በኢኮኖሚ፣ በሶሻል፣ በፖለቲካና በተለይም በእስትራቴጂ (በጂኦግራፊ አቀማመጥ) ከኢትዮጵያ ጋር የተሳሰረና ያለ ኢትዮጵያ ለመኖር የማይችል እንዲሁም ለሃገሪቱ ዋነኛው የመከላከያ በር ስለሆነ የግዛቱ የወደፊት ዕድል በሰልፍ ዲተርሚኔሽንም ሆነ በሌላ ረገድ ሲወሰን እነኚህን ዕውነታዎች መሠረት ማድረግ እንዳለበት ያሳስባል:: ይህንን መሠረት የማያደርግ ማንኛውንም ውሳኔ ግን ኢትዮጵያ በምንም አኳኋን የማትቀበል መሆኗን በማያወላውል ሁኔታ ገለፀ::

በወቅቱ በተ.መ.ድ. ለኢትዮጵያ ቋሚ መልዕክተኛ ለልጅ እንዳልካቸው መኮንን የተላለፈው መመሪያ በጥቅሉ የጅቡቲን የራስን ዕድዕ በራሰ የመወሰን መብት ሳይቃወሙ ከላይ የተመለከተውን ኢትዮጵያ በግዛቱ ላይ ያላትን አቋም መሠረት በማድረግ እንደ ጉዳዩ አመጣጥ ለመከላከልና ለማስረዳት እንዲሞክሩ ነበር::[69]

የፈረንሳይ መንግስት በጅቡቲ ህዝበ-ውሳኔ ለማድረግ ቁርጠኛ አቋም መያዙ እንደተረጋገጠ በኢትዮጵያ በኩል ሂደቱን ለመቆጣጠርና ከሃገሪቱ ብሔራዊ ጥቅም አንፃር ለማስኬድ እንዲቻል ጠንካራ የድርጊት መርሐ-ግብር ተነድፎ እንቅስቃሴ ተጀመረ:: መጀመሪያ በጅቡቲ ጉዳይ ፖሊሲ ለማውጣትና በፖለቲካውም አመራር ረገድ ሊፈጠር የሚችለውን ለውጥ እየመረመረ ውሳኔ የሚሰጥ በጸሐፊ ትእዛዝ እክሊሉ ሐብተ ወልድ የሚመራና የተመረጡ ሚኒስትሮች በአባልነት የሚገኙበት አንድ የበላይ ኮሚቴ ተቋቋመ:: የበላይ አካሉን ማሳሰቢያ ተከትሎም ንጉሠ ነገሥቱ መስከረም 6፣ 1959 ለአገር ውስጥና ለውጭ አገር ጋዜጠኞች ኢትዮጵያ ስለጅቡቲ የወደፊት ዕድል ያላትን ፖሊሲ ገለፁ::





ንጉሰ ነገስቱ ለመጀመሪያ ጊዜ የሰጡት ኦፊሴላዊ መግለጫ "የፈረንሳይ ሶማሌ" በ19ኛው ክፍለ ዘመን በኮሎኒያሊስቶች ከመያዙ በፊት የኢትዮጵያ ግዛት እንደነበር፤ ግዛቱ በኢኮኖሚ፣ በህዝብና በጂኦግራፊ ከኢትዮጵያ ጋር የተሳሰረና ያለኢትዮጵያ ለመኖር የማይችል መሆኑን፤ የጅቡቲ ወደብ ለኢትዮጵያ ዋና የንግድ በር መሆኑን ያትታል:: በተጨማሪም ኢሳና አፋል የሆኑ ኢትዮጵያውያን ነገዶች በብዛት የሚገኙት በኢትዮጵያ ውስጥ ስለሆነ በጅቡቲ የሚኖሩት አነስተኛ ቁጥር ያላቸው እነዚሁ ነሳዎች ተቆራርጠው ወደሌላ እንዲሆኑ ኢትዮጵያ የማትፈቅድ መሆንዋን፤ የጅቡቲን ሕዝበ-ውሳኔ ሃገራቸው ስትደግፍ የግዛቱ ህዝብ ለራሱ ጠቃሚ ባልሆነ በተቃራኒ መንገድ እንደማይጓዝ በማመን እና ከኢትዮጵያም እንዳይለይ ለማድረግ ማንኛውንም እርምጃ ለመውሰድ ቁርጠኛ ሃሳብ እንዳላት በአጽንኦት ያወሳል:: እንዲሁም ጅቡቲን በሚመለከት ወደፊት የሚሰጡ ማናቸውም ውሳኔ ከላይ ከተመለከቱት ዋና ዋና ሁኔታዎች ጋር የማይያያዝና ግዛቱን ከኢትዮጵያ የሚነጥል ከሆነ መንግስታቸው በምንም አይነት እንደማይቀበለው አሳውቀዋል::[70]

ይህንን ከፍተኛ የፖሊሲ መመሪያ ተከትሎ ተጨማሪ እንቅስቃሴዎች ተግባር ላይ መዋል ጀመሩ:: በጥቅምት 1959 የጅቡቲን ህዝብ ባህልና የፖለቲካ ጠባይ የሚያውቁ እና የመንግስታቸውን ፖሊሲ ተከትለው ለመስራት ይችላሉ ተብሎ የታመነባቸው ግለሰቦች ቁልፍ የሥራ ኃላፊነት ተሰጣቸው:: በዚህም መሠረት አቶ አሐዱ ሳቡሬ ከሞቃዲሾ ተዛውረው በአምባሳደርነት ማዕረግ በጅቡቲ ቆንስል ጀኔራል ሆኑ:: እንዲሁም

[69] ውጉሚ:- ጅቡቲ 52-D3 4፤ ከተማ ይፍሩ ለልጅ እንዳልካቸው መኮንን (ኒውዮርክ) - በጅቡቲ ዙርያ የኢትዮጵያ ፖሊሲ ዘዋሪ መመሪያ፡ ጳጉሜ 4፣ 1958:: ውጉሚ:- ጅቡቲ 55-D3 3፤ ጅቡቲ ለኢትዮጵያ በምትሰጠው ጠቀሜታ ዙሪያ የተዘጋጀ ማስታወሻ፡ ጳጉሜ 5፣ 1958

[70] ውጉሚ:- ጅቡቲ 52-D3 20፤ የንጉሰ ነገስቱ የፖሊሲ ንግግር፡ መስከረም 6፣ 1959፤ በጅቡቲ ጉዳይ ከፍተኛ የፖሊሲ ውሳኔዎች፡ ህዳር 24፣ 1959. Seyoum Haregot, 170-173.

ቀድሞ በጅቡቲ ቆንስል የነበሩት ሻለቃ ደመቀ ረታ የአዳልና ኢሳ አውራጃ ገገር፣ አቶ አሰፋ ገብረማርያም የድሬዳዋ አውራጃ ገገር ተደርገው ሲሾሙ ፊታውራሪ አሰጋኸኝ አርዓያ የአውሳ አውራጃን አቶ አሰፋ ድፋዬ የአሰብ አውራጃን እንዲያስተዳድሩ ተደረገ።

እነኚህ ግለሰቦች ሀገራቸው በጅቡቲ ላይ ያላትን ፖሊሲ ተከትለው የፖለቲካ ዘመቻውን በቀጥታ እንዲመሩና እንዲያስፈፅሙ አደራ ተጣለባቸው። ከፍተኛው የፖሊሲ መመሪያ በሁለት መንገድ - በፅሑፍና በቃል ትዕዛዝ - የተላለፈ ሲሆን ሁለቱም ዓይነት መመሪያ በጥብቅ ሚስጥር ደረጃ የተያዘ ነበር። የአውራጃ ገገርዎቹ በተለይ የጅቡቲ ህዝብ ከኢትዮጵያ ጋር ተዋህዶ ለመተዳደር ፈቃደኝነቱን ሊገልፅ በሚችልበት ሁኔታ፣ ኢትዮጵያዊ የሆነ ዝንባሌና ስሜት እንዲሠርፅበት ለማድረግ እና የግዛቱ ህዝብ በምንም መንገድ ከሶማሊያ ጋር ለመዋሃድ ምኞት ወይም ፍላጎት እንዳያድርበት በተገኘው ዘዴና ስብከት ለመከላከል ያቀደ የሥራ ድርሻ ተሰጣቸው። ቆንስሉ ደግሞ ለፈረንሳይ ባለሥልጣኖች የሚታይ ቀጥተኛ ጣልቃ ገብነት ሳያደርግ በግዛቱ ከሚገኙት የፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር ስውር ግንኙነት የመፍጠርና በሂደቱም የኢትዮጵያ እጅ በጅቡቲ ውስጥ እንዲሠርግ የማድረግ ከፍተኛ ኃላፊነት ተጣለበት።[71]

የጅቡቲ ነፃ አውጭ ንቅናቄንም በተመለከተ የተላለፈው መመሪያ ድርጅቱን በማደርጀት ኢትዮጵያ ለግዛቱ ነፃነት ያላትን ምኞት ለዓለም ማሳወቂያ የፕሮፓጋንዳ መሣሪያ እንዲሆን ነው። በጊዜው የነበረው የኢትዮጵያ አቋም እንደሚያመለክተው የዚህን ንቅንቄ መቋቋም ፈረንሳዮች ቀደም ብለው የሚያውቁት ስለሆነ በሁለቱ አገሮች መካከል አለመግባባት ይፈጥራል ተብሎ አልተገመተም። አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘም ኢትዮጵያ በአ.አ.ድ. ቃል ኪዳን አባልነቷና ካላት ልዩ ተሰሚነት የተነሳ ይህን ድርጅት ከነዓላማው ከመደገፍ ቸል ለማለት እንደማትችል ፈረንሳዮችን ማስገንዘብ እንደሚያሻ ተመልክቷል። በሌላ በኩል ደግሞ

[71] ዝኒ ከማሁ





ሶማሊያና አጋሮቿ ኢትዮጵያ ኮሎኒያሊስት ከሆነው ከፈረንሳይ መንግሥት ጋር በመሻረክ ጅቡቲ በፈረንሳይ አስተዳደር ውስጥ እንዲቆይ ትገፋፋለች ተብሎ የሚነገረውን የፕሮፓጋንዳ ዘመቻ ለመቃረን ንቅናቄውን በፖለቲካ መሣሪያነት መጠቀሚያ ማድረግ እንደሚያሻ ተብራርቷል።

የጅቡቲን ህዝበ-ውሳኔ አስመልክቶ ለነኚህ አስፈጻሚ አካላት በቃል የተላለፈው ትዕዛዝ የግዛቱን የወደፊት ዕጣ ፈንታ በተመለከተ የኢትዮጵያን ትክክለኛ አቋም ያንፀባርቃል። የፈረንሳይ መንግሥት ለጅቡቲ የሰጠው የምርጫ ዕድል በሁለት አቅጣጫ ብቻ የተመራና የተወሰነ መሆኑን የፖሊሲ መመሪያው ያትታል። ይህም በመሆኑ ህዝቡ የወደፊት ዕድሉን ቀጥተኛ በሆነ መንገድ ከኢትዮጵያ ጋር ለማስተሳሰር እንዲያስችለው ሐሳቡን የሚገልፅበት አማራጭ እንዳልተሰጠው በአፅንዖት ያወሳል። ስለዚህም የኢትዮጵያ የፖለቲካ ትግል የጅቡቲ ህዝብ ለራሱ ዘላቂ ጥቅምና ለኢትዮጵያ ዓላማ የሚበጅ መንገድ እንዲመርጥ በመምራትና በመገፋፋት የግዛቱን በሂደት ከኢትዮጵያ ጋር መዋሃድ በሚያረጋግጥ መልኩ መሆን እንዳለበት ያሳስባል።

ይህንን ዕቅድ ለማሳካት በመጪው መጋቢት በጅቡቲ ከሚደረገው ሪፈረንደም ጋር በተያያዘ ኢትዮጵያ ሁለት የፖለቲካ ስምሪት ምርጫ እንደሚጠብቃት ታመነበት። አንደኛው የጅቡቲ ህዝብ በፈረንሳይ ጥበቃ ሥር መተዳደሩን ነቅፎ የተሟላ ነፃነት እንዲጠይቅ በመገፋፋት ከነፃነት በኋላ ከኢትዮጵያ ጋር እንዲቀላቀል የፖለቲካ ዘመቻ ማድረግ ነው። ይህን አማራጭ መከተሉ በራሱ የሚያስከትለው መዘዝ አለ። በመጀመሪያ ደረጃ ትግሉ ከሶማሊያ ሪፐብሊክ ጋር ብቻ መሆኑ ይቀርና ኢትዮጵያን ሲደግፍ ከነበረውና በጅቡቲ ለመቆየት ዕኑ ፍላጎት ካለው ከፈረንሳይ መንግሥት ጋርም ይሆናል። በሁለት ግንባር የሚደረገው ዘመቻ በሰው ኃይልና በገንዘብ ከሚያስከትለው ጉዳት በተጨማሪ የጅቡቲ ህዝብ በኢትዮጵያ፣ በሶማሊያና በፈረንሳይ ዝንባሌ ለሦስትዮሽ ሲከፋፈል የኢትዮጵያ ደጋፊ ሆነው የሚገኙት ክፍሎች መጠናቸው ይቀንሳል። በዚህም የተነሳ በሠላማዊ መንገድ ጅቡቲን የማስመለሱ ጥረት እንቅፋት ያጋጥመዋል።

በሌላ በኩል በሪፈረንደሙ ማግስት ጅቡቲ ነፃ ቢሆን ደግሞ ኢትዮጵያ ተፈላጊነቷንና ተወዳጅነቷን በህዝቡ ዘንድ በአስተማማኝ መንገድ ማስረፅ ከመቻሏ በፊት ይሆናል:: ስለዚህም ፈረንሳይ ግዛቷን ለቃ በምትሄድበት ወቅት በሚፈጠረው ክፍተት (vacume) ምክንያት ኢትዮጵያ በቂ የመደራጃ ጊዜ ሳታገኝ አሉታዊ ገፅታ ሊኖረው የሚችል ወታደራዊ እርምጃ ለመውሰድ ትገደዳለች:: ይህ አካሄድ አገሪቱን በወራሪነት በማስፈረጅ ለተ.መ.ድ. እና አ.አ.ድ. ውግዘት ሊያጋልጣት ከመቻሉም በላይ በዓለም መድረክ ያላትን ክብር ሊያጎድፈው እንደሚችል ተገመተ::

ሁለተኛው አማራጭ የጅቡቲ ህዝብ ለነፃነቱ በቂ ጊዜና ዝግጅት እስኪያገኝ ላልተወሰነ ጊዜ በፈረንሳይ ጥበቃ ሥር መተዳደሩን እንዲመርጥ ውስጥ ውስጡን መገፋፋት ነው:: ይህ ዕውን ከሆነ እስከ ነፃነት ባሉት ዓመታት ኢትዮጵያ የህዝቡን ድጋፍና ዝንባሌ በሚያስተማምን አኳኋን ለማግኘት የሚያስችላትን የረጅም ጊዜ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ዘመቻዋን አጣምራ ለማቀድና ለማስረግ ዕድል ይኖራታል:: የዚህ አማራጭ ሌላኛው በጎ ገፅታ ተደርጎ የተወሰደው ከፈረንሳይ ጋር ያለውን ወዳጅነት ማስጠበቅ መቻሉ እና ህዝቡ ከኢትዮጵያ ለመዋሃድ ባይፈልግ ሊወሰድ ለሚገባው ወታደራዊ ጣልቃ ገብነት የመዘጋጃ በቂ ጊዜ መስጠቱ ነው:: በመጨረሻም ሁለተኛውን አማራጭ በመከተል ኢትዮጵያ የጅቡቲ ህዝብ በሪፈረንደሙ የተሟላ ነፃነቱን መጠየቁን በይፋ ሳትቃወምም ሳታደፋፍርም ግን በፈረንሳይ አስተዳደር ሥር መቆየቱን እንዲመርጥ እንድትገፋፋ የፖ.ሊ.ሲ. ውሳኔ ተላለፈ::[72]

የኢትዮጵያንየፖለቲካ ዘመቻ በቀዳሚነት እንዲያስተባብርና እንዲመራ ኃላፊነት የተጣለበት ኮሚቴ (የጅቡቲው ቆንስልና አራቱ የአውራጃ አስተዳዳሪዎች የሚገኙበት) ከህዳር 29 እስከ ታህሣሥ 5፣ 1959 ባደረገው የፖ.ሊ.ሲ. ግምገማ ከላይ የተሠጠውን መመሪያ በብርቱ ተቃወመ:: በተለይም የቀደመው

[72] ዝኒ ከማሁ





ውሳኔ የተመሠረተበትን በጅቡቲ ህዝብ ዘንድ ለኢትዮጵያ በጎ አመለካከት የለም፣ የግዛቱ ተቀዳሚ ምርጫም ከሶማሊያ ሪፐብሊክ መቀላቀል ወይም ነፃነት ነው የሚለውን እሳቤ ትክክለኛ እንዳልነበር በመረጃ በማስደገፍ አመላከተ:: ይልቁንም የፈረንሳይ በግዛቱ ለተወሰኑ ዓመታት መቆየት ለኢትዮጵያ የመዘጋጃ ጊዜ ይሰጣታል የሚለውን እሳቤ በብርቱ አጣጣለ:: በመካከለኛው ምሥራቅ፣ በአፍሪካና በተቀረው ዓለም ሊፈጠር ከሚችለው የፖለቲካ መለዋወጥ አንፃር ይህንን ማስፈፀሙ እንደታሰበው ቀላል ሊሆን እንደማይችል በአፅንዖት ለመከራከር ተሞከረ:: ለአገሪቱ የሚበጃትም እስከ ሪፈረንደሙ ያሉትን ወራት በመጠቀም የጅቡቲ ህዝብ ነፃነቱን እንዲያገኝ መጣርና በተከታይም ከኢትዮጵያ መዋሃዱን እንዲተገበር መሥራት መሆኑን ተከራከረ::[73] ይህ ሐሳብ በከፍተኛ ባለሥልጣናት ዘንድ ተቀባይነት ቢያጣም በኋላ እንደታየው ትክክል ነበር::

ንጉሰ ነገሥቱ በተገኙበት ጥር 25 የተደረገው ከፍተኛ የፖ.ሊ.ሲ. ስብሰባ በቀደመው አካሄድ እንዲቀጥል ከመወሰኑም በላይ በአተገባበሩ ላይ ተጨማሪ መመሪያዎችን አሳለፈ:: ለኢትዮጵያ ዕቅድ ቁልፍ የሆኑት አዳሎች (አፋሮች) ለዚሁ ሲባል ከፍተኛ ትኩረት ተሰጣቸው:: በምክትል ፕሬዚደንቱ መሐመድ ካሚል መሐመድ እና በቀድሞው ምክትል ፕሬዚደንት ዓሊ አሬፍ ቡርሃን መሪነት ለሁለት ተከፍለው ሲታመሱ የነበሩት የጅቡቲ አፋሮች በጎሳው መሪዎች አማካኝነት እንዲታረቁና የጋራ ግንባር እንዲፈጥሩ ተወሰነ:: ይህንንም ተግባራዊ ለማድረግ አፄ ኃይለ ሥላሴ የራሂታውን ሱልጣን ደጃዝማች ዳውድን እና የአውሳውን ፊታውራሪ ያዩን አስጠርተው እንዲያናግሩ፤ እንዲሁም ቆንስል አለሙ ሳቡሬ በጅቡቲ ያሉትን የጎባድ፣ የኦቦክና የታጁራ ሱልጣኖች እንዲያስተባብሩ ኃላፊነት ተሰጣቸው::

ከዚህም በላይ የጅቡቲ አፋሮች ውድድሩን ለመቋቋምና ብሎም ለማሸነፍ እንዲችሉ የ200,000 ብር ድጋፍ ተደረገላቸው::

[73] ውጉሚ፡- ጅቡቲ 55-D3፤ የፖ.ሊ.ሲ. ውይይትና የውሳኔ ሐሳብ፡ ታህሳሥ 12፣ 1959

እንዲሁም የጅቡቲው ቆንስላ እና አራቱ አጎራባች አውራጃዎች ከዓመታዊ በጀታቸው በተጨማሪ ወደ 250,000 ብር ተመደበላቸው። የጅቡቲ አገረ ገዢ ባሳሰቡት መሠረትም ሶማሊያ መራጮችን ወደ ግዛቱ ለማስረግና የምርጫውን ውጤት ለመቀየር የምታደርገውን ጥረት ለማጨናገፍ፡ የኢትዮጵያ ወታደሮች የጋራ ድንበሩን እንዲያጥሩ ተደረገ። የኢትዮጵያ ሬድዮ በአዳልኛ ቋንቋ መደበኛ ሥርጭት እንዲጀምር ለማስታወቂያ ሚኒስትሩ ለዶ/ር ምናሴ ኃይሌ ኃላፊነት የተሰጣቸው ሲሆን በጅቡቲ የተከሰተውን ረሃብ ተንተርሶም ማሽላ በቅናሽ ዋጋ እንዲቀርብላቸው ተወሰነ።

ከሁሉም የሚያስገርመው ውሳኔ የጅቡቲ ፖለቲካ መሪዎችን እና ታዋቂ ሰዎችን በጎ ፈቃድ ለመሳብ ሲባል ጫት በነፃ እንዲፈቀድላቸው እና በምድር ባቡሩ ላይ በሚካሄደው የኮንትሮባንድ ንግድ ላይ ቁጥጥሩ እንዲላላ መደረጉ ነው። እንዲሁም ተቀማጭነቱ በድሬዳዋ ለሆነው ለኢሳው ባላባት (ዑጋዝ) አንድ መርቸዲስ አውቶሞቢል፣ ለሚስታቸውም የከተማ ቦታና የገንዘብ ችሮታ ተደረገላቸው። [74]

የሬፈረንደሙ ጊዜ እየተቃረበ ሲመጣ ከሁሉም አቅጣጫ ጫናው እየተበራከተ መጣ። የሶማሊያው ጠቅላይ ሚኒስትር አብዲራዛቅ ኑር ሁሴን ለጸሐፊ ትእዛዝ አክሊሉ በፃፉት ደብዳቤ ኢትዮጵያ ስለ ጅቡቲ ነፃነት ከህዝበ-ውሳኔው በፊት እውቅና እንድትሰጥ ጠየቁ። በዚህ መሃል ግን የጅቡቲ ጉዳይ ከታለመለት መንገድ ቢወጣ ኢትዮጵያ ልትወስድ ስለሚገባው ወታደራዊ ጣልቃ ገብነት በሚስጥር ጥናት መደረግ ተጀምሮ ነበር። በተለይም በሦስተኛው ክፍለ ጦር ዋና አዛዥና በኢትዮ-ሶማሊያ ድንበር የጊዜያዊ አዋጅ የታወጀባቸው ግዛቶች የበላይ አስተዳዳሪ በሜጀር ጄኔራል አበበ ገመዳ ኃላፊነት አጠቃላይ ወታደራዊ እቅዱ ተጠንቶ ተጠናቀቀ።[75]

የዚህ ሁሉ ጥረት ውጤት እትዮጵያ እንደፈለገችውና እንዳቀደችው ሆነ። 60 ከመቶ የሚሆነው የግዛቱ ህዝብ (አብላጫው ደንከል) በፈረንሳይ አስተዳዳር ሥር መቆየትን

[74] ውጉሚ፡- ጅቡቲ 55-D3 2፤ በጅቡቲ ሬፈረንደም ዙሪያ የፖሊሲ ውሳኔ፡ ጥር 24፣ 1959። ውጉሚ፡- ጅቡቲ 54-D3፤ ስለ ጅቡቲ ህዝበ-ውሳኔ የቀረበ የትንታኔ ሪፖርት፡ የካቲት 15፣ 1960





ሲመርጥ የተቀረው ግን አፋጣኝ ነፃነትን ጠየቀ። ከሬፈረንደሙ በኋላ ኢትዮጵያ ልትከተለው በሚገባት ፖሊሲ ዙሪያ በተደረገው ውይይት እንደተወሰነው አገሪቱ የጅቡቲ ህዝብ "ጥቅሙንና ጉዳቱን በትክክል አውቆና ተረድቶ ይጠቅመኛል" ብሎ የወሰነውን ምርጫ በደፋ ተቀበለች። በመንግስት ባለሥልጣናት የተወሰደው ግንዛቤ እንደሚያመለክተው ፈረንሳይ በግዛቱ ለጊዜው እንድትቆይ ቢወሰንም በሂደት ጅቡቲን ለቃ መውጣቷ የማይቀር መሆኑን ነው። ስለሆነም ኢትዮጵያ በፈረንሳይ ላይ ሙሉ እምነት ሳትጥል የግዛቱ ህዝብ ወደሷ የሚያዘነብልበትን ዘዴና መንገድ በማዘጋጀት በሥራ ላይ የመተግበሩ አስፈላጊነት ተሰመረበት። ይህም የተባለበት ምክንያት የፈረንሳይ መንግስት ጅቡቲን ለኢትዮጵያ ያስረክባል የሚለው የቆየ እምነት ተጨባጭነት የሌለው መሆኑን በማጤን ነበር።[76]

በዓሊ አሬፍ ጠቅላይ ሚኒስትርነት የሚመራው አዲሱ የጅቡቲ ህግ መምሪያ ምክር ቤት (chamber of deputies) በወሰነው መሠረት የግዛቱ መጠሪያ ከ "ፈረንሳይ ሶማሊላንድ" ወደ "አፋርና ኢሳ የፈረንሳይ ጠረፍ" ተቀየረ። ምንም እንኳን የኢትዮጵያ ፍላጎት የነበረው ጅቡቲ የሚለው ስም ለጊዜው ተቀባይነት ባያገኝም ሶማሌ የሚለው ክፍል ለዘለቄታው መሠረዙ ተፈላጊው ነጥብ ነበር። በቀጣይነት በተላለፈው ውሳኔ መሠረት የኢትዮጵያ መልዕክተኞች በሚገኙባቸው ስብሰባዎች ሁሉ ከአዲሱ መጠሪያ 'ፈረንሳይ' የሚለውን ቃል ትተው "የአፋርና የኢሳ ግዛት" በሚለው ብቻ እንዲጠቀሙ ትዕዛዝ ተላለፈ።

በዚህ መሐል ግን የኢሳዎች ከፖለቲካው ሥልጣን ሙሉ በሙሉ መገለልና የደንከሎቹ ፍፁም የበላይነት (አዲሱን መጠሪያ የአፋሮች ግዛት ብቻ ለማሰኘት እስከመዝለቅ የደረሰ) ለኢትዮጵያ

[75] ውጉሚ፡- ጅቡቲ ሪፖርት 10 825፤ ቆንስል አሐዱ ለሜጀር ጄኔራል አበበ ገመዳ እና ለብ/ጄኔራል ተሾመ እርገቱ (የጦር ሠራዊቶች ሁለተኛ መምሪያ መኮንን)፡ ህዳር 19፣ 1959። ውጉሚ፡- ሶማሌ 8-D1 6፤ ጠቅላይ ሚኒስትር አብዲራዛቅ ለጸሐፊ ትእዛዝ አክሊሉ፡ እ.ኤ.አ. የካቲት 12፣ 1967

[76] Shehim and Searing, 214-214. Thomas A. Marks, "Djibouti: France's Strategic Toehold in Africa", In *African Affairs,* Vol. 73 (January 1974), 102. Shilling, 620-626.

ዕቅድ ተስማሚ አልነበረም። ከሪፈረንደሙ ማግሥት በተደረገ የፖ.ሊ.ሲ. ውይይት ላይ ይህ ጉዳይ በስፋት አከራክሮ ነበር። ከተወሰኑ ክፍሎች የተነሳው ነጥብ በአንድ በኩል የሶማሌዎችን የብሔረተኝነት ስሜት ለማድከም እየተጣረ በሌላ በኩል አፋሮችን ብቻ በማጎልመስ ሂደት ውስጥ ወደፊት ሊያውክ የሚችል የአፋር ናሽናሊዝም (bloc Afar) እንዳይፈጠር ነው።

የኢትዮጵያ ባለሥልጣናት ያስጀመሩት በጅቡቲ አፋሮችና ስሜታቸውና ዓላማቸው በትክክል በማይታወቀው ደጃዝማች ዓሊ ሚራህ መካከል የተጀመረው የትብብር ንግግር ከህዝበ-ውሳኔውም በኋላ መቀጠሉ አደገኛ መሆኑ ተወስቷል። ይህንን ከግንዛቤ በማስገባት ቀድሞ ተግባራዊ ሆኖ የነበረውን ኢሳዎችን የመነጠሉ ፖለቲካ በፍጥነት እንዲቋረጥና በተለይ የኢሳ ህዝባዊ ንቅናቄ ፓርቲ (movement popular) ከሶማሊያ ጋር የመሠረተውን ጠንካራ ግንኙነት ለመስበር ጥረት እንዲደረግ ተወሰነ።

ሌላኛው ውሳኔ የሚያሻው ጉዳይ በድሬዳዋና በአሳይታ መቀመጫውን ያደረገው የጅቡቲ ነፃ አውጭ ንቅናቄ ጉዳይ ነበር። አሁንም የተደረሰው መግባባት ንቅናቄው ተግባሩን እንዲቀጥል የማድረግና ይህን ለማድረግ የተፈለገበትን ምክንያት ለፈረንሳይ መንግሥት በቅድሚያ የማሳወቁ አስፈላጊነት ነው። ስለ ሪፈረንደሙም ቢሆን ከአፍሪካ ነፃ አውጭ ኮሚቴ ለንቅናቄው ጥያቄ በሚቀርብለት ወቅት ውጤቱን ሳይነቅፍ በጅቡቲ ፖለቲካ ውስጥ አንድ እመርታ መሆኑን እንዲያስረዳ ተወሰነ። በተጨማሪም ንቅናቄው ዓላማው ጅቡቲ ራስዋን ችላ ነፃ እንድትወጣ እንደሆነ እንዲያስረዳ ቢጠየቅ ደግሞ ራስን ችሎ ለመኖርም ሆነ ከኢትዮጵያ ጋር ለመቀላቀል ወደፊት ተጨማሪ ህዝበ-ውሳኔ መደረግ እንደሚኖርበት ማስታወቅ እንደሚኖርበት ተወሰነ።[77]

[77] ውጉማ፡- ጅቡቲ 55-D3፤ በጅቡቲ ጉዳይ የፖ.ሊ.ሲ. ውሳኔ፡ ሰኔ 20፣ 1959። ውጉማ፡- ጅቡቲ 55-D3 2፤ በጅቡቲ ጉዳይ የፖ.ሊ.ሲ. ውሳኔ፡ ሚያዝያ 30 እና ሰኔ 30፣ 1959። ውጉማ፡- ጅቡቲ 57-D3 3፤ በጅቡቲ ጉዳይ የፖ.ሊ.ሲ. ጥናት፡ ሐምሌ 17፣ 1959





ነገር ግን ህዝበ-ውሳኔው ሶማሊያን ጨምሮ ከአፍሪካውያን እና ከተቀረው ዓለም የገጠመው ተቃውሞ ከሚጠበቀው በላይ ጠንካራ ነበር። ገለልተኛ የውጭ ታዛቢዎች ሂደቱን አለመታዘባቸው፣ ውጤቱ በዋነኛነት የጎሳ ልዩነትን የተከተለ መሆኑ፣ የግዛቲ የነፃነት ጥያቄ በቆይታ መያዙ ወዘተ የተቃውሞው መሠረቶች ነበሩ። ከአሥራ አንዱ የአ.አ.ድ. የነፃ አወጭ ኮሚቴ አባላት ስድስቱ ሪፈረንደሙን አወገዙ። በተጨማሪም በድሬዳዋ ያለው የጅቡቲ ንቅናቄ ውጤቱን በመቀበሉ በአ.አ.ድ. እንዲወገዝና ከድርጅቱ የሚያገኘው የገንዘብ እርዳታ እንዲቋረጥበት ማሳሰባቸው ለኢትዮጵያ ባለሥልጣናት አሳሳቢ ነበር።

የተ.መ.ድ. ነፃ አውጭ ኮሚቴም በጉዳዩ ላይ ሊሰጥ የሚችለው አሉታዊ መግለጫ ኢትዮጵያውያኑን ስላሳሰባቸው በሪፈረንደሙ ውጤት ዙሪያ በተ.መ.ድ. ስብሰባዎች ላይ አስተያየት ከመስጠት እንዲቆጠቡ አስገደዳቸው። በተለይ የራስን ዕድል በራስ ከመወሰን መርህ አንፃር በጅቡቲ የተከናወነው ምርጫ ውጤት አጠራጣሪነት፣ የተ.መ.ድ. ታዛቢዎች በሂደቱ ያለመሳተፍ ወይም በሪፈረንደሙ ዋዜማ ሶማሌ የሆኑ የግዛቲ ነዋሪዎች እንዲባረሩ ስለመደረጋቸው ንግግር መደረጉን ኢትዮጵያ አልፈለገችውም ነበር። ጉዳዩ በተ.መ.ድ. ጉባኤ ለውሳኔ የሚቀርብ ከሆነ ግን በነኚህ ነጥቦች ላይ ገለልተኛ እንዲሆኑ (abstain) ለኢትዮጵያ ልዑካን መመሪያ ተሰጠ።[78]

የመጋቢት 1959ኙን የጅቡቲ ህዝበ-ውሳኔ ተከትሎ የንጉሡ ነገሥቱ መንግስት ሂደቱን ለመቆጣጠር እና ላመነበት ፖ.ሊ.ሲ. ተፈፃሚነት ያሳየው ቁርጠኝነት ከምርጫው በኋላ ሊቀጥል ሳይችል ቀረ። በረጅም ጊዜ ሊተገበሩ ታቅደው የነበሩ

[78] ውጉማ፡- ጅቡቲ 55-D3 3፤ ማስታወሻ ለጃንሆይ፡ ነሐሴ 18፣ 1959። ውጉማ፡- ጅቡቲ 55-D3 2፤ በተመድ የኢትዮጵያ ልዑካን የተላለፈ መመሪያ፡ ጥቅምት 1960

ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች መና ሆኑ:: አገሪቱ የምትከተለው ፈረንሳይን ያለማስቀየም እና በሌላ በኩል ደግሞ በአ.አ.ድ. መድረኮች የጅቡቲን ነፃ መውጣት የመደገፍ ተፃራሪ አካሄድ በአስቸኳይ የማስተካከሉም ጥሪ ቸል ተባለ:: በአሳፋሪ ሁኔታ ላይ የሚገኙትን በጅቡቲ የኢትዮጵያ ቆንስላ ጽ/ቤትና ሌሎችም ንብረቶች ለመጠገንና በሂደቱም የሃገሪቱን መልካም ገፅታ ለማስጠበቅ፣ ለአርባ ጂቡቲያውያን የትምህርት ዕድል ስለመፍቀድ፣ ቀደም ሲል ከፈረንሳይ መንግስት ጋር በተፈረሙ ስምምነቶች የተረጋገጡ የኢትዮጵያ ጥቅሞችን (በአሳል ሐይቅ፣ በምድር ባቡርና በወደብ ዙሪያ) ሥራ ላይ ማዋል ወዘተ ከቀረቡ ዋና ዋና ሃሳቦች መካከል ሲሆኑ ተግባራዊ ሳይሆኑ ቀሩ::[79] ይልቁንም የሃገሪቱ ዋነኛ ትኩረት የአ.አ.ድ. ነፃ አውጭ ኮሚቴ የድሬዳዋውን ንቅናቄ ለመጎብኘት ሲመጣ ስለ ድርጅቱ ጥንካሬና እንቅስቃሴ የተዛባ መረጃ በመስጠት ማሳመን እና በአ.አ.ድ. መድረኮች የሶማሊያ አቤቱታ ተቀባይነት እንዳያገኝ መታገል ነበር::

በስልሳዎቹ ሁለተኛ አጋማሽ በኢትዮጵያ የተከሰተው የፖለቲካ ትኩሳትና ይህን ተከትሎ የመጣው ለውጥ የጅቡቲ ጉዳይ (እንደተቀረው የውጭ ግንኙነት ፕሮግራሞች ሁሉ) እንዲረሳ አደረገ:: ስለ አተገባበራቸው ክርክር ይደረግባቸው የነበሩ የፖሊሲ ሐሳቦች በእንጥልጥል ቀሩ:: ከሁሉም በላይ አጠቃላይ ሂደቱ በጅቡቲ ፖሊሲ ዙሪያ አዳዲስ ተዋንያንን አስተዋወቀ::

[79] ውጉሚ:- ጅቡቲ 54-D3፤ ፊታውራሪ ደምሴ ተፈራ (ጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት) ለጸሐፊ ትእዛዝ አክሊሉ እና ለከተማ ይፍሩ፡ የካቲት 15፣ 1960:: ውጉሚ:- ጅቡቲ 52-D3 26፤ በጅቡቲ ጉዳይ የፖሊሲ ጥናት፡ ሚያዝያ 29 እና 30፣ 1960:: ውጉሚ:- ጅቡቲ 55-D3፤ በፖሊሲ ጥናት ክፍል የቀረቡ የተግባር ሐሳቦች፡ ሚያዝያ 30፣ 1960:: ውጉሚ:- ጅቡቲ 54-D3፤ ቆንስል አሐዱ ለጃንሆይ በጅቡቲ ጉዳይ ሊሰሩ ስለሚገቡ ሥራዎች፡ ሚያዝያ 28፣ 1962





## 3.2. ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ እና ጅቡቲ

የ1966ቱን ህዝባዊ አመፅ ተከትሎ ወደ ስልጣን የመጣው ወታደራዊ መንግሥት በጅቡቲ ጉዳይ ላይ የበኩሉን አቋም ለመያዝ ያስገደዱት ዘርፈ ብዙ አከባቢያዊና ዓለም አቀፋዊ ተፅዕኖዎች ነበሩ:: በጅቡቲ እየጠነከረ የመጣው የብሔረተኝነት ስሜት፣ የሶማሊያ መንግሥት ፖለቲካዊና ወታደራዊ ግፊቶች፣ በአፍሪካ ቀንድ የተከሰተው የርዕዮተ-ዓለም መለዋወጥና ይህንን ተከትሎ የመጣው ትንቅንቅ ወዘተ ከብዙዎቹ ምክንያቶች መካከል ይመደባሉ:: አዲሱ የኢትዮጵያ መንግሥት የሶሺያሊዝም መርህ አራማጅ መሆን ሃገሪቱ ከጅቡቲ ቅኝ ገዢ ከፈረንሳይ ጋር የነበራትን መቀራረብ ያደበዘዘው ከመሆኑም በላይ የምዕራቡን ዓለም አጠቃላይ ይሁንታ አሳጣው:: በተቃራኒው ደርግ ሥልጣኑን ለማደላደል በሚሞክርባቸው የመጀመሪያዎቹ ወሳኝ ዓመታት ውስጥ ሶማሊያ በዚያድ ባሬ መሪነት ወታደራዊ አቅሟን ከማጎልበቷም በላይ በጅቡቲ ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎች ላይ ጠንካራ ተፅዕኖ ማሳደር ቻለች:: ደርግ ስለ ጅቡቲ የወደፊት ህልውና የተደራጀ ፖሊሲ ለመንደፍ የወሰደበት ጊዜ አጭር ቢሆንም በአብዮቱ አፍላ የትግል ሂደቶች ኢትዮጵያ ያባከነቻቸው ጥቂት ወራት አጠቃላይ ስዕሉን ቀየሩት::

ጅቡቲ በኢትዮጵያ ፖለቲካና ኢኮኖሚያዊ ህልውና ላይ ያላትን የማይናቅ ሚና የተረዱት የደርግ ባለሥልጣናት የግዛቱ የወደፊት የፖለቲካ አዝማሚያ የሃገሪቱን እርምጃ ሊያሳድገውም ሆነ ሊያደናቅፈው እንደሚችል ግንዛቤ የወሰዱት ወደ ሥልጣን በመጡ በጥቂት ወራት ውስጥ ነበር:: ስለሆነም ከጅቡቲ ጋር ያላቸውን ወደፊትም ሊኖራቸው የሚገባውን አቋም በአስቸኳይ ማስላትና ማስተካከል ከተሳናቸው ለመጪው ትውልድ ችግር አውራሽ እና ተወቃሽ መሆናቸው እንደማይቀር አመኑ::

በፖሊሲ ጥናት ክፍል የቀረቡ የተግባር ሐሳቦች፡ ሚያዝያ 30፣ 1960:: ውጉሚ:- ጅቡቲ 54-D3፤ ቆንስል አሐዱ ለጃንሆይ በጅቡቲ ጉዳይ ሊሰሩ ስለሚገቡ ሥራዎች፡ ሚያዝያ 28፣ 1962

ነገር ግን በደርግ ባለሥልጣናት መካከል ግዛቱን በተመለከተ ፍፁም መግባባት ነበር ማለት አይቻልም። ወታደራዊውን አንጃ ያምሱ የነበሩ ርዕዮተ-ዓለማዊ አመለካከቶች ጅቡቲንም በተመለከተ በፖለቲከኞቹ መካከል የሃሳብ ልዩነት ፈጥረው ነበር። ጥሩ ምሳሌ ሊሆን የሚችለው በዶ/ር ሠናይ ልኬ (መኢሶን) መሪነት የተወሰነው ቡድን ለግዛቱ አፋጣኝ ነፃነት ስለመስጠት አስፈላጊነት መከራከሩ ነው። ቡድኑ የኢትዮጵያ መሠረታዊ ፍራቻ የነበረውን የጅቡቲ ከሶማሊያ የመቀላቀል አማራጭ እምብዛም ከግንዛቤ ሊያስገባ አለመፈለጉ ለተቀረው የደርግ ክፍል አስደንጋጭ ሆኖ ነበር። እነ ዶ/ር ሰናይን ከዚህ አንፃር ለማሳመን የተደረገው ጥረት መክሸፉ በደርግ መዋቅር ውስጥ ከአገራዊ እሳቤ ባሻገር ለፖለቲካዊ አስተሳሰብ ቅድሚያ ይሰጥ እንደነበር አመላካች ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል።[80] በሂደት ግን ይህ ቡድን ተሰሚነት እያጣ መምጣቱ ለዘላቂው የደርግ ፖሊሲ መቀረጽና ተግባራዊ መሆን በር ከፈተ።

በወቅቱ የጅቡቲ ሁኔታን አሳሳቢ ካደረጉት ምክንያቶች መካከል እየተጠናከረ የመጣው የቀይ ባሕር በዓረብ መንግሥታት ብባ ሥር መውደቅ እና ይህም በኢትዮጵያ ላይ የሚያደርሰው ተጠቂነት፣ ጅቡቲ ከሶማሊያ ጋር እየተደረገ ለቆየው ትግል አንዱ አካል መሆኑ፣ ግዛቱ በኤደን ባህረ ሠላጤ በኩል ከህንድ ውቅያኖስ ጋር የሚያገናኝ ቁልፍ በር መሆኑ ወዘተ ይገኙባቸዋል። ይህንን ለማስፈፀም ኢትዮጵያ ከሶማሊያም ሆነ ከጅቡቲ ፖለቲካ አይላ መገኘት እንዳለባት፤ በሃገር ውስጥ አስተዳደር የጅቡቲ አዋሳኝ አውራጃዎችን አስተዳደራዊና ኢኮኖሚያዊ ድርጅት ማጎልበት፣ በማናቸውም የጅቡቲ ምርጫዎችና እንቅስቃሴዎች የኢትዮጵያ እጅ፣ ዓይንና ጆሮ በቅርበት እንዲገኝ እና በጅቡቲና በፓሪስ ከፍተኛ የፖለቲካ ችሎታ ያላቸው አምባሳደሮች እንዲሾሙ ተመከረ።[81]

---

[80] አምባሳደር ፍትጉ ታደሰ (በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የጅቡቲ ጥናት ቡድን መሪ እና በአምባሳደር ማዕረግ በጅቡቲ ቆንስል)

[81] ውጉማ፡- ጅቡቲ 49-D3 11፤ በጅቡቲ ጉዳይ የቀረበ የውሳኔ ሐሳብ፡ ታህሳሥ 27፣ 1967





ይህን ተከትሎ ለረጅም ጊዜ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የጅቡቲ ጥናት ክፍል ኃላፊ የነበሩት ዶ/ር ፍትጉ ታደሰ በአምባሳደር ማዕረግ በጅቡቲ ቆንስል ሆነው ተሾሙ።

ዘርፈ ብዙው የጅቡቲ ጉዳይ ግን እንዲሁ በቀላሉ የሚታለፍ አልነበረም። የመጀመሪያው ፈተና የጅቡቲ የውስጥ አስተዳደር መሪ ዓሊ አሬፍ ከፈረንሳይ እና ሶማሊያ በመቀናጀት ሊተገብሩት የሞከሩት የትልቁ አፋር ሪፐብሊክ (ብሎክ አፋር) ውጥን ነው። ከ1967 የመሬት ዓዋጅ በኋላ ወደ ጅቡቲ የተሰደዱት የአፋሩ ባላባት ቢትወደድ ዓሊ ሚራህ በዓሊ አሬፍና በግዛቱ ገዢ ሙሴ ደብሩን የተደረገላቸው አቀባበልና ድጋፍ፤ የዓሊ ሚራህ ልጆች ሐንፍሬ ዓሊና አዳይስ ዓሊ ከሞቃዲሾ ይህንኑ ለመተግበር መንቀሳቀሳቸው በኢትዮጵያ የግዛት ሉዐላዊነት ላይ እንደተቃጣ ወንጀል ተቆጠረ። የብሎክ አፋርን ውጥን ለማክሸፍ በሚል በአውሳና በአሰብ በኩል ያለው የጅቡቲ ድንበር በጥብቅ ቁጥጥር ሥር እንዲሆን ከመታዘዙም በላይ ዓሊ ሚራህን በራሳቸው ሰዎች ለማስገደል ታቀደ። ነገር ግን ሁለተኛው እቅድ ከመተግበሩ በፊት ጭምጭምታው በመሰማቱ በአፋሮች ዘንድ የተከሰተውን አለመረጋጋት ለማስቀረት ሲባል ቢሰረዝም ቢትወደዱ ከጅቡቲም እንዲወጡ ግፊት ስላሳደረባቸው ቋሚ አድራሻቸውን በጅዳ አደረጉ፤ ልጃቸው ሐንፍሬም ወደ ሰንዓ (የመን) ተሰደደ።[83]

የደርግ ሌላው እርምጃ በኢትዮጵያ በተከናወነው የመንግሥት ለውጥና አገሪቷ በተከተለችው ግራ ዘመም

---

[82] ውጉማ፡- ጅቡቲ 49-D3 11፤ በጅቡቲ በመገኘት የተደረገ ጥናት ሪፖርት፡ ሚያዝያ 14፣ 1967፤ ቆንስል ዶ/ር ፍትጉ ታደሰ ለብ/ጀኔራል ተፈሪ ባንቲ (የደርግ ሊቀ መንበር) - ከጅቡቲ ገዢና ከዓሊ አሬፍ ጋር የተደረገ ውይይት ሪፖርት፡ ሚያዝያ 15፣ 1967። ፍቅረሥላሴ ወግደረስ፣ *እኛና አብዮቱ* (ሎስ አንጀለስ- ካሊፎርኒ፡ ፀሐይ አሳታሚ, 2006 ዓ.ም.), ገፅ 203-204. Yasin Mihammed Yasin, "Political History of the Afar in Ethiopia and Eritrea," in *Africa Spectrum*, Vol. 43, No. 1 (2008), 44-50.

ፖለቲካ ጥርጣሬ ያደረባትን ፈረንሳይን የማግባባቱ ጥረት ነበር። እየተጠናከረ በመጣው የጅቡቲ ፓርቲዎች የነፃነት ጥያቄ እና የሶማሊያ ግዛቱን የመጠቅለል ፍላጎት የተረበሹት ፈረንሳዮች አጋራቸው በነበረችው ኢትዮጵያም መተማመን አልቻሉም። በመጋቢት 1967 የፈረንሳዩ ፕሬዚደንት ዠስካር ደስታንግ በሴኔጋሉ መሪ በኩል ለብ/ጀኔራል ተፈሪ ባንቱ በላኩት መልዕክት ሃገራቸው ለጅቡቲ ነፃነትን ለማቀዳጀት እንደምትሻ በመልሱ ግን በጅቡቲ ወደብም ሆነ በአጠቃላይ ግዛቱ አንዳንድ ፋሲሊቲ እንዲኖራት ዋስትና እንደምትፈልግ ጠየቁ። በተጨማሪም ኢትዮጵያና ሶማሊያ ጅቡቲን በኃይል ለመያዝ እንደማይፈልጉ ፈረንሳይ አስተማማኝ ዋስትና እንደምትፈልግ አስታወቁ።[83]

የብሎክ አፋር መርህን በመደገፍ በኢትዮጵያ የውስጥ ፖለቲካ ፈረንሳይ የምታደርገውን ጣልቃ ገብነት የሚያወግዘው የደርጉ አቋም ጎን ለጎን በጅቡቲ ያለውን የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅም ለማስጠበቅ የፈረንሳይን በጎ ፈቃድ መፈለጉ አልቀረም። ጅቡቲን ለዘለቄታው ከኢትዮጵያ ጋር በኢኮኖሚ ለማስተሳሰር ተወጥኖ በነበረው ፖሊሲ ከፈረንሳይ ጋር በመተባበር በጅቡቲ ከተማ የነዳጅ ማጣሪያና የጋራ ባንክ ለማቋቋም እንዲሁም በአፋር የጂኦተርማል ኢነርጂ ልማት ለማድረግ የተደረገው ጥረት የዚሁ አንዱ አካል ነበር። ፈረንሳይም በበኩሏ ከኢትዮጵያ ጋር ለመተባበርና ለመመካከር ዝግጁነቷን አሳይታ ነበር። ነገር ግን ብዙም ሳይቆይ በጅቡቲ ላይ ያላትን አቋም እና በተያያዘም ከኢትዮጵያ ጋር የነበራትን የመተባበር መንፈስ ቀየረች።

በኢትዮጵያ በኩል ለዚህ መለዋወጥ እንደ ምክንያት ከቀረቡት መካከል የአረብ አገራት በነዳጅ ሃይላቸው (petro-clout) በመጠቀም በፈረንሳይ ላይ ያሳደሩት ተፅዕኖ፣

[83] ውጉሚ፦ ጅቡቲ 49-D3 11፤ በጉዳዩ ዙሪያ የቀረበ ማስታወሻ፡ ሚያዝያ 2፣ 1967። Julian Crandall Hollick, "French Intervention in Africa in 1978," in *The World Today*, Vol. 35, No. 2 (Feb. 1979), pp. 71-72.





ሶማሊያ በእጅ አዙር የአረቦችን ድጋፍ ከመጠቀምም በላይ ሞቃዲሾ በሚገኘው የጅቡቲ ነፃ አውጭ ድርጅት (F.L.C.S.) እና ጅቡቲ ግዛት ውስጥ በሚገኘው ዋነኛ የተቃዋሚ ፓርቲ (Liberation populaire Africains pour l'independance — L.P.A.I.) አማካይነት በግዛቱ ብጥብጥ እንዲነሳ በማድረግ በፈረንሳይ ላይ ያሳደረችው ተፅዕኖ፣ የፈረንሳዩ ፕሬዚደንት ሙሴ ዠስካር ዴስታን አገራቸው በጅቡቲ ጉዳይ ስትከተለው የነበረውን አቋም መቀየራቸውና አፋጣኝ ነፃነት ለመስጠት ማቀዳቸው፣ የአረብ ሊግ አባል የሆነችው ሶማሊያ ከሰኔ 1974 እስከ ሐምሌ 1975 ድረስ የአ.አ.ድ. ሊቀ መንበር መሆን ወዘተ ይገኙበታል።[84]

ከየአቅጣጫው የተከሰተባትን ጫና ከጥቅሟ አንፃር ለማራመድ በመሻትም ፈረንሳይ ከሶማሊያ ሪፐብሊክ ጋር ወደመስማማቱ ያዘነበለች ሲሆን ለዚሁም የሚሆን አስታራቂ ሐሳብ (modus vivendi) አገኘች። በዚህም መሠረት በአንድ በኩል ሶማሊያ ጅቡቲን ከግዛቱ እቀላቅላለሁ ማለቷን በይፋ ከማሳወቅ እንድትቆጠብና የፈረንሳይን ጦር ሠፈር በጅቡቲ ውስጥ መኖር እንድትቀበል ተደረገ። በተለዋጩ ደግሞ F.L.C.S. የተባለው ሞቃዲሾ የመሠረተችው የጅቡቲ ነፃ አውጪ ሠራዊት በአዲስ መልኩ በጅቡቲ ጦር ኃይል ውስጥ እንዲካተት ፈረንሳይ ልታመቻች፣ ጥረቱንም በገንዘብም ልትረዳ፣ በግዛቱም የሶማሊያ

[84] ውጉሚ፦ ጅቡቲ ልዩ ልዩ ፋይሎች 2 1፤ ጅቡቲን ከኢትዮጵያ በኢኮኖሚ ለማስተሳሰር የተላለፈ መመሪያ። ብ/ጀኔራል ተፈሪ ባንቱ ለጳውሎስ አብርሃም (ፕላን ኮሚሽን ኮሚሽነር)፡ ግንቦት 14፣ 1967፤ በፕላን ኮሚሽን ስለተደረገ ውይይትና ውሳኔ ክፍሌ ወዳጆ (ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር) ያቀረቡት ማስታወሻ፡ ሐምሌ 10፣ 1967። ውጉሚ፦ ጅቡቲ 49-D3 11፤ ጳውሎስ አብርሃም ለክፍሌ ወዳጆ፡ ሰኔ 13፣ 1967፤ በፈረንሳይ አቋም መለዋወጥ ዙሪያ የቀረበ ማስታወሻ፡ መስከረም 1968። ውጉሚ፦ ጅቡቲ 54-D3፤ በጅቡቲ ወቅታዊ ሁኔታ ላይ የተደረገ ጥናት ሪፖርት፡ መጋቢት 30፣ 1968፤ ቆንስል ፍትጉ ታደሰ ለክፍሌ ወዳጆ፡ ሐምሌ 20፣ 1968። ውጉሚ፦ የጅቡቲ ሁኔታ ሪፖርት 9 1፤ ቆንስል ፍትጉ ታደሰ ለክፍሌ ወዳጆ፡ ሐምሌ 23፣ 1968

ይዞታ እንዲጠናከር በማድረግ አፋሮችን የሚጎዳ ስምምነት አደረገች::

ከዚያን ጊዜ ወዲህ የL.P.A.I. አጋር የሆነው F.L.C.S. በጅቡቲ ስልጣን እንዲይዝ ለማድረግ ሶማሊያ ከፍተኛ ዝግጅት ማድረግ ጀመረች:: ይህን ውጥን ከግቡ ለማድረስ በአንድ በኩል በኢሳዎች የተገነባ የጦር ሠራዊት ተመሠረተ:: በሌላ በኩል በወደፊቱ የጅቡቲ መንግስት መዋቅር በየዘርፉ ተመድበው ሊያገለግሉ የሚችሉ በርካታ የሲቪል ሠራተኞች እንዲሰለጥኑ ተደረገ:: የዚህ ውጤት በኢትዮ-ፈረንሳይ ወዳጅነት ወቅት ሲተገበር የነበረው የአፋር ጎሳን የቁጥር የበላይነት የተመረኮዘው የጅቡቲ የውስጥ አስተዳደር ሥርዓት ተለውጦ ፈረንሳዮች የኢሳውን የበላይነት የሚያረጋግጥ ፖለቲካ መፍቀዳቸው ነበር:: ይህን ተከትሎም በሐምሌ 1968 የአፋር ወገን የነበሩት የግዛቱ ጠቅላይ ሚኒስትር ዓሊ አሬፍ ከስልጣን እንዲወርዱና በምትካቸው የተቃዋሚው የኢሳ ፓርቲ የፖለቲካ ምህዳሩን በበላይነት እንዲመራ ተደረገ::

የሶማሊያ መንግሥት ለረጅም ዓመታት ያራመደው የተቀናጀ ጅቡቲን የመጠቅለል ፖሊሲ በግዛቱ ለታየው አጠቃላይ ለውጥ እንደ ምክንያት ሊጠቀስ ይችላል:: ሶማሊያ አባል ከሆነችበት ከአረብ ሊግ ያገኘችው ይሁንታ እቅዷን ለማሳካት የተሻለ ዕድል እንዲኖራት አስቻለ:: አገሪቱ ነፃ ከወጣችበት ጊዜ አንስቶ በጅቡቲ ጉዳይ የተከተለችው ወጥ ፖሊሲ እና ይህንን ለመተግበር በፖለቲካውና በወታደራዊው መስክ ያደረገቻቸው ዝግጅቶች በጊዜው ውጤት ማሳየት ጀምረው ነበር:: በኢትዮጵያና በሶማሊያ መካከል ጅቡቲን በተመለከተ ፍጥጫው ወደ ወታደራዊ ግጭት ቢያመራ እንኳን በወቅቱ የነበረው የኃይል ሚዛን ወደ ሶማሊያ ያዘነበለ እንደነበር በደርግ ባለሥልጣናት በኩል ታመነ::

የዚህ ሁሉ ውስብስብ ችግር መደራረብ በኢትዮጵያ በኩል አፋጣኝ ውሳኔን የሚሻ ነበር:: በደርግ በኩል የተወሰደው የመጀመሪያው እርምጃ አጠቃላይ ጉዳዩን የሚያጠና እና ለአገሪቱ የሚበጃትን የፖሊሲ ውሳኔ የሚያቀርብ የሚኒስትሮች ኮሚቴ ማቋቋም ነው:: ኮሚቴው በታህሳሥ 1967 የተዋቀረ ሲሆን ከረጅም ጊዜ ጥናት በኋላ የውሳኔ ሃሳቡን በሚያጠናቅርበት ወቅት ፈረንሳይ በሐምሌ 1969 ለጅቡቲ ነፃነት ለመስጠት ወስና ነበር:: በመሆኑም መመሪያው የቀደሙ ዕውነታዎችን ከመገምገም ባሻገር መጪውን ሁኔታ ከግምት ማስገባት ነበረበት::[85]

በነዚህ ጊዜያት ግን አገሪቱ በጅቡቲ ጉዳይ ስትከተላቸው የነበሩት መርሆዎች ሙሉ ለሙሉ ተቀየሩ:: ዋነኛ የነበረው ግዛቱን የኢትዮጵያ ሉዐላዊ አካል አድርጎ ይቆጥር የነበረውን የቀደመውን ፖሊሲ በመተው ጅቡቲ ራሱን የቻለ ነፃ መንግሥት እንዲመሰርት መደገፉ ነው:: በ1967 ኢጋማሽ ይፋ የተደረገው አዲሱ አቋም እንደሚከራከረው በጅቡቲ አከባቢ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅም ሊጠበቅ የሚችለው የጅቡቲ ህዝብ ከኢትዮጵያ ጋር ያለውን የጋራ ጥቅም ተገንዝቦ በሠላምና በጥሩ ጉርብትና ከኢትዮጵያ ጋር ለመኖር ሲፈልግ መሆኑ ተሰምሮበታል:: በተጨማሪም የጅቡቲ መንግስት የኢትዮጵያን ጥቅም ሊቀናቀን የሚችል ኃይል በግዛቱ የማያስገባ እውነተኛ ነፃነት ፈላጊ መንግሥት ሊሆን ይገባል:: ኢትዮጵያ በጅቡቲ ላይ ምንም ዓይነት የመሬት ጥያቄ እንደሌላትም በይፋ ተገለፀ::

ይህ ሲባል ግን ኢትዮጵያ በጅቡቲና በቀይ ባህር የነበሯትን ብሔራዊ ጥቅሞች በማንኛውም መንገድ ለማስጠበቅ ዝግጁ መሆኗን በማረጋገጥ ጭምር ነበር:: በተለይ ከሶማሊያም ሆነ ከአረቦች ጣልቃ ገብነትና ተፅዕኖ ግዛቱን ለመከላከል ቁርጠኛ አቋም ተያዘ፣ በይፋም ተነገረ:: የደርግ አቋም ጅቡቲ የኢትዮጵያን 75 ከመቶ የንግድ እንቅስቃሴ በባብ ኤል መንደብ በኩል ወደ ህንድ ውቅያኖስ ለማውጣት ያለውን ስትራቴጂካዊ ጠቀሜታ ከማስታወሱም በላይ ይህ ግዛት የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅም ሊቀናቀን በሚችል በማንኛውም የውጭ ኃይል እጅ ቢወድቅ ለኢትዮጵያ ደህንነት (security) አስጊ ሁኔታ እንደሚፈጥር ያስረግጣል:: የጅቡቲን ነፃነት የሚያምነው አዲሱ ፖሊሲ ጎን ለጎን ግዛቱ በኢትዮጵያ ላይ ያለውን የኢኮኖሚ ጥገኝነት በመሳሪያነት መጠቀምንም መሠረት ያደርጋል::

[85] ውጉሚ ጅቡቲ 49-D3 11፣ የፖሊሲ ኮሚቴ ስለማቋቋም፡ ታህሳሥ 24፣ 1967

ከቀደመው መንግሥት ፖ.ሊሲዎች ጋር በተመሳሰለ ግን በሶማሊያ ይደገፍ የነበረውን እንቅስቃሴ ለመቀልበስ ሲባል በድሬዳዋ የሚገኘውን የጅቡቲ ነፃ አውጭ ንቅናቄ ማጠናከሩ እና የአፋር ወገኖችን የማሰልጠኑና የማስታጠቁ ሥራ ተጠናክሮ ቀጠለ። በተጨማሪም በግዛቱ የውስጥ አስተዳደርና ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ ጉዳይ እያየለ የመጣውን ሶማሊያ ዘመም የሆነውን የኢሳ ወገኖች ፓርቲ (L.P.A.I.) ሊቋቋም የሚችል በዓሊ አሬፍ የሚመራ የአፋሮች ፓርቲ (Union Nationale pour l'independendance - U.N.I. በዘልማዳዊው የኢትዮጵያ ባለስልጣናት አጠራር – ዩኒ) በኢትዮጵያ አነሳሽነት በህዳር 1968 ተመሠረተ። እንዲሁም በሐሰን ጉሌድ ከሚመራው የጅቡቲ ተቃዋሚ ፓርቲ ጋር የመጀመሪያ ደረጃ ንግግር ተጀምሮ ነበር።[86]

በታህሳሥ 16፣ 1969 የቀረበው የሚኒስትሮች ኮሚቴ ሪፖርት ጅቡቲን በሚመለከት ያሳለፋቸው ውሳኔዎች በግዛቱ እየተካሄዱ ከነበሩ ፈጣን ለውጦች አንፃር የዘገየ ቢሆንም የኢትዮጵያን አጠቃላይ የፖሊሲ አቅጣጫ የወሰነ ነበር። የፖ.ሊሲ ውሳኔው በተለይ ከዓመት ባነሰ ጊዜ ውስጥ ተግባራዊ የሚሆነውን የጅቡቲን ነፃነት ከግንዛቤ በማስገባት፤ በሂደቱም ሥልጣን ሊይዙ የሚችሉ የፖለቲካ ሃይሎችን ለማዘጋጀት፣ የሶማሊያን የተቀናጀ ፖለቲካዊ ጣልቃ ገብነት እና ወታደራዊ

[86] ውጉሚ:- ጅቡቲ 49-D3 11፤ በጅቡቲ በመገኘት የተደረገ ጥናት ሪፖርት፡ ሚያዝያ 14፣ 1967፤ ጳውሎስ አብርሃም ለክፍሌ ወዳጆ፡ ሰኔ 13፣ 1967፤ በፈረንሳይ አቋም መለዋወጥ ዙሪያ የቀረበ ማስታወሻ፡ መስከረም 1968፤ ለጅቡቲ አፋር ወጣቶች የውትድርና ስልጠና ስለመስጠትና ስለማስታጠቅ፡ ግንቦት 3፣ 1968። ውጉሚ:- ጅቡቲ 51-D3 1፤ በአውሳ የማሰልጠኛ ካምፕ ስለተደረገ ጉብኝት፡ ግንቦት 4፣ 1968።ውጉሚ:- ጅቡቲ 54-D3፤ በጅቡቲ ወቅታዊ ሁኔታ ላይ የተደረገ ጥናት ሪፖርት፡ መጋቢት 30፣ 1968። ውጉሚ:- ጅቡቲ 54-D3 11፤ በጅቡቲ ጉዳይ የኢትዮጵያ ፖ.ሊሲ መግለጫ፡ እ.ኤ.አ. ታህሳሥ 7፣ 1975። ውጉሚ:- ጅቡቲ 54-D3 24፤ በጅቡቲ ጉዳይ የኢትዮጵያ ፖ.ሊሲዎች አስመልክቶ የወጭ ጉዳይ መግለጫ፡ እ.ኤ.አ. ሚያዝያ 30፤ 1976። ውጉሚ:- ጅቡቲ 49-D3 4፤ በአዲስ አበባ ከጉሌድ ጋር የተሰጠ የጋራ መግለጫ፡ እኤአ ሰኔ 22፣ 1976





ዝግጁነት እንዲሁም በጊዜው በግዛቱ የነበረውን ወደ ሞቃዲሾ ያዘነበለ ስሜት ለማክሸፍ ወዘተ በማቀድ የተላለፈ የሥራ መመሪያ ነበር። በደርግ ባለልጣናት በኩል ለጅቡቲ የተሰጠውን ትኩረት እንደሚያመላክተው የግዛቱ ሁኔታ በኢኮኖሚ፣ ስትራቴጂና በፖለቲካ መስክ ከወቅቱ የኤርትራ ችግር ጋር በእኩልነት ደረጃ የሚታይ ተደረጎ ተመደበ።[87]

የዚህ የፖ.ሊሲ መመሪያ መሠረታዊ ነጥብ ኢትዮጵያ ልትወስዳቸው የምትችላቸውን እርምጃዎች በጊዜው ካልወሰደች በቅርብ ጊዜ ውስጥ በጅቡቲ ያለቀለት ሁኔታ ሊገጥማት እንደሚችል መገመቱ ነው። ይህ ፍራቻ በተለይ የግዛቱ ህዝብ ወኪሎች በድምፅ ብልጫም ይሁን በኃይል ተዕፅኖ ከሶማሊያ የመቀላቀሉን ዕቅድ የሚያራምዱ መሪዎች ሥልጣን እንዲይዙ ቢወስኑ የሚፈጠረውን አደጋ ታሳቢ ያደረገ ነበር። በዚህ መልክ ያለቀለት ሁኔታ ያጋጠመ እንደሆን በኢትዮጵያ በኩል ሊኖር የሚችለው ብቸኛ ምርጫ ሁኔታውን በቀጥታ በጦር ኃይል መቋቋም ይሆናል። በተለይ ሶማሊያ ቀድማ ወደ ጅቡቲ የጦር ኃይሏን ካስገባች በኢትዮጵያ በኩል ይህንን ወታደራዊ እርምጃ መቀልበሱ በፖለቲካ በኩል አስቸጋሪ ሁኔታን ከመፍጠሩም በላይ የኤርትራ ችግር እስከቀጠለና በኢጋዴን ግንባር ሥጋት እስካለ ድረስ የኃይል እርምጃው እንደማያስተማምን ታመነ።

ይልቁንስ ወታደራዊ ፍጥጫው የመጨረሻው አማራጭ ሆኖ ከዚህ በፊት ለኢትዮጵያ የሚበጁ ሌሎች የድርጊት አቅጣጫዎች ተነደፉ። እነዚህም አቅጣጫዎች የሶማሊያን ዓላማ የሚቃወሙ ክፍሎችን በመደገፍና በማጠንከር የጅቡቲ የውስጥ ፖለቲካ ሂደት ወደ ሶማሊያ ፍላጎት እንዳያመራና ከሶማሊያ ጋር ለመቀላቀል የሚፈልጉ ወገኖች ሥልጣን እንዳያገኙ መከላከል፤ በተዘዋዋሪ መንገድ ሶማሊያ የሚደግፏትን ክፍሎች (በምርጫ ወይም ይህ ካልተሳካ ከግዛቱ ነፃነት በኋላ በመፈንቀለ መንግሥት)

[87] ውጉሚ:- ጅቡቲ 54-D3፤ የሚኒስትሮች ኮሚቴ ሪፖርትና የፖ.ሊሲ መመሪያ፡ ታህሳሥ 16፣ 1969

ሥልጣን ላይ ለማውጣት ብትፈልግ ይህን ለመቋቋም እንዲቻል ኢትዮጵያም በጅቡቲ ውስጥ ተመሳሳይ ፖለቲካዊና ወታደራዊ ድርጅት ያላቸው ኃይሎች እንዲኖሩት ማድረግን ያካትታል። በተጨማሪም ሶማሊያ በተዘዋዋሪ መንገድ ዓላማዋን ከግብ ለማድረስ እንደማትችል ተገንዝባ ወታደራዊ ጣልቃ ገብነትን ለመተግበር ብትፈልግ ኢትዮጵያ አፀፋዊ እርምጃ ለመውሰድ እንደምትገደድ ሶማሊያ በማያጠራጥር ሁኔታ እንድታውቀው ማድረግ እንደሚያስፈልግ ተወሰነ። ይህንንም ለማረጋገጥ ሲባል የሃገሪቱ የጦር ኃይሎች በአፋጣኝ እንዲደራጁና ዝግጁነታቸውንም ሶማሊያ በቅድሚያ እንድትረዳ እንዲደረግ ተወሰነ።

እነዚህ እርምጃዎች ኢትዮጵያ በጅቡቲ ያለቀለት ሁኔታ እንዳያጋጥማት እንደሚያስችሉ ታመነባቸው። ከአጠቃላይ የጅቡቲ ጉዳይ አስጊነትና አስቸኳይነት በመነሳትም የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅም በአስተማማኝ ለመጠበቅ እንዲቻል አስፈላጊውን የገንዘብ መስዋዕትነት የመክፈሉ ግዴታ ታመነበት። አጠቃላይ ሃገሪቱ በጂቡቲ የምትከተለው ይህ ፖሊሲ "እያደገ የሚሄድ የአጸፋ ፖሊሲ" (policy of graduated response) ተብሎ ተሰየመ።

ይህንን ፖሊሲ ከመተግበር አኳያ የመጀመሪያው አማራጭ በጅቡቲ ፖለቲካ ውስጥ የሶማሊያን ዓላማ የሚቃወሙ ክፍሎችን መለየት፣ ማደራጀትና መርዳት ነበር። በግዛቱ ከነበሩ የፖለቲካ ፓርቲዎች መካከልም ዩኒ (U.N.I.) እና ኤም.ፒ.ኤል ለዚህ ሥራ ታጩ። የዩኒን እንቅስቃሴ በቅርበት እንዲከታተል ጅቡቲ ተልኮ የነበረ ቡድን ባቀረበው ሪፖርት መሠረት ፓርቲው 90 በመቶ የአፋሮች ድጋፍ የነበረውና ብዙ ተከታዮችም ያፈራ ቢሆንም የተቀናጀ ድጋፍ ባለማግኘቱ የተዳከመና ሶማሊያ በኤል.ፒ.ኤ.አይ. በኩል የምታደርገውን ግፊት ለመቋቋም የማይችልበት ደረጃ ደርሶ ነበር።

በጊዜው ዩኒ ከኢትዮጵያ ሰፊና አስቸኳይ ዕርዳታ ጠይቆ ስለነበር እስከ ጅቡቲ ነፃነት የሚዘልቅ የዕርዳታ ፕሮግራም ተነደፈ። ድጋፉ ፓርቲው የፖለቲካ ድርጅቱን የሚያጠናክርበትና





የሚስፋፋበት፣ በምርጫው ውድድር ወቅት የሚጠቀምበትና የምርጫውን አካሄድ በተጽዕኖው ሥር የሚያውልበት በሦስት ዙር የሚደርሰው 6,000,000 ብር የሚያወጣ የዕርዳታ ፕሮግራም ነበር። አብዛኛው ዕርዳታ በገንዘብ ሳይሆን በዕቃ ሆኖ እነኚህ ዕቃዎች በከፊል ከኢትዮጵያ የሚገኙ እንዲሆን ታቀደ። ከዚህ ቀደም በዩኒ ጥያቄ ድርጅቱንና የአፋሩን ህዝብ እንዲከላከሉ በኢትዮጵያ መንግሥት በውትድርና ሞያ ሰልጥነው በጅቡቲ ከተሠማሩት 131 ወጣቶች በተጨማሪም እስከ 600 የሚደርሱ የአፋር ወጣቶችን በውትድርና ለማሰልጠን አስፈላጊው ዝግጅት ተደረገ።

ኤም.ፒ.ኤል. (Mouvement Populaire Djiboutien — M.P.L.) የሶሺያሊስት አቋም ባላቸው የአፋር ወጣቶች በ1968 የተቋቋመ ሲሆን ከጥቂት የጅቡቲ ከተማ ነዋሪዎች በስተቀር ብዙም ድጋፍ ያልነበረው ፓርቲ ነበር። ድርጅቱ ከላይ ለተጠቀሰው ዓላማ ሲታጭ እስከ ግዛቱ ነፃነት ድረስ በቀረው ጊዜ ውስጥ ከፍ ያለ የፖለቲካ አስተዋጽኦ ያደርጋል ተብሎ አልነበረም። ይልቁንም ሁኔታው ከተረጋጋ በኋላ ለዘለቄታው በነፃይቱ ጅቡቲ ውስጥ ከኅብረተሰባዊት ኢትዮጵያ ጋር ለመተባበር የሚችል ቡድን ስለነበር እንጂ። የተነደፈው የዕርዳታ መርሐ ግብር እንደሚያመለክተው ድርጅቱ በጠየቀው መሠረት የረጅም ጊዜ ዓላማውን ለማደርጀት ለመሪዎቹና ለካድሬዎቹ የትምህርት ዕድል እንዲሰጥ፤ በአጭር ጊዜ ደግሞ ለአሥር ካድሬዎች በየካቲት 66 ትምህርት ቤት የፖለቲካ ትምህርትና የውትድርና ኮርስ እንዲሰጣቸው ተወሰነ። ለዚህም ማስፈፀሚያ አስፈላጊው በጀት ተያዘ።[88]

በተያያዘም የእነዚህን ፖሊሲዎች አተገባበር የሚከታተል ከፍተኛ የአስፈጻሚዎች ኮሚቴ ተቋቋመ። ኮሚቴው ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ሁለት፣ ከአገር መከላከያ ሚኒስቴር እና ከአገር አስተዳደር ሚኒስቴሮች አንድ አንድ እንዲሁም

88 ዝኒ ከማሁ

ከካቢኔ ልዩ መምሪያ ሁለት ተወካዮችን በማካተት ተዋቀረ። ቡድኑ ተጠሪነቱ ለሚኒስትሮች ኮሚቴ ሆኖ በጅቡቲ ጉዳይ ላይ በማዕከላዊ መንግሥትም ሆነ በጠረፍ አውራጃዎች የሚደረጉ እንቅስቃሴዎችን እንዲከታተልና እንዲያቀናጅ ኃላፊነት ተሰጠው።[89]

ቅድሚያ የተሰጠው የድርጊት መርሐ-ግብር መጪውን የጅቡቲ ምርጫ ለኢትዮጵያ ፍላጎት ተስማሚ በሆነ አካላት ተዕዕኖ ሥር እንዲሆን ማስቻል ነበር። በተለይም የአፋሩ ጎሳ በምርጫው በስፋት እንዲሳተፍ ማድረጉ ይህንን ዕቅድ የማስፈጸሚያ ዋነኛ መሳሪያ ተደርጎ ተወሰደ። "ፕሮጀክት አቃቂ" የዚህ ውጥን ተግባራዊ መገለጫ ነበር። የፕሮጀክቱ ዓላማ በጥር ወር 10,000 የኢትዮጵያ አፋሮችን ወደ ጅቡቲ በማስገባት የምርጫ መታወቂያ ካርድ እንዲወስዱ ማድረግ ነበር።

ዝርዝር ፕሮግራሙ እንደሚያመለክተው 1,000 አፋሮች ከአሰብ ወደ ሙላሒሌ በእግር ተጉዘው ወደ አቦክ የምርጫ ቀበሌ ይገባሉ፣ 4,000 ከአውሳ በዳደቶ በኩል በመኪና ጠረፍ ከደረሱ በኋላ እነሱም ወደ አቦክ ያቀናሉ፣ 2,000ዎቹ ከገዋኔ እስከ አሳይታ በመኪና ከዚያም ወደ አፋምቦ በእግር ተጉዘው ወደ ዲኪል ምርጫ ጣቢያ የሚገቡ ሲሆን ቀሪዎቹ 3,000 አፋሮች ከሚሌ፣ ከሎጊያና ከኤሊዳሬ ወደ በልሆና ዳይሞሌ መቃረቢያ ድረስ በመኪና ከተጓጓዙ በኋላ ወደ ታጁራ ቀበሌ እንዲገቡ ተደረገ። አፋሮቹ በሚንቀሳቀሱበት ጊዜ አደጋ እንዳይደርስባቸው በኢትዮጵያ ጦር ኃይሎች አስፈላጊው ጥበቃ የተደረገላቸው

---

አትመው (ከአገር አስተዳደር ሚኒስቴር)፣ እና አቶ ተወልደብርሃን ታዕዛዝ (ገንዘብ ያኸር)ና መ/አ አንዳርጌ ብርሃኔ ከካቢኔ ልዩ መምሪያ ነበሩ.

[89] ውጉማ፡- ጅቡቲ 52-D3 8፤ የአስፈጻሚ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት መመሪያ፡ የካቲት 15፣ 1969። የኮሚቴው አባላት አቶ ወሰን በሻህ (ከውጉሚ-ሊቀ መንበር)፣ አቶ ዓለማየሁ መኮንን (ከውጉሚ-ጸሐፊ)፣ ሌ/ኮሎኔል ዓለሙ ጥበቡ (ከአገር መከላከያ ሚኒስቴር)፣ ኮሎኔል ተስፋዬ

[90] ውጉማ፡- ጅቡቲ 54-D3 24፤ ብርሃኑ ዲንቃ (ውጉሚ- አፍሪካ መምሪያ ኃላፊ) ለክ/ል ዶ/ር ፈለቀ ገድለ ጊዮርጊስ (ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር) ስለ ፕሮጀክት አቃቂ የቀረበ ማስታወሻ፡ ታህሳሥ 21፣ 1969





ሲሆን ጅቡቲ ሲገቡም ችግር እንዳያጋጥማቸው ለዩኒ ፓርቲ ተወካዮች በጅቡቲ ቆንስል በኩል መመሪያ ተላለፈ። አጠቃላይ ፕሮጀክቱ ወደ 150,000 ብር ወጪ ጠየቀ።[90]

በዚህ መሐል የኢትዮጵያን ጥረት ያቀዘቀዘ ክስተት ተፈጠረ። የጅቡቲን ነፃነት ታሳቢ ያደረገና በቀጣይነት የሚመሠረተውን ፓርላማ አወቃቀር ለመወሰን ፈረንሳይ በመጋቢት 1969 በፓሪስ የግዛቲን ፓርቲዎች ያሳተፈ ስብሰባ አዘጋጀች። በስብሰባው ከተሳታፊ ወገኖች ጋር በሂደቱ ዙሪያ ስምምነት ላይ ከመድረስም ባሻገር ስለ አፈፃፀሙ ውሳኔ እንዲተላለፍ አደረገች። በዚህ ስብሰባ አብዛኛዎቹ የኢሳ-ሶማሌ ፓርቲዎች እና በካሚል የሚመራው የጅቡቲ አስተዳደር ተካፋይ የነበሩና ውሳኔውን የተቀበሉ ሲሆን ዋነኞቹ የአፋር ፓርቲዎች (በተለይ ዩኒ፣ ኤም.ፒ.ኤል እና ኤም.ኤል.ዲ.) በኢትዮጵያ መንግሥት ገፋፊነት በፓሪሱ ስብሰባ ሳይሳተፉ ቀሩ።

ይህ የኢትዮጵያ ውሳኔ ከመነሻው ከአንዳንድ የአገሪቱ ዲፕሎማቶች ተቃውሞ ገጥሞት የነበረና ሊያስከትል የሚችለው አሉታዊ ተፅዕኖ የተዘረዘረ ቢሆንም ተግባራዊ ተደረገ። የዚህ ውጤት የፓሪሱ ስብሰባ ተሳታፊዎች ከአፋር ፓርቲዎች ጋር በቀጣዩ የግዛቱ መንግሥት አወቃቀር ዙሪያ ለመደራደር ፈቃደኛ ሳይሆኑ ቀሩ። የፓሪሱ ስምምነት ህዝበ-ውሳኔው ሚያዝያ 30፣ 1969 እንዲካሄድ ከመወሰኑም ባሻገር አዲሱ የጅቡቲ ምክር ቤት ስልሳ አምስት መቀመጫ እንዲኖረው ተደረገ። በአምስት በተከፈለው የምርጫ ክልል ድልድል መሠረትም አፋሮች 29፣ ሶማሌዎች 3፣ አረቦች 2 እና ኢሳዎች 31 ወንበር ይኖራቸዋል።[91]

በኢትዮጵያ ገፋፊነት የአፋር ፓርቲዎች የተሳተፉበት ቀጣይ ስብሰባ በጋና አክራ ተደረገ። ዋነኛው የድርድር ነጥብ አፋሮች ያቀረቡት፡ በምክር ቤቱ ከኢሳዎች እኩል 31 መቀመጫ

---

[91] Shehim and Searing, 219-222. Kadamy, 512-513.

እንዲኖራቸው የሚጠይቀው ሃሳብ ነበር። ሆኖም የአክራው ድርድር የፓሪሱን ስምምነት ሊለውጥ አልቻለም። ከአክራ መልስም በኢትዮጵያ ገፋፊነት አፋሮቹና ኢሳዎቹ በወንበር ክፍፍሉ ዙሪያ በጅቡቲ ባደረጉት ንግግር አፋሮቹ ለእኩል ውክልና መብት ቢከራከሩም በስተመጨረሻ ሐሰን ጉሌድ ባቀረቡት ማስታረቂያ ሃሳብ መሠረት አፋሮቹ 30 መቀመጫ እንዲይዙ በደርግ በኩል ተፈቀደ።

ከሁሉም በላይ አደጋ ያስከተለው አፋሮች በአብደላ ካሚል፣ አህመድ ዲኒ እና በርከት ጉሌድ በሚመሩ የጎሳ መዋቅሮች መከፋፈላቸው ሲሆን በተቃራኒው በተለይ በሐሰን ጉሌድ ፕሬዚደንትነት የሚመራው የኢሳ-ሶማሌ ጥምረት (L.P.A.I.) ጠንካራ የፓርቲ መዋቅር መመሥረት መቻሉ ነበር። አብደላ ካሚል በጊዜያዊነት የአፋር ፓርቲዎችን ውህደት መፍጠር ችሎ የነበረ ቢሆንም ከሥልጣን ጥማቱ የተነሳ በጅቡቲ ምክር ቤት ምርጫ ወቅት ለአፋሮች የተሰጠውን 30 መቀመጫ በፓርቲ መዋቅር ሳይሆን ለግል ፍላጎቱ በሚያመች መልኩ በጎሳ ተዋረድ እንዲከፋፈል አደረገ።

ከሁሉም የከፋው በአፋር ፖለቲከኞች መካከል የተከሰተውን ምስቅልቅል ተከትሎ በኢትዮጵያ ይደገፉ የነበሩት ዩኒ እና ኤም.ፒ.ኤል ፓርቲዎች በምክር ቤት ምርጫው ሳይሳተፉ መቅረታቸው ነበር። ይህንንም ተከትሎ በምክር ቤቱም ሆነ በመንግስቱ አስተዳደር ውስጥም ተወካይ ሳይኖራቸው ቀረ። ይህ በአዲሱ ምክር ቤት የአፋሮቹን ተሰሚነት ከመቀነሱም በላይ በጉሌድ የተመራው የኢሳ-ሶማሌ-አረብ ጥምረት (ኤል.ፒ.ኤ.አይ.) አጠቃላይ አብላጫ እንዲቆጣጠር አስቻለው። ይህንን ተከትሎም ወደ አፋሮች ያዘነብል የነበረው የኢትዮጵያ የፖሊሲ አቅጣጫ

[92] ውጉሚ፡- ጅቡቲ 51-D3 3፤ ኮማንደር ሙሳ ያሲን (በጅቡቲ ምክትል ዋና ቆንስል) ለኮ/ል ዶ/ር ፈለቀ ገድለ ጊዮርጊስ - በፓሪስ እና አክራ ስብሰባዎች ውጤት ዙሪያ የቀረበ የግምገማ ሪፖርት፡ እ.ኤ.አ. መጋቢት 29፣1977። ውጉሚ፡- የጅቡቲ ሁኔታ ሪፖርት 9 2፤ ኮማንደር ሙሳ ለኮ/ል ዶ/ር ፈለቀ፡ ሚያዝያ 14፤ 1969፤ ኮ/ል ዶ/ር ፈለቀ ለሙሳ፡ ሚያዝያ 18፣ 1969





አደጋ ተጋረጠበት። ለሃገራቱ ብቸኛ መፅናኛ የነበረው በአጠቃላይ የስምምነትና የምርጫ ሂደቱ በሶማሊያ መንግስት እና በሐሰን ጉሌድ ፓርቲ (L.P.A.I.) መካከል የተፈጠረው አለመግባባትና የዓላማ ልዩነት ነበር።[92]

ሚያዝያ 30 በተደረገው የጅቡቲ ሪፈረንደም 98 በመቶ የሚሆነው የግዛቱ ህዝብ ነፃነትን መረጠ። በምክር ቤቱ ምርጫም በሙሴ ሐሰን ጉሌድ የሚመራው ፓርቲ አብላጫውን መቀመጫ አገኘ። ጅቡቲ ሰኔ 20፣ 1969 (29 June 1977) ነፃነቷን እንድትቀዳጅም ቀን ተቆረጠ። ይህንን ተከትሎ ቀጣዩ የኢትዮጵያ ጥረት በአዲሱ የጉሌድ ካቢኔ ውስጥ የዩኒና ሌሎችም የአፋር ፖለቲከኞች ውክልና እንዲኖራቸው ማድረጉ ላይ አተኮረ። የአገራቱ የአጭር ጊዜ የፖሊሲ አቅጣጫ ከጉሌድና ከመንግስታቸው ጋር የቅርብ ግንኙነት ማድረግና በሁለቱ አገሮች መካከል ያለው የኢኮኖሚ፣ የንግድና የባህል ግንኙነት እንዲስፋፋና እንዲጠነክር ማድረግ ሆነ። በረጅም ጊዜ ደግሞ ሶማሊያ ጅቡቲን እንዳትይዝ ማድረግና የግዛቱ ነፃነት ዘላቂ እና አንድነቱ የተጠበቀ እንዲሆን ተወሰነ። ለዚህም እንዲያገለግል በተለይ የአፋሩን ወገን እና ከሶማሊያ መቀላቀልን የሚቃወሙ የኢሳ ፖለቲከኞችን ማደራጀት ዋና ዓላማ መሆን እንደሚኖርበት ተመከረ።[93]

ኢትዮጵያ ሰኔ 20 ነፃ መንግስት በሚሆነው ጅቡቲ ዙሪያ ልትከተለው ስለሚገባው በአጠቃላይ ፖሊሲ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ግንቦት 16 ቀን 1969 ስብሰባ አደረገ። በዚህ ወቅት መፃኢው የኢትዮ-ጅቡቲ ግንኙነት የሁለቱንም አገሮች ጥቅም በሚያስከብር ሁኔታ ሊመሠረት እንደሚገባ ግንዛቤ ተወሰደ። ስብሰባው ጅቡቲን በተመለከተ በማናቸውም ጉዳይ የሚደረገውን እንቅስቃሴ እንዲያስተባብር ቀድሞ ለተመሠረተው ለአስፈፃሚዎች ኮሚቴ የበለጠ ኃላፊነት ሰጠ። ይህንኑ ኮሚቴ

[93] ውጉሚ፡- የጅቡቲ ሁኔታ ሪፖርት 9 2፤ ቆንስል ዶ/ር ፍትጉ ለኮ/ል ዶ/ር ፈለቀ፡ ግንቦት 16፣ 1969

ለማጠናከር በማሰብም የግዛቱ የወደፊት ሁኔታ በይበልጥ ከሚመለከታቸው ከትራንስፖርትና መገናኛ እንዲሁም ከንግድና ቱሪዝም ሚኒስትሮች የተውጣጡ ኤክስፐርቶች ተጨመሩለት።

በከፍተኛው የሚኒስትሮች ኮሚቴ በሚሰጠው ውሳኔና መመሪያ መሠረትም የአስፈፃሚው ኮሚቴ በኅብረተሰብአዊት ኢትዮጵያና በአዲሲቱ ጅቡቲ መካከል በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚ፣ በንግድና በመሳሰለው ሊኖር ስለሚገባው ግንኙነት ለውሳኔ የሚረዳ ሃሳብ እንዲያቀርብ፤ ኢትዮጵያ በጅቡቲ ያላት ጥቅም የሚጠበቅበትን ሁኔታ በማጥናት ሃሳብና አስተያየት እያቀረበ በማስወሰን ይኸው በሥራ ላይ መዋሉን እንዲከታተል፤ እና ስለ ሁለቱ አገሮች ግንኙነት በጅቡቲ መንግስት በኩል የሚኖረውን አስተያየት በመከታተል በየጊዜው ሊወሰድ ስለሚገባው እርምጃ ሃሳብ እያቀረበ አፈፃፀሙን እንዲከታተል ኃላፊነት ተሰጠው። አስፈፃሚ ኮሚቴው በኢትዮጵያና በጅቡቲ መካከል ስላለው የምድር ባቡርና የወደብ አጠቃቀም መብት ዙሪያ እና ከጅቡቲ መንግስትና ከፈረንሳይ መንግስት ጋር በነዚህ መብቶች ዙሪያ በተናጠል ለሚደረጉ ድርድሮች መንደርደሪያ ሃሳቦች እንዲያዘጋጅ ታዘዘ።

በተጨማሪም ከባድ ዕቃዎችን፣ የጦር መሳሪያዎችን እና የመሳሰሉትን በማስመጣት ረገድ በጅቡቲ ወደብ ላይ ብቻ ያለውን ጥገኝነት ለመቀነስ እንዲቻል በአሰብ ወደብ በይበልጥ ለመጠቀም አስፈላጊው ዝግጅት እንዲደረግ ለትራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስቴር ትዕዛዝ ተላለፈ። ከአዲሱ የጅቡቲ መንግስት ጋርም ለሁለት ዓመት የንግድ ስምምነት ለማድረግ በታቀደው

[94] ውጉሚ፦ ጅቡቲ ልዩ ልዩ ፋይሎች 2 1፤ ኃይሉ ይመኑ (የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሰብሳቢ ጽ/ቤት ተቀዳሚ ሚኒስትር) ከ/ል ዶ/ር ፈለቀ ገድለ ጊዮርጊስ፡ ግንቦት 19፣ 1969፤ ከ/ል ዶ/ር ፈለቀ ገድለ ጊዮርጊስ ለአስፈፃሚ ኮሚቴ፡ ግንቦት 22፣ 1969፤ ከ/ል ዶ/ር ፈለቀ ገድለ ጊዮርጊስ ለአቶ ዘውዴ አበፋው (የእርሻና የህዝብ ማስፈር ሚኒስትር) እና ለአቶ ተስፋዬ ዲንቃ (የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ቋሚ ተጠሪ)፡ ግንቦት 24፣ 1969፤ ተስፋዬ ዲንቃ ከ/ል ዶ/ር ፈለቀ፡ ሰኔ 14፣ 1969





መሠረት የሚመለከታቸው አካላት በኢትዮጵያ በኩል ሊቀርቡ ስለሚችሉ የእርሻ ምርቶችና የኢንዱስትሪ ውጤቶች ዝርዝር መረጃ እንዲያቀርቡ ተደረገ። በሃገሪቱ ያለው ምርት ለራስ ፍጆታ እንደማይበቃ ቢታመንም በኮታ ሥርዓት ለጅቡቲ የሚሆን ድርሻ እንዲዘጋጅ ተወሰነ።[94]

እነዚህ ዝግጅቶች ተግባራዊ እልባት ከማግኘታቸው በፊት ግን የጅቡቲ ነፃነት ቀን ሰኔ 20 ደረሰ። በደርግ መንግስት በኩል ለጅቡቲ ነፃነት ቀን አከባበር ዝግጅት መደረጉ አልቀረም። የመጀመሪያው ለክብረ በዓሉ የሚውል የምግብ ዓይነት ተገዝቶ እንዲላክ በሌ/ኮሎኔል መንግስቱ ኃይለ ማርያም በታዘዘው መሠረት ለዚሁ የሚውል 1,000,000 ብር ወጪ ተደረገ። በዚህ አጋጣሚ በግዛቱ የኢትዮጵያን ጥቅም ሊጎዳ የሚችል ማናቸውም አይነት እንቅስቃሴ እንዳይኖርም የዩኒ እና ኤም.ፒ.ኤል. አባላት የሆኑ የአፋር ወጣቶች በጥንቃቄ ተመርጠው በጅቡቲ እንዲሰማሩ ታዘዘ፤ አስፈላጊው ትጥቅም ተሟላላቸው።[95]

በአዲሱ የሐሰን ጉሌድ መንግስት በኩል ስለ ኢትዮጵያ የነበረው አመለካከት ግን ከሚጠበቀው በታች ነበር። በተለይ ኢትዮጵያውያኑን ያስከፋቸው በክብረ በዓሉ ላይ ለነሱ የተመደበው የልዑክ መጠን ከሶማሊያ በግማሽ ያነሰ መሆኑ (15 ለ 30) እና መቀመጫውን በሶማሊያ አድርጎ የነበረው የጅቡቲ ነፃ አውጭ ግንባር (F.L.C.S.) ዓርማ የጅቡቲ ሰንደቅ እንዲሆን መወሰኑ ነው። የኢትዮጵያ መንግስት ይህንን በፅኑ የተቃወመ ሲሆን በተለይ የሰንደቁ ጉዳይ የሶማሊያን ተፅዕኖ ማየል እንደሚያመለክትና በዚህም እንደማይስማማ በግልፅ ለሐሰን ጉሌድ ተነገራቸው። ጉዳዩ በአስቸኳይ ካልተስተካከለም በኢትዮጵያና በጅቡቲ ግንኙነት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እንደሚያሳድር፤ ኢትዮጵያም የጅቡቲን

[95] ውጉሚ፦ ጅቡቲ 51-D3 3፤ ከ/ል ዶ/ር ፈለቀ ለሌ/ኮ መንግስቱ፡ ሰኔ 1፣ 1969፤ ቆንስል ዶ/ር ፍቅሩ ለወሰን በሻህ (የአስፈፃሚ ኮሚቴ ሊቀ መንበር)፡ ሐምሌ 6፣ 1969። ውጉሚ፦ የጅቡቲ ሁኔታ ሪፖርት 9 2፤ ብርሃኑ ዲንቃ ለቆንስል ዶ/ር ፍቅሩ፡ ሰኔ 2፣ 1969

ነፃነት የምትደግፈው የግዛቱ ነፃነት እውነተኛና ከማንኛውም ውጫዊ ተፅዕኖ የፀዳ ከሆነ ብቻ እንደሆነ ለጅቡቲው መሪ ተገለፀ::[96]

በሁለቱ አገሮች መካከል የመጀመሪያዎቹ ወራት ግንኙነት የተጠበቀውን ያክል አዎንታዊ ገፅታ አልነበረውም:: የምድር ባቡሩ መስመር ግንቦት 24፣ 1969 በሶማሊያ ሠርጎ ገቦች መሰበር፣ የዚያድ ባሬ የጅቡቲ ጉብኝትና ሊያሳድረው የሞከራቸው ፀረ-ኢትዮጵያ አቋሞች፣ የሐሰን ጉሌድ በተደጋጋሚ ኢትዮጵያን በድንበር ጥሰት መወንጀል፣ የሐምፍሬ አሊ ሚራህ በአረብ መንግስታት ድጋፍ በጅቡቲ የሚገኙ አፋሮችን ለውትድርና ዘመቻ እያዘጋጀ መሆኑ፣ በኢትዮ-ሶማሊያ ጦርነት ወቅት (1969/70) የጅቡቲ መንግስት ገለልተኛ ቢመስልም በተዘዋዋሪ ለሶማሊያ ያደላ አቋም መያዙና የሶማሊያ ጦር በግዛቱ እያለፈ ኢትዮጵያን እንዲያጠቃ መፍቀዱ፣ የወደብ ስምምነቱን በመጣስ በጅቡቲ በኩል ነዳጅ ወደ ኢትዮጵያ እንዳያልፍና በወደብ ላይ የተራገፉ ዕቃዎች እንዳይነሱ መከልከሉ፣ ፕሬዚደንት ጉሌድ ገንዘብ ፍለጋ በአረብ አገራት ያደረጉት ጉብኝት (ነሐሴ 1969) እና ከነዚህ መንግስታት በኩል ጅቡቲ ለሶማሊያ በመወገን የኢትዮጵያን ጥቅሞች እንድታጠቃ የቀረበላት ጥያቄ፣ የጉሌድ በይፋ የምዕራብ ሶማሌ ነፃ አውጭ ድርጅትን መደገፍ ወዘተ ለዚህ የጥርጣሬ መንፈስ አስተዋፅኦ አበርክተዋል:: ከዚህም ባሻገር በኢሳ-ሶማሌ የበላይነት የተያዘው የጅቡቲ ጦር ተከታታይ

---

[96] ውጉሚ:- ጅቡቲ 51-D3 3፤ ኮ/ል ዶ/ር ፈለቀ ለፕሬዚደንት ሐሰን ጉሌድ፡ ሰኔ 1969

[97] ውጉሚ:- ጅቡቲ 51-D3 3፤ ማስታወሻ ለሌ/ኮ መንግስቱ ኃይለማርያም፡ ሐምሌ 1969:: ውጉሚ:- የጅቡቲ ሁኔታ ሪፖርት 9 2፤ ኮማንደር ሙሳ ያሲን (ጅቡቲ) ለዶ/ር ፈለቀ፡ ነሐሴ 7፣ 1969፤ ዶ/ር ፈለቀ ለደርግ ጽ/ቤት፡ ቋጉሚ 3፣ 1969፤ ምንዳዬ ደሬሳ (ውጉሚ አማካሪ) ለኮማንደር ሙሳ ስለ ጅቡቲ ከሶማሊያ ወገን መቆም፡ ቋጉሚ 5፣ 1969:: Harry Ododa, "Somalia's Domestic Politics and Foreign Relations since the Ogaden War of 1977-78," in *Middle Eastern Studies,* Vol. 21, No. 3 (July 1985), 290-293.





የተጨማሪ ሥልጣን ጥያቄ እና ከአፋር ጎሳ የጦር አባላት ጋር በተደጋጋሚ የተደረጉ ግጭቶች በግዛቱ የውስጥ ጉዳይ የሶማሊያ መንግስት እጅ እየበረታ ለመምጣቱ አመላካች ተደርጎ ተወሰደ::[97]

ይህ አጣብቂኝ በኢትዮጵያ በኩል አፋጣኝ የፖሊሲ ክለሳ እንዲደረግና የመፍትሄ እርምጃ እንዲወሰድ በር ከፈተ:: የአስፈፃሚ ኮሚቴው በመስከረም ወር 1970 የመጀመሪያ ሳምንት ባደረገው አስቸኳይ ስብሰባ ከላይ የተጠቀሱትን ፀረ-ኢትዮጵያ እንቅስቃሴዎች በማጤን የፖሊሲ ሃሳቦችን አቀረበ:: የፖሊሲ ሃሳቡ የተንደረደረው ሃገሪቱ በጅቡቲ ጉዳይ ስትከተለው የነበረውን አቋም ህጸፆች በመጠቆም ነው:: ከዚህ አንፃር ሁለት መሠረታዊ ችግሮች ተነቅሰው ወጡ፡ አንደኛው የሶማሊያ የምንግዜም የመስፋፋት እቅድ ሲሆን ሁለተኛው በጅቡቲ ላይ የሚስተዋለው የምዕራባውያን (በፈረንሳይ መሪነት) እና "የአረብ አድሃሪ ኃይሎች" ተፅዕኖና ጣልቃ ገብነት ነው::[98] የዚህ ሁለንተናዊ ተፅዕኖ ውጤትም ጅቡቲ ሶማሊያ በኢትዮጵያ ላይ ለነበራት የመስፋፋት ዓላማና ለፈፀመችው ወረራ ግልፅ ተባባሪ መሆን ነው:: በሂደትም ኢትዮጵያ ስትከተለው የነበረው ፖሊሲ በጅቡቲ ውስጥ ያስገኘው ውጤት ከሶማሊያ ስኬት ጋር ሲነፃፀር ኢምንት ሆኖ ተገኘ::

በአስፈፃሚው ኮሚቴ ግንዛቤ መሠረትም በጅቡቲ መንግስት፣ አስተዳደርና የጦር ኃይል ውስጥ የሶማሊያ መንግስት ዓላማ ደጋፊዎች በብዛት መስግሰግ በግዛቱ መፈንቅለ መንግስት ለማድረግ በሶማሊያ በኩል የነበረውን ፍላጎት አመላካች ተደርጎ ተወሰደ:: ይህ እቅድ የሚፈፀም ከሆነ ደግሞ የጅቡቲ ወደ ሶማሊያ መቀላቀል በህጋዊ መንገድ የሚከናወን ያለቀለት ጉዳይ ይሆናል:: ከዚህ አንፃር ኢትዮጵያ የምትከተለው የነፃ ጅቡቲ መርህ የሶማሊያን ሴራ ለማክሸፍ ያለመ መሆን ይኖርበታል:: በኮሚቴው ግምገማ መሠረት ኢትዮጵያንና ጅቡቲን ካራራቃቸው

---

[98] J.P. Anand, "Horn of Africa: Superpowers' Manoeuvres," in *Economic and Political Weekly,* Vol. 12, No. 35 (Aug. 27, 1977), pp. 1537-1538.

ምክንያቶች መካከል ዋና ዋናዎቹ የባቡር ሐዲዱ መሰበር፣ የሐሰን ጉሌድ መንግስት በግምት ስህተትና በተፅዕኖ በምስራቅ ኢትዮጵያ የሶማሊያ ጊዜያዊ ስኬት ተታለው ከሶማሊያ ጋር መሰለፍ ነበሩ። በሌላ በኩል ደግሞ በወቅቱ በጅቡቲ የተከሰተ የሐሰን ጉሌድን መንግስት እድሜ በአጭሩ ሊቀጭ የሚችል ከባድ የኢኮኖሚ ችግር አለ። የኢትዮጵያና የጅቡቲ መራራቅ እና በጅቡቲ ያለው የኢኮኖሚ ችግር እየተባባሰ ከሄደ ኢትዮጵያ በግዛቱ ያላትን ዓላማና ብሔራዊ ጥቅም የሚፃረር ለሶማሊያ አመቺ የሆነ ሁኔታ ይፈጠራል።

ይህ እንዳይሆን ለመከላከል እቅዶች ተነደፉ። እነሱም፡ መራራቁን ለማጥበብና ብሎም ለማሻሻል በአስቸኳይ በጅቡቲ አምባሳደር መሾም ኤምባሲውንም በሰው ኃይልና በገንዘብ ማጠናከር፤ የተፈጠረውን የኢኮኖሚ ችግር ለማቃለል በጅቡቲ ጋላፊ መንገድ የሚካሄደውን የንግድ እንቅስቃሴው ባስቸኳይ ማሻሻል፤ ይህም ለጅቡቲ መንግስት የመኖር ዋስትና ሊሆን ከመቻሉም በላይ የባቡር መስመሩን በማፍረስ ሂደት የተባበረውን የኢሳውን ወገን ከንግዱ እንቅስቃሴ ውጭ በማድረግ በፈፀመው ጥፋት ተጎጂው ራሱ መሆኑን ማሳመን፤ የኢሳው ወገን ሁኔታውን ተገንዝቦ ተረድቶ ሶማሊያ የፈጠረችውን ችግር እንዲቃወም ማድረግና ለሐዲዱ ደህንነት ራሱ ዋስትና እንዲያበጅ መገፋፋት ይገኙበታል።

በተጨማሪም ሶማሊያ በጅቡቲ ያቀደችው ያሰቀለተ ሁኔታ እንዳይፈፀም ከአፋሮች ጋር ያበልጥ ማበር፣ ድጋፍና እርዳታውን መቀጠል እና ቀደም ሲል የሠለጠኑና የታጠቁት ክፍሎች እንዲዘጋጁና ነቅተው እንዲጠብቁ ማድረግ፤ እና በሶስተኛ መንግስት በኩል የጅቡቲ መሪዎች የሶማሊያን እቅድ እንዲረዱ፣ የኢኮኖሚ ችግራቸው ሊቃለል የሚችለው ከኢትዮጵያ ጋር ሲቀራረቡ ብቻ መሆኑን እንዲረዱ ለማድረግ ታቀደ። ለተግባራዊነቱም ለመነሻ የሚሆን የአንድ ሚሊዮን ብር በጀት ተፈቀደ። ከነዚህ ውጥኖች ቅድሚያ የተሰጠው የተቀዛቀዘውን የንግድ እንቅስቃሴ እንዲያንሰራራ ማድረግና በሂደቱም ኢትዮጵያ በጅቡቲ ላይ የነበራትን የኢኮኖሚ የበላይነት መልሶ ማረጋገጥ ነበር። የጋላፊ ጅቡቲ መንገድ በአስቸኳይ ተጠግኖ ዋናው የገቢና ወጪ ዕቃዎች መመላለሻ በር እንዲሆን ከመደረጉም በላይ በሂደቱ ለሚሳተፉ ከባድ የጭነት መኪናዎች የሥራ ክንውን ህጋዊ ማዕቀፍ ተዘጋጀ።[99]

በዚህ መሐል ግን በጅቡቲ ያለው የፀጥታ ሁኔታ





ከዕለት ወደ ዕለት እየተባባሰ፣ የኢሳ-ሶማሌ ጥምረት በመንግስቱ አስተዳደር ያገኘውን የበላይነት በመጠቀም በግዛቱ አፋሮችና በኢትዮጵያውያን ላይ የሚያደርሰው በደል እየከፋ መምጣቱ ተጨማሪ ውሳኔን ጠየቀ። በተከታይም የኤም.ፒ.ኤል.ን መታገድ ተከትሎ የዚህን ድርጅት እና የዩኒ ፓርቲ አባሎች ወደ ኢትዮጵያ ሸሽተው ገቡ። በግዛቱ የመንግስት መዋቅር የኢሳ ጎሳ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ወታደራዊ የበላይነቱ የተረጋገጠ ሲሆን፤ በዚህም መሠረት የፕሬዚደንትነት መንበሩና የመከላከያ ሚኒስትርነቱ ቦታ በቋሚነት የኢሳዎች ሆነ። በስልጣን ክፍፍሉ ስምምነት መሠረት የጠቅላይ ሚኒስትርነቱ ቦታ ለአፋሮች የተተወ ቢሆንም በግዛቱ የእለት ተእለት እንቅስቃሴ ውስጥ የውሳኔ ሰጭነት ሚናው እምብዛም ስላልነበር አፋሮቹን ሊያስደስት አልቻለም። አጠቃላይ ሁኔታው በመጀመሪያዎቹ ሁለት የነፃነት ዓመታት ለታየው የአፋሮች አመፅ እና ለተከታታይ የአፋር ጠቅላይ ሚኒስትሮች - አህመድ ዲኒና አብዱላህ ሞሐመድ ካሚል - በፍቃድ ከስልጣን መልቀቅም ምክንያት ሆነ።[100]

በታህሳስ 1970 የአፋር ጎሳ አባል የሆኑት የጅቡቲ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሙሴ አብደላ መሐመድ ካሚል ከፓሪስ ቆይታ ወደ አገራቸው ሲመለሱ በአዲስ አበባ በኩል አልፈው ስለጉዳዩ ከውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩና ከሊቀ መንበር መንግስቱ

---

[99] ውጉሚ፡- ጅቡቲ 51-D3፤ የአስፈፃሚ ኮሚቴ ስብሰባ ሪፖርት፡ መስከረም 3፤ 1970። ውጉሚ፡- የጅቡቲ ሁኔታ ሪፖርት 9 2፤ ሻለቃ ዳዊት ወልደጊዮርጊስ (ውጉሚ ቋሚ ተጠሪ) ለሚኒስቴር መ/ቤቶች፡ መስከረም 26፤ 1970፤ መርሻ ቀፀላ (የአገር አስተዳደር ሚኒስቴር ቋሚ ተጠሪ) ለክፍለ ሀገር አስተዳዳሪዎችና ለደህንነት ተቋማት፡ መስከረም 28፤ 1970

[100] Kassim Shehim and James Searing. "Djibouti and the Question of Afar Nationalism." In *African Affairs*. Vol. 79. No. 315 (April 1980): 209-210. Peter J. Schraeder. " Ethnic Politics in Djibouti: From 'Eye of the Hurricane' to 'Boiling Cauldron'". in *African Affairs*. Vol. 92. No. 367 (April 1993). 206-208. Kadamy. 512-513.

ጋር ሰፊ ውይይት አካሄዱ። ወገናቸውን ለመታደግም ኢትዮጵያ አፋጣኝ ወታደራዊና ፖለቲካዊ እርዳታ እንድትሰጣቸው ጠየቁ። በተለይም በጎሳቸው ላይ እየተፈፀመ የሚገኘውን በደል በመቃወም የጠቅላይ ሚኒስትር ሙሴ አህመድ ዳኒና ሌሎች አምስት የካቢኔ አባሎች ሥልጣን መልቀቅ እና አፋር የምክር ቤቱ አባላት ፓርላማውን ረግጠው መውጣታቸውን ተከትሎ በሁለቱ ዋነኛ ጎሳዎች መካከል ግጭት ሊነሳ ስለሚችል የኢትዮጵያ አፋጣኝ ድጋፍ አስፈላጊ መሆኑን ገለፁ።

የአፋሮችን ደህንነት በአስተማማኝ ለመጠበቅም ከዚህ ቀደም ኢትዮጵያ ያሰለጠነቻቸው የዩኒ እና ኤም.ፒ.ኤል. ወጣቶችና ሌሎች ለተመሳሳይ ዓላማ የተዘጋጁ የኢትዮጵያ አፋር ወታደሮች ተሰብስበው በአስቸኳይ ለእርዳታ ሊደርሱ በሚችሉበት ቦታ እንዲቀመጡ፤ እና የኢሳዎችን ማንአለብኝነት ለመቀነስ እና ከአፋሮች ጀርባ አንድ ኃይል መኖሩን ተረድተው ከድርጊታቸው እንዲታቀቡ ለማድረግ የኢትዮጵያ መንግስት በምስጢር እስከ 5,000 ለሚደርሱ የጅቡቲና ኢትዮጵያ አፋሮች የሦስት ወር ወታደራዊ ስልጠና እንዲሰጥና ለግዳጅ እንዲያዘጋጅ፤ የረጅም ጊዜ እቅድ ተይዞ ደግሞ በርዕሰ ከተማዋ በጅቡቲ የአፋሮችን ቁጥር ከኢሳዎች የበለጠ ወይም እኩል ለማድረግ ወደ 50,000 የሚጠጉ የኢትዮጵያ አፋሮችን ወደ ግዛቱ ለማስረግ እንዲቻል የጅቡቲው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሊቀ መንበር መንግስቱን ጠየቁ።[101]

በጥያቄው ዙሪያ የኢትዮጵያን መልካም ፈቃድ የገለፁት ሊቀ መንበሩ ወደ አፈፃፀም ከመገባቱ በፊት በጅቡቲ በመገኘት ጉዳዩን የሚመረምር የመልዕክተኞች ቡድን ለመላክ ወሰኑ። የልዑካን ቡድኑ ከሌሎች የአፋር መሪዎች ጋር ተገናኝቶ ከኢትዮጵያ የሚፈለገው እርዳታ ዓይነትና መጠን ምን መሆን እንዳለበት በምንስ መንገድ እንደሚሰጥ እንዲነጋገር ታቀደ። በዚህም መሠረት በአቶ ብርሃኑ ዲንቃ (የአፍሪካ መምሪያ ኃላፊ)

[101] ውጉሚ፡- ጅቡቲ 51-D3፤ በጉዳዩ ዙሪያ የተዘጋጀ ማስታወሻ፡ ታህሳሥ 21፣ 1970





የሚመራ ዶ/ር አሰፋ መድኃኔና አቶ ወሰን በሻህ የሚገኙበት ቡድን ከታህሳሥ 17-24፣ 1970 በጅቡቲ በመገኘት ያለውን ሁኔታ አጥንቶ ሪፖርት አቀረበ። በተለይም ቡድኑ ከአፋር ፓርቲ ተወካዮች ጋር ባደረጋቸው ውይይቶች የጅቡቲ አፋሮች በሙሴ አሃመድ ዳኒ መሪነት አንድነት መመስረታቸውን እና ከኢትዮጵያ ጋር ለመተባበር ፈቃደኛ መሆናቸውን አረጋገጠ። ይህ የአፋሮች አንድነት ከመቼውም ጊዜ በላይ ለኢትዮጵያ ዓላማ አመቺ ሁኔታን መፍጠሩንም አሳሰበ።

የቡድኑ የማጠቃለያ አስተያየት ካቀረባቸው የውሳኔ ሃሳቦች መካከልም ለሦስት ሺ ሰዎች ትጥቅ የሚሆን ልዩ ልዩ መሣሪያና ፈንጂ በአስቸኳይ ወደ ጠረፍ ተልኮ በኢትዮጵያ ጦር ቁጥጥር ሥር እንዲቀመጥ፣ ከዚህ በፊት ከጅቡቲ ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ሰልጥነው የነበሩት 500 አፋሮች ሸሽተው ወደ ኢትዮጵያ በመግባት ላይ ስለሆኑ እነሱንና 500 ከዚህ ቀደም የሰለጠኑ ኢትዮጵያውያን አፋሮች እንዲታጠቁና እንዲዘጋጁ፣ ከጅቡቲ በመምጣት ላይ ከሚገኙ ወጣት አፋሮችና ከኢትዮጵያውያን የተውጣጡ ከ4,000-5,000 የሚሆኑ ሰዎች በሚቀጥሉት ሦስት ወራት በውትድርና ትምህርት እንዲሰለጥኑ፣ እና ጅቡቲ ውስጥ ግጭት ቢፈጠር እዚያ የሚኖሩትን ኢትዮጵያውያን ለማውጣት እንዲቻል አንድ ፕላን እንዲያዘጋጁ የአገር መከላከያና የመገናኛ ሚኒስቴሮች እንዲታዘዙ የሚሉት ይገኙበታል።[102]

ከላይ በቀረቡ ጥያቄዎች መሠረትም የኢትዮጵያ ወታደሮች በጅቡቲ ድንበር አከባቢ ንቅናቄ ያደረጉ ሲሆን ዋነኛ ዓላማውም በግዛቱ ላሉት አፋሮች የሞራል ድጋፍ ለመስጠት ነበር። ለአፋር ወጣቶችም ወታደራዊ ስልጠናው እና የመሳሪያ አቅርቦቱ ተጠናክሮ ቀጠለ። አጠቃላይ ግፊቱ ከፈጠረው ተፅዕኖ ባሻገር የጅቡቲ አፋር ፖለቲከኞች በጉሌድ ላይ ባሳደሩት ጫና የተነሳ በአብደላ ካሚል ጠቅላይ ሚኒስትርነት የሚመራ አፋሮች የሚበዙበት መንግስት ተመሠረተ።[103]

በተለይ ከሶማሊያ ወረራ መቀልበስ በኋላ በጉሌድ

[102] ዝኒ ከማሁ

[103] ውጉሚ፡- ጅቡቲ 51-D3፤ኮማንደር ሞሳ ለብርሃኑ ዲንቃ፡ ጥር 2 እና 24፣ 1970፤ ኮማንደር ሙሳ ለዶ/ር ፈለቀ፡ ጥር 29፣ 1970

መንግስት ላይ የደረሰው የሞራል ውድቀት እና የውስጥ መከፋፈል ለኢትዮጵያ ሌላኛው ድል ነበር:: ይህን ተከትሎ የተወሰደው የኢትዮጵያ የዲፕሎማሲና ፖለቲካ የትግል መስመር ካተኮረባቸው ግቦች መካከል ዋነኞቹ፤ የጉሌድ መንግስት ከግትር ብሔረተኝነት ወጥቶ ለአፋሮች ተገቢ መብታቸውን በማጎናጸፍ የውስጥ ፖለቲካውን እንዲያረጋጋ፣ የውጭ ፖለቲካውን በፍፁም ገለልተኛነት ላይ እንዲመሰርት፣ በጅቡቲና በኢትዮጵያ መካከል ያለው የንግድ ልውውጥ እንዲዳብር አመቺ ሁኔታ እንዲፈጠር፣ እና በባቡር ሐዲዱና በጅቡቲ ወደብ በኩል የሚተላለፈው የኢትዮጵያ የውጭ ንግድ አለምንም እክል በጋራ ተጠቃሚነት መርህ እንዲካሄድ ማስቻል ነበር:: ለዚህም በኢትዮጵያ በኩል እንደ መሳሪያ የተጠቀመችው በአህመድ ዲኒ አህመድ መሪነት የተመሠረተውን የአፋሮች አንድነት ነው:: ይህን ቡድን በገንዘብ ለማጠናከር ሲባልም በአፍሪካ እና አውሮፓ እየተዘዋወረ ለሚያከናውናቸው የፖለቲካ እንቅስቃሴዎች የሚውል ተጨማሪ 100,000 ብር ተመደበለት::[104]

ሶማሊያ በጅቡቲ ታደርገው የነበረውን ጣልቃ ገብነት ለዘለቄታው ለማክሸፍ ታስቦም በደወሌ አከባቢ ያለው የኢትዮጵያ ጦር እንዲጠናከርና በአቅራቢያው ባሉ የሶማሌ ወታደሮች ላይ ድብደባ እንዲፈፀም ተደረገ:: በግንቦት ወር 1970 ሊቀ መንበር መንግስቱ ሞቃዲሾ ጅቡቲን ብትወር ኢትዮጵያን ለዳግም ጦርነት መጋበዝ መሆኑን በይፋ አስታወቁ:: የአፋር ታጣቂዎች በተመረጡ የጅቡቲ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ተቋሞች ላይ አደጋ እንዲያደርሱ ተደረገ:: ለጅቡቲ መንግስት ይሠራሉ ተብለው የተጠረጠሩ ፈረንሳዊያንም በተለያየ ጊዜ

[104] ውጉሚ፡- ጅቡቲ 52-D3 5፤ ብርሃኑ ዲንቃ (አፍሪካ መምሪያ) ለኮ/ል ዶ/ር ፈለቀ፡ መጋቢት 15፣ 1970:: ውጉሚ፡- ጅቡቲ 51-D3 3፤ ማስታወሻ ለሊቀ መንበር መንግስቱ፡ መጋቢት 15፣ 1970

[105] ውጉሚ፡- ጅቡቲ 51-D3 3፤ ብርሃኑ ዲንቃ ለሻለቃ ዳዊት ወልደጊዮርጊስ (ውጉሚ ቋሚ ተጠሪ)፡ መጋቢት 15፣ 1970፤ ኮማንደር ሙሳ ለብርሃኑ ዲንቃ፡ ነሐሴ 17፣ 1970፤ ጅቡቲ ቆንስላ ለኮ/ል ዶ/ር ፈለቀ፡ ሰኔ 6፣ 1971:: አዲስ ዘመን ግንቦት 11፣ 1970:: ውጉሚ፡- የጅቡቲ





በኢትዮጵያ መንግስት በሚደገፉት የአፋር ወታደራዊ ቡድኖች ይጠለፉ ጀመር:: ከሁሉም በላይ ከጅቡቲ ተሰደው የነበሩት የኒ. እና ኤም.ፒ.ኤል. በኢትዮጵያ አደራዳሪነት በሰኔ 1971 አር.ፒ.ኤል (Rassemblement populaire pour l'progres) የተሰኘ የጋራ ግንባር ፈጠሩ:: እነኚህ እርምጃዎች ከጅቡቲና ሶማሊያ በተጨማሪ የፈረንሳይ መንግስትንም ወደ ድርድር ለማምጣት ያለሙ ነበሩ::[105]

በኢትዮጵያ በኩል አሁንም በጅቡቲ ላይ የተፈለገውን ያክል አመኔታ ሊፈጠር ስላልቻለ ተጨማሪ እርምጃዎች ተወሰዱ:: አንዱና ዋነኛው የአሰብ አውራጃ አስተዳደርን ማጠናከር ነበር:: የሚኒስትሮች ምክር ቤት ጥር 16፣ 1970 ባካሄደው ስብሰባ ላይ እንደተብራራው ይህንን እርምጃ ለመውሰድ የተፈለገው በወቅቱ አሰብ የኢትዮጵያ የወጪና ገቢ ንግድ የሚከናወንበት እና ከውጭ የመገናኛ ብቸኛ በር ስለነበር ነው:: የምፅዋ ወደብ መዘጋትና የአዲስ አበባ ጅቡቲ የባቡር መስመር መቋረጥ፤ የአሰብን ወደብ፣ የነዳጅ ማጣሪያውንና ሌሎችንም የኢኮኖሚ አውታሮች ከውጭ ጠላትና ከኤርትራ አማፅያን ጥቃት ለመጠበቅ፤ ከኤርትራ ክፍለ ሀገር ርዕሰ ከተማ ሆኖ አሰብን ማስተዳደሩ አስቸጋሪ እየሆነ መምጣቱ ወዘተ አስተዳደራዊ ለውጥ እንዲደረግ ምክንያት ነበሩ:: ስለሆነም ወደቡ የሚገኝበትን አውራጃ አስተዳደር በማሻሻልና በማጠናከር ተገቢውን አገልግሎት ለማግኘት ሲባል የአሰብ አውራጃን በማዕከላዊ መንግስት መዋቅር ስር ማድረግ አስፈለገ::

የውሳኔው ዋነኛ ነጥቦች የአሰብ አውራጃ አስተዳደር በጊዜያዊነት መልክ ተጠሪነቱ በቀጥታ ለማዕከላዊ መንግስት መዋቅር እንዲሆን፤ በዚሁ መሠረት አሰብ አውራጃ የሚገኙ

ሁኔታ ሪፖርት 9 1፤ ኮማንደር ሙሳ ለብርሃኑ ዲንቃ፡ ግንቦት 19፣ 1970:: ውጉሚ፡- ጅቡቲ 51-D3 1፤ መሐመድ ኢ. ናፋ (የዩኒ. ፖለቲካ ቢሮ ዋና ጸሐፊ) ለሊቀ መንበር መንግስቱ ያቀረቡት የሥራ ሪፖርት፡ መስከረም 24፣ 1972:: Jeff Crisp, "The Politics of Repatriation: Ethiopian Refugees in Djibouti, 1977-83," in ,*Review of African Political Economy*, No. 30 (Sept. 1984), 75.

የመንግስት መስሪያ ቤቶችና ድርጅቶች ቅርንጫፎች ተጠሪነታቸው ለጊዜው በቀጥታ አዲስ አበባ ለሚገኙት ለሚመለከታቸው ሚኒስትሮች ወይም ድርጅቶች እንዲሆን፣ ቅርንጫፍ የሌላቸውም እንደአስፈላጊነቱ እንዲያቋቁሙ፤ እና በዚህ ውሳኔ መሠረት የአሰብ አውራጃ ቅርንጫፍ መስሪያ ቤቶቻቸውን ለማጠናከር አስፈላጊው በጀትና የሰው ኃይል እንዲመደብ ተደረገ። የአውራጃውን አስተዳደራዊ አቋም ይበልጥ ለማጠናከር ሲባልም የአውራጃው የአብዮት ዘመቻ አስተባባሪ ኮሚቴ የክፍለ ሀገር አቻውን ሥልጣንና ተግባር ደርቦ እንዲሰራ፣ ለኮሚቴው ሰብሳቢነትም ቋሚ የደርግ አባል እንዲመደብና ተጠሪነቱም በቀጥታ ለማዕከላዊ ዕዝ እንዲሆን ተወሰነ። በጉዳዩ ላይ ንግግር በተደረገበት ወቅት በግልፅ የተብራራው ነጥብ ይህ ውሳኔ በኢትዮጵያ አፋሮች ቀርቦ የነበረውን የአፋር ህዝብ ክፍለ ሀገር የመመስረት ጥያቄ ጋር በፍፁም ግንኙነት የሌለው መሆኑ ነው።[106]

በተያያዘም ሰኔ 22፣ 1970 ሊቀ መንበር መንግስቱ በተገኙበት በተካሄደ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ስብሰባ የአሰብ ትራንስፖርት ልዩ ኮሚቴ የተሰኘ መዋቅር ተጠሪነቱ ለብሔራዊ አብዮታዊ ዘመቻ መምሪያ ሆኖ በአዋጅ ተቋቋመ። በመሐል አገር የተከሰተው የሸቀጣ ሸቀጥ እጥረት እና በአሰብ ወደብ የነበረው ከፍተኛ ክምችት ለትራንስፖርት ልዩ ኮሚቴው መቋቋም ዋነኛው ምክንያት ነበር።[107] በዚህ መካከል ግን የአሰብ ወደብ በመጣበቡ ምክንያት የተፈለገውን ውጤት ሊሰጥ ባለመቻሉ በጅቡቲ ወደብና በጅቡቲ-ጋላፊ መንገድ በይበልጥ መጠቀሙ አማራጭ የሌለው መሆኑ ስለታመነበት በጉዳዩ ዙሪያ ከጅቡቲ ባለስልጣናት ጋር የሚነጋገር ከፍተኛ የልዑካን ቡድን መላኩ ግድ ሆኖ ነበር።[108]

[106] ውጉሚ፦ ኢትዮ-ጅቡቲ ወደብ አጠቃቀም 1 1፤ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ውሳኔ፡ የካቲት 10፣ 1970

[107] ዝኒ ከማሁ፤ ኃይሉ ይመኑ ለኮ/ል ዶ/ር ፈለቀ፡ ሰኔ 26፣ 1970፤ የአሰብ ትራንስፖርት ልዩ ኮሚቴ የድርጅት አቋምና የአስተዳደር አመራር አዋጅ፡ ሰኔ 1970





ከሶማሊያ ወረራ መክሸፍ በኋላ የሐሰን ጉሌድ መንግስት ከኢትዮጵያ ጋር ለመግባባትና ለመተባበር በተደጋጋሚ ፍላጎት ማሳየቱን አልቀረም። በተለይም በውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ በሙሴ መሚን ብህድን በኩል ዓላማውን ለማሳካት ተደጋጋሚ ጥረቶች ሲያደርግ ቆየ። ነገር ግን ይህንን ጥረት አስመልክቶ በደርግ በኩል የነበረው ግንዛቤ የጅቡቲው የኢሳ ሶማሌ መንግስት ዓይነተኛውና የመጨረሻ ዓላማ አፋሮችን ከኢትዮጵያ መነጠል ነው። ጅቡቲያውያኑ ለዚህ እቅዳቸው መሳካት ሁለት የተግባራ አማራጮችን እንዳሰቡ ተገመተ። አንደኛው የወደፊት ዕጣ ፈንታቸው ያለየለትን የምድር ባቡሩንና የጅቡቲን ወደብ ተጠቃሚነት በመደራደሪያነት በማቅረብ በስልጣን ላይ ካለው የኢሳ ሶማሌ መንግስት ጋር የቀረበ ግንኙነት እንዲደረግና በዚያም ሳቢያ ኢትዮጵያን ከአፋሩ ወገን ማራራቅ፤ ሁለተኛው አማራጩ ደግሞ ኢትዮጵያ ከጉሌድ መንግስቱ ጋር ለመተባበር ካልፈለገችና የጅቡቲ አፋሮችን መርዳቷን ከቀጠለች በሡልጣን አሊሚራ የሚመራውን የብሎክ አፋር ውጥን በማጠንከር አፀፋዊ እርምጃ መውሰድ ነው።[109]

በስተመጨረሻ ግን ዘርፈ ብዙውን የኢትዮጵያ ጫና ተከትሎ በመስከረም 1971 በጅቡቲ የካቢኔ ለውጥ ተደረገ። የፕሬዚደንቱ ካቢኔ ሹም እና የአገሪቱ የፀጥታ ኃላፊ ሙሴ እስማኤል ኡመር ጊሌ በተለይ በጅቡቲ ለሚገኙ የኢትዮጵያ ዲፕሎማቶች እንደገለፁት የለውጡ ዋነኛ ዓላማ የውስጥ አስተዳደሩን ማሻሻል እና የጎሳ ሚዛኑን ማስተካከል ነበር። በማያያዝም የኢትዮጵያ መንግስት በጅቡቲ መንግስት ላይ አመኔታ እንዲኖረውና የሁለትዮሽ ግንኙነቱን ለማበላሸት የሚጥር የየትኛውንም የውጭ ኃይሎች ቅስቀሳ እንዳያዳምጥ ጥሪ አስተላለፉ።[110] ግንኙነቱን ይበልጥ ከማጠናከር አንፃር ግን የሁለቱ መንግስታት አለመተማመን ተጨማሪ የአንድ

[108] ስለዚህ ጉዳይ ቀጣዩን ምዕራፍ ተመልከት

[109] ውጉሚ፦ ጅቡቲ 57-D3 3ፉ በወቅታዊ ጉዳዮች ዙሪያ የቀረበ ማስታወሻ፡ የካቲት 1971

ዓመት ተኩል ቆይታን ጠየቀ። ከጅቡቲ ነፃነት በኂላም ኢትዮጵያ በየካቲት 1972 ብርሃኑ ዲንቃን የመጀመሪያው አምባሳደር አድርጋ ሾመች። በነዚህ ጊዜያት በጅቡቲ የኢትዮጵያን ዲፕሎማሲ ሲያከናውኑ የነበሩት እንደ አርጋው ካብታሙ ያሉ የደርግ የደህንነት ሰዎች ነበሩ።[111]

ነገር ግን ፕሬዚደንት ሐሰን ጉሌድ ኢትዮጵያን በኦፊሴል ለመጎብኘት ይዘውት የነበረውን ፕሮግራም በተደጋጋሚ ማራዘማቸው (ከህዳር 1972 ጀምሮ) ችግሮቹ በተገቢው ሁኔታ ያለመፈታታቸው አመላካች ነበር። አንዱ ያለመግባባት ነጥብ የነበረው በምድር ባቡሩ ላይ በተከታታይ ሲደረግ የነበረው ድርድር ነበር። በጅቡቲ በኩል ከፕሬዚደንቱ ጉብኝት በፊት ለጉዳዩ እልባት ለማበጀት የነበረው ግፊት ኢትዮጵያ በተከተለችው ሃዲዱን እንደ መያዣ የመጠቀም አማራጭ ምክንያት በተከታታይ ከሸፈ። ይልቁንስ የወታደራዊው መንግስት ምርጫ የነበረው በጥቃቅን የሁለትዮሽ ጉዳዮች ላይ ማተኮር ስለነበር በጅቡቲ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ፣ የመድን ድርጅት እና የባህር ትራንዚት ኮርፖሬሽን ቅርንጫፎች እንዲከፈቱና የውጭ ንግድ ሚኒስቴር ተወካይ ጽ/ቤት እንዲከፈት ተደረገ። በስተመጨረሻም የደርግ ጫና አይሎ ሐሰን ጉሌድ ኢትዮጵያን በመጋቢት 1973 ለሰባት ቀናት ጎበኙ።[112]

በአንድ በኩል የሶማሊያ ጦር ከኢትዮጵያ ተሸንፎ መውጣቱ በአካባቢው ያስከተለው የኃይል ሚዛን ለውጥ፣ በሌላ

[110] ውጉሚ፡- ጅቡቲ 51-D3 1፤ አርጋው ካብታሙ (በጅቡቲ ቆንስል አማካሪ) ለሻለቃ ዳዊት ወልደጊዮርጊስ፡ መስከረም 17፣ 1971

[111] ከአምባሳደር ብርሃኑ ዲንቃ በመቀጠል በውጭ ጉዳይ ለረጅም ጊዜ በጅቡቲ ጥናት ክፍል ያገለገሉት አምባሳደር ወሰን በሻህ (ከሐምሌ 1976-1986) ተሾሙ


[112] ውጉሚ፡- ጅቡቲ 57-D3 3፤ አምባሳደር ብርሃኑ ዲንቃ (ጅቡቲ) ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፡ የካቲት 18፣ 1973። ውጉሚ፡- ኢትዮ-ጅቡቲ ምድር ባቡር 1 2፤ አርጋው ካብታሙ (ጅቡቲ ኢምባሲ አማካሪ) ለዶ/ር ፈለቀ፡ መጋቢት 2፣ 1973






በኩል የኢትዮጵያን ሁለንተናዊ ጣልቃ ገብነት ተከትሎ የውስጥና የውጭ ደህንነት ዋስትና በማጣቱና የኢኮኖሚና ማህበራዊ ችግሮች ተደራርበው ባሳደሩት ጫና የጅቡቲ መንግስት ከኢትዮጵያ ጋር ያለውን ግንኙነት ለማሻሻል እንዳስገደደው መገመት ይቻላል።

ከፕሬዚደንት ጉሌድ ጉብኝት በኂላም በሁለቱ መንግስታት መካከል የተፈጠረው መግባባት በጋራ ጥቅምና መግባባት መርህ መንዝ ጀመረ። በጉሌድ ጉብኝት ወቅት ለቀጣይ ግንኙነት መሠረት የሆኑ በርካታ ውሎችና ስምምነቶችም ተፈረሙ። ከነዚህም መካከል የወዳጅነትና የትራድኦ ስምምነት፣ ጠቅላላ የትራንስፖርት ውል እና የምድር ባቡር ስምምነቶች ይገኙበታል። ከዚህም በተጨማሪ በጉብኝቱ ወቅት ጅቡቲ ከኢትዮጵያ ለምትገዛቸው ምርቶች መደጎሚያ የሚሆን 10 ሚሊዮን ብር ተፈቀደ። እንዲሁም በድሬዳዋ ከተማ ከፍተኛ 1 ቀበሌ 02 ክልል ለጅቡቲ ህዝብ አገልግሎት የሚውል 200,000 ካሬ ሜትር መሬት ተሰጠ።



ምንጭ፡ አዲስ ዘመን መጋቢት 13፣ 1973



ምንጭ፡ አዲስ ዘመን መጋቢት 13፣ 1973

ጓድ መንግስቱ እ.ኤ.አ. በ1984 ጅቡቲን በደፋ በጎበኙ ጊዜም የጋራ ኮሚሽን ማቋቋሚያ፣ የዲፕሎማቲክና ልዩ ፓስፖርት የያዙ የሁለቱ አገሮች ባለስልጣኖችና ግለሰቦች ያለ ቪዛ እንዲዘዋወሩ የሚያስችሉ ስምምነቶች ተፈረሙ:: የጋራ ኮሚሽኑ ለመጀመሪያ ጊዜ አዲስ አበባ በተሰበሰበበትም ወቅት ተጨማሪ ስምምነቶችና ፕሮቶኮሎች ተፈርመዋል:: ከነዚህም መካከል የቱሪዝም ማስፋፊያ ስምምነት፣ የጠረፍ አስተዳዳሪዎች/ ኮሚሽነሮች የጋራ ኮሚቴ ማቋቋሚያ እና የጋራ የደህንነት ኮሚቴ ማቋቋሚያ ስምምነት ይገኙበታል:: በመጨረሻም እ.ኤ.አ. በ1987 ሁለቱ መንግስታት የመንገድ ትራንስፖርት ስምምነቱን አጸደቁ::[113]

የእነዚህ ስምምነቶችና ፕሮቶኮሎች መፈረም ከጅቡቲ ነፃነት በኋላ በሁለቱ አገሮች መካከል ተፈጥረው የነበሩ ችግሮች እልባት ለማግኘታቸው አመላካች ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል:: ነገር ግን ሁሉን አቀፍ መግባባት ላይ ተደረሰ ለማለት አያስደፍርም:: የፕሬዚደንት ጉሌድን ጉብኝት ተከትሎ በነበሩት አምስት ተከታታይ ዓመታት በሁለቱም መንግስታት በኩል ችግሮች ቢፈጠሩ እንኳን የሌላኛውን ወገን አጸፋ በመፍራት ጥንቃቄ ሲደረግ ነበር:: በምሳሌነት ሊቀርብ የሚችለው ለጅቡቲ መንግስት ተቃዋሚዎች ጥገኝነት ላለመስጠት የተላለፉ ውሳኔዎች ናቸው:: በሂደት ግን ተቃዋሚዎችን የማደራጀቱ እና የመርዳቱ እንቅስቃሴ ስለመበራከታቸው መረጃዎች ያመላክታሉ::

በአገራቱ መካከል ለተፈጠረው መግባባት ዋነኛ አመላካች ተደርጎ ሊወሰድ የሚችለው በምሥራቅ አፍሪካ በይነ መንግስታዊ ድርጅት (Inter-Governmental Authority on Drought and Development, IGADD) ምሥረታና (ጥር 1978) ሂደት ወቅት የተስተዋሉ የጋራ ጥረቶች ናቸው:: የድርጅቱ ቋሚ መቀመጫ በጅቡቲ እንዲሆን ሐሳብ ያቀረበችውና ለዚሁም ተፈጻሚነት

[113] ውጉማ:- ኢትዮ-ጅቡቲ ግንኙነት፤ በሁለቱ አገሮች ግንኙነት ዙሪያ የቀረበ የጥናት ሪፖርት፡ ጥቅምት 7፤ 1984





የግዛቱን ባለሥልጣናት ያሳመነችው ኢትዮጵያ ነበረች:: ይህም ከሱዳን በኩል ተነስቶ የነበረውን ተመሳሳይ ጥያቄ ለማኮላሸትና ክፍለ አህጉራዊው ተቋም በአረብ/እስላማዊ መንግስታት (ሱዳንና ሶማሊያ) ተጽዕኖ ስር እንዳይወድቅ በማሰብ የተከናወነ ነው:: ለኢትዮጵያ ይህንን ለማስፈፀም በወቅቱ ወዳጅነቱን አድሶ ከነበረው ከጅቡቲ መንግስት የተሻለ አማራጭም አልተገኘም:: በተጨማሪም የጅቡቲ ሰዎች እንደዚት ጥያቄውን ማቅረብ እንዳለባቸው፣ አባል አገራቱን ለማሳመን መውሰድ ያለባቸው የቅድሚያ እርምጃዎች (initiatives) እንዲሁም የድርጅቱን ረቂቅ መተዳደሪያ ደንብ እንዲያዘጋጁ ወዘተ ጥቆማ ቀረበላቸው:: የኢትዮጵያ እርምጃ ከጅቡቲ ጋር የተመሰረተውን ወዳጅነት ከማጠንከሩም ባሻገር ክፍለ-አህጉራዊው ድርጅት በቅርብ ክትትል ሥር እንዲውል መንገድ ጠረገ::[114]

ኢትዮጵያም ኢጋድ የሚያራምዳቸውን የማህበራዊና ኢኮኖሚዊ የልማት ፕሮጀክቶች እውን ከማድረግ ባሻገር በዚሁ ተቋም ጥላ ሥር ከጅቡቲ ጋር የሚያስተሳስሩትን የጋራ እቅዶች ነድፋ ለተግባራዊነቱ መንቀሳቀስ ጀመረች:: ለምሳሌ በድርጅቱ የመጀመሪያ ሁለት ዓመታት ውስጥ ኢትዮጵያ አሥር ያህል ክፍለ-አህጉሩን የሚያስተሳስሩ ፕሮጀክቶች አቅርባ ከነዚሁ ውስጥ ስድስቱ በተግባር እንዲውል ማስጸደቅ ችላ ነበር:: ጅቡቲን በተመለከተ የተፈቀዱት በ150,000 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ወጪ ሊከናወን የታቀደው የአዲስ አበባ-ጅቡቲ የባቡር ሐዲድ መሥመር ጥገና እና 230,000 ሚሊዮን ዶላር በጀት የተመደበለት የኢትዮ-ጅቡቲ የኤሌክትሪክ ኃይል ማስተላለፊያ መሥመር ዝርጋታ ናቸው:: ከነዚህም በተጨማሪ ከፍተኛ በጀት የተያዘላቸው የአዘዞ-መተማ-ገዳሪፍ መንገድና ፓን አፍሪካን ቴሌኮሚኒኬሽን ማይክሮዌቭ መሥመር (ከሱዳን ጋር)፤ የፊለገወይን-ቀለም-ናማረጎት-ሎዲታኡንግ-ሎድዋር መንገድ (ከኬንያ ጋር) ይገኙባቸዋል::[115]

[114] Belete Belachew, *Black Ethiopia: a Glimpse into African Diplomacy* (Tsehai Publishers: Los Angeles, 2014), pp. 41-43.
[115] ዝኒ ከማሁ, pp. 48-49.

ነገር ግን በህዳር 1979 የጅቡቲ መንግስት በድብቅ ወደ ኢትዮጵያ ግዛት እንዲገባ ያደረገው የጦር መሳሪያ ጉዳይ በኢትዮጵያ በኩል ለተወሰዱ አጸፋዊ እርምጃዎች መነሻ ሆነ። መሳሪያው በኢትዮጵያ የሚገኙት የኢሳ ጎሳ አባላት ከአፋሮች ጋር ለሚያደርጉት ውጊያ እንዲውል የታሰበ መሆኑ የጅቡቲ መንግስት የውስጥ ፖለቲካ ሚዛኑን ከጋራ ድንበሩም ባሻገር ለማስረፅ እየሞከረ ስለመሆኑ አመላካች ተደርጎ ተወሰደ:: በወቅቱ በተካሄዱ የአፋር-ኢሳ ግጭቶች አፋሮች የበላይነት ነበራቸው:: በጅቡቲው የኢሳ-ሶማሌ መንግስት እምነት ይህ ሊሆን የቻለው የኢትዮጵያ መንግስት ከአፋሮች ጋር በመወገኑ ነበር:: የመሳሪያ አቅርቦቱ ይህንን ለመቀልበስ ያለመና በሂደቱም ኢሳዎችን ለማደራጀት ያቀደ እንደነበር በኢትዮጵያ በኩል ተገምቷል::[116]

በኢትዮጵያ በኩል ደግሞ የጎሳ ግጭቱን ለመፍታት አንዱ መፍትሄ የሆነውን አፋሮቹንና ኢሳዎችን በእኩል ትጥቅ ማስፈታት የሚለውን መፍትሄ ለመቀበል አልተፈለገም። ይልቁንስ የአፋሩን ወገን ማጠናከሩና የሐሰን ጉሌድን ተቃዋሚዎች ማደራጀቱ እና መርዳቱ የጅቡቲን ሁኔታ ለመቆጣጠር አማራጭ የተጽዕኖ መሳሪያ ሆኖ እንዲቀጥል ታቀደ::

1981 መጀመሪያዎቹ ላይ በኢትዮጵያ በኩል የሁለቱን አገሮች ግንኙነት እንደገና ለማጤን ያስገደዱ ውስብስብ ችግሮች ተከሰቱ:: ከነዚህ መካከል ዋነኛዎቹ በጅቡቲ እየተባባሰ የመጣው ጭፍን የሶማላይዜሽን ፖሊሲ እና የሥልጣን ውርርስን በሚመለከት በኢሳ ጎሳ ውስጥ የተከሰተው ትግል ነበሩ:: የሐሰን

[116] ውጉሚ፡- ጅቡቲ ልዩ ልዩ ፋይሎች 2 5፤ ብርሃኑ ባዩህ (ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር) ለተስፋዬ ገብረኪዳን (የአገር መከላከያ ሚኒስትር)፡ ህዳር 9፣ 1979፤ አምባሳደር ወሰን በሻህ ለአምባሳደር ይልማ ታደሰ (ውጉሚ የአፍሪካ መምሪያ ኃላፊ)፡ ህዳር 9፣ 1979፤ ብርሃኑ ባዩህ ለተስፋዬ ገብረኪዳን ለተስፋዬ ወልደሥላሴ (የሀገርና ሕዝብ ደህንነት ጥበቃ ሚኒስትር)፡ ህዳር 10፣ 1979፤ እንዳለ ተሰማ (የአገር አስተዳደር ሚኒስትር) ለብርሃኑ ባዩህ፡ ታህሳሥ 27፣ 1979






ጉሌድ መንግስት የተከተለው ኢሳ-ሶማሌዎችን በብዛት የማስፈርና የማደራጀት፣ አፋሩን ከምርጫ መዝገቦች የመሰረዝና የዜግነት መብት የመንፈግ እንዲሁም ከፖለቲካውና ኢኮኖሚው ሥልጣን የማግለል ይፋ ፖሊሲ፣ 75 ከመቶ የሚሆነውን የጅቡቲን ጦር ከኢሳ-ሶማሌ በተውጣጡ ኃይሎች ቁጥጥር ሥር ማድረጉ ወዘተ በኢትዮጵያ በኩል በአደገኝነት እንዲፈረጅ አደረገው:: አጠቃላይ ሂደቱ በኢሳውና በአፋሩ መሀከል የፈጠረው ከባድ ቅራኔ የጅቡቲን የውስጥ መረጋጋት ከማደፍረሱም በላይ በኢትዮጵያ ጥቅሞች ላይም አሉታዊ ተፅዕኖ እንደሚኖረው እሙን ነበር::[117]

ከነፃነት በኋላ በተደረጉ የሕዝብ ቆጠራዎች የኢሳ-ሶማሌውን ፍፁም የበላይነት ለማረጋገጥ ሲባል የጅቡቲ አፋሮች ብዛት የግዛቱን 20 ከመቶ ብቻ በሚወክል መልኩ ተስተካከለ:: ቀደም ባሉ ወቅቶች በቁጥር አብላጫ የነበራቸው አፋሮች በ1980ቹ መጀመሪያ ብዛታቸው በከፍተኛ ሁኔታ እንዲቀንስ ተደርጎ 60,000 ብቻ እንደሆኑ በይፋ ተገለጠ:: የኢሳ-ሶማሌው ቁጥር በአንፃሩ በ1947 በተደረገው ቆጠራ ከነበረበት 16,000 ከፍተኛ ዕድገት በማሳየት ወደ 200,000 ከፍ እንዲል ተደረገ:: ይህ በግዛቱ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ህልውና ውስጥ የኢሳዎችን ፍፁም የበላይነት ለማረጋገጥ የተወጠነ እቅድ ነበር:: በተጨማሪም እንደ አገር አስተዳደር፣ ኢኮኖሚና ፋናንስ፣ ውጭ ጉዳይ፣ ንግድ፣ ትራንስፖርትና ቱሪዝም፣ ወደብና የባህል ጉዳይ ያሉ ቁልፍ የሚኒስትር መሥሪያ ቤቶች በኢሳ-ሶማሌዎች የተያዙ ሲሆን የመከላከያ ሚኒስትርነቱ ለአፋር ቢሰጥም ዕውነተኛ ሥልጣኑ የፕሬዚደንቱና የኢታ ማዦር ሹሙ ነበር::

አፋሮቹ በጎጥ መከፋፈላቸው የጋራ ግንባር እንዳይመሠርቱ ካገዷቸው ምክንያቶች ዋነኛው ነበር:: በሂደትም ከጅቡቲ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ህይወት በከፍተኛ ሁኔታ የተገለሉበት

[117] ውጉሚ፡፤- ኢትዮ-ጅቡቲ ግንኙነት፤ ስለ ጅቡቲ የቀረቡ የጥናት ሪፖርቶች፡ ጥቅምት 13፣ 1981፤ ጥቅምት 7፣ 1984.

ደረጃ ላይ ደረሰ። በተቃራኒው የጉሌድ ወገኖች ከኢትዮጵያ ጋር የተፈጠረውን የመግባባትና የመተባበር ፖሊሲ በመጠቀም የኢኮኖሚና የፖለቲካ ጡንቻቸውን ይበልጥ አጎለበቱ። በተለይ በኢኮኖሚው ረገድ በባቡርና በመንገድ ትራንስፖርት የሚካሄደው ተመላላሽ ንግድ በኢሳ-ሶማሌዎች ተያዘ፣ የጫት ንግድ በሞኖፖል ለአንድ ኢሳ-ሶማሌ ተሰጠ፣ የአትክልትና ፍራፍሬ እና የቁም ከብት ንግድ በኢሳ-ሶማሌዎች እጅ ሆነ ይህንኑም ተከትሎ የኮንትሮባንድ ንግዱንም ተቆጣጠሩት። የባበሩ መስመር ሙሉ በሙሉ በኢሳ-ሱማሌ ግዛት ውስጥ ማለፉ ለዚህ ዕውነታ የበኩሉን ድርሻ አበርክቷል።[118]



የጅቡቲ-አዲስ አበባ ምድር ባቡር መሥመር በጅቡቲ ግዛት ውስጥ (ምንጭ፡ ውጉሚ)

[118] ዝኒ ከማሁ. Schraeder, 206-211.






በኢትዮጵያ በኩል የጅቡቲን ጉዳይ ለማጤን ያስገደደው ሁለተኛው ምክንያት በኢሳዎች መካከል የተከሰተው የሥልጣን ሽኩቻ ነበር። የፕሬዚደንት ጉሌድ በዕድሜ መግፋት (በጊዜው ከ70 ዓመት በላይ መሆን) እና ጤና ማጣት በኢሳው መካከል ለተከሰተው የሥልጣን ፉክክር እና መከፋፈል ዋነኛው መንስኤ ነበር። ከህገ መንግስታዊ ድንጋጌና ከፓርቲው ሥነ ሥርዓት ውጭ በኢሳዎች የጎሳ ፖለቲካ ላይ የተመሠረተው የሥልጣን ውርርስ ሌላኛው የችግሩ ምንጭ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል። ኢሳዎች በሁለት ታላላቅ ቤቶች (አብጋልና ዳሎል) የተከፈሉ ሲሆን አገራቱን የመምራቱ ሥልጣን በሁለቱ ቤቶች ተወካዮች በፈረቃ እንዲያዝ የሚያስችል ያልተፃፈ ስምምነት እንደነበር ይታመናል። የውጥረቱ አንደኛው መነሻ በሥልጣን ላይ የሚገኘው የአብጋል ቤት ሥልጣኑን ለማስቀጠል ካሳየው ፍላጎት ባሻገር ከራሱ ንዑስ ጎሳ (ማማሳን) አባላት መካከል ቀጣዩን መሪ ለመሾም መፈለጉ ነው። በጅቡቲ ከሶማሌይዜሽን እንቅስቃሴው ጎን "የማማሳናይዜሽን" ፖሊሲ መካሄዱ እና የመንግስቱን ስልጣን በጉሌድ የሥጋ ዘመዶች ቁጥጥር ሥር ለማቆየት እየተደረገ ያለው ጥረት በሶማሊያ እንደታየው የሥልጣን ተዋረዱ ቤተሰባዊ አዝማሚያ እየያዘ ስለመምጣቱ አመላካች ተደርጎ ተወሰደ።

ሁኔታውን ይበልጥ ያወሳሰበው የሥልጣን ውርርሱ ቤተሰባዊ ገፅታ መያዙን የሚቃወሙ ማማሳኖች መኖራቸውና ይህም በአብጋል ቤት ውስጥ የፈጠረው ልዩነት፤ ጉዳዩ በአብጋልና በዳሎል ቤቶች መካከል ይፋ የሆነ ሽኩቻ ማስከተሉ፤ እና ይህን ተከትሎ የፕሬዚደንት ጉሌድን መንግስት የሚቃወሙ የኢሳ ወገኖች በውጭና በውስጥ መደራጀት መጀመራቸው ነው። በተከሰተው የሥልጣን ሽኩቻ በተለይ ኢስማኤል ኦማር ጌሌ፣ ሙሚን ባህዶን ፋራህ፣ ኢስማኤል ጌዲ ሀሬድ እና ሞሀመድ ጃማ ኤላቤ ለፕሬዚደንታዊው ወንበር ዋነኞቹ ተቀናቃኞች እንደሆኑ ተለይቶ ታወቀ። የስልጣን ሽኩቻውም በሚያዝያ 1991 ሲጠናቀቅ ኢስማኤል ኦማር ጌሌ አጎታቸውን ተክተው ቀጣዩ የጅቡቲ ፕሬዝደንት ሆኑ።[119]

[119] Amedee Bollee, "From French Outpost to US Base", in *Review of African Political Economy*, Vol. 30, No. 97 (Sept. 2003), 481-484.




የጅቡቲ-አዲስ አበባ ምድር ባቡር መሥመር በጅቡቲ ግዛት ውስጥ
(ምንጭ፡ ወ.ገ.ሚ.)

በዚህ መካከል በኢትዮጵያ በኩል የነበረው ግንዛቤ እንደሚያመለክተው ችግሩን ለዘለቄታው ለመፍታት ብቸኛ መፍትሔ ተደርጎ የተወሰደው የሁለቱን ዋነኛ ጎሳዎች (አፋር እና ኢሳ) ሚዛናዊ የሥልጣን ክፍፍል ማረጋገጥ ነው:: በጅቡቲ የተከሰቱት ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ማህበራዊ ችግሮች ቀድሞውንም በኢትዮጵያ በኩል ተጠንስሰው ለነበሩ ተቃዋሚዎችን የማደራጀትና የመርዳት ፖሊሲ መጠናከር በር ከፈቱ::

ከ1978 ጀምሮ በኢትዮጵያ በፖለቲካ ጥገኝነት እንዲኖሩ የተፈቀደላቸው የቀድሞው የጅቡቲ ወታደራዊ መረጃ ኃላፊ ኤደን ሮብሌ አዋሌህ (ኢሳ) ለዚሁ የመንግስት ውጥን መንደርደሪያ ሆኑ:: ግለሰቡ ድንበር ጥሰው ወደ ኢትዮጵያ ከገቡበት ጊዜ አንስቶ ወደ ፈረንሳይ ተሻግረው ከመሰል ተቃዋሚ ቡድኖች ጋር ጥምረት እስከፈጠሩ ድረስ በመንግስት አስፈላጊው ድጋፍ ሲደረግላቸው ቆይቷል:: የሚመሩት Mouvement national djiboutien pour l'instauration dela democratie (MNDID) የተሰኘው ንቅናቄ በተደጋጋሚ በጅቡቲ ከተማ ውስጥ ጥቃት ሲያደርስም ሁኔታው ከኢትዮጵያ ባለሥልጣናት እውቅና ውጭ አልነበረም:: በጥር 1982 MNDID ከዋነኛው የአፋር ተቃዋሚ ቡድን Front Democratique de Liberation de Djibouti (FDLD) ጋር በመዋሃድ l'Union des Mouvements Democratiques (UMD) ሲመሰረትም ሂደቱ በኢትዮጵያ እውቅናና ምርቃት የተከናወነ ነበር:: FDLD በጅቡቲ ነፃነት ዋዜማ ተመስርቶ የነበረውን Mouvement Populaire Djiboutien — MPL የተሰኘ የአፋር አንጃ የተካ ነው::[120]

[120] ውጉሚ፡- ጅቡቲ ልዩ ልዩ ፋይሎች 2 5፤ ሌ/ኮ ዱሬሳ ዋማ (በሀገርና ሕዝብ ደህንነት ጥበቃ ሚኒስቴር የጥበቃና አስቸኳይ ጉዳዮች ማባሪያ ዋና መምሪያ ኃላፊ) ለአምባሳደር ይልማ ታደሰ (ውጉሚ አፍሪካ መምሪያ ኃላፊ)፡ ጥር 18፣ 1979፤ አምባሳደር ይልማ ታደሰ ለአምባሳደር ወሰን በሻህ (ጅቡቲ)፡ ግንቦት 4፣ 1979፤ አምባሳደር ሀብተማርያም ሥዩም (ፓሪስ) ለአምባሳደር አሰፋ ወልዴ (ውጉሚ ተጠባባቂ ሚኒስትር)፡ መጋቢት 22፣ 1981፤ አምባሳደር ሀብተማርያም ሥዩም (ፓሪስ) ለተስፋዬ ዲንቃ (የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር)፡ የካቲት 16፣ 1982፤ ተቀዳ ዓለሙ (የአፍሪካ መምሪያ ኃላፊ) ለሞቃዲሾ ኤምባሲ፡ ጥቅምት 14፣ 1983፤ ፓሪስ ኤምባሲ ለውጉሚ፡ ሐምሌ 26፣ 1983. Shehim and Searing, 224-226. Schraeder, 210-212.





ኤደን ሮብሌ ከFDLD መሪ ከሞሐመድ አዶኢታ ጋር በጥምር (co-president) አዲሱን አንጃ መምራት ጀመሩ:: UMD ጅቡቲና ኢትዮጵያን በአንድ የኢኮኖሚ ክልል (Espace Economique) የማጣመር ፖሊሲን እንደሚያራምድም ይፋ አደረገ:: አጠቃላይ ሂደቱ ኢትዮጵያ ያቀደቻቸው ብሔራዊ ጥቅሞቿን የማስጠበቅ እና የጅቡቲ ዋነኛ ጎሳዎች የእኩል ተጠቃሚነት ፖሊሲ አተገባበር አካል ስለመሆኑ አመላካች ነው:: አዲሱን የተቃዋሚዎች ህብረት ከጅቡቲ መንግስት ጋር ለማደራደርና ለማስታረቅ የቀረበለትን ጥያቄ የኢትዮጵያ መንግስት ችላ ማለቱም ከበስተጀርባ የነበረውን ድብቅ አጀንዳ ያንፀባርቃል:: በተጨማሪም Action pour la Ravision de l'ordre a Djibouti (A.R.O.D.), Front pour la Restauration du Droit et de l'Egalite (F.R.D.E.) እና Front de la Rasistance Patriotique de Djibouti (F.R.P.D.) የተሰኙ የአፋር ተቃዋሚ አንጃዎች በሐምሌ 1983 ተዋህደው Front pour la Restauration de l'unite et de la Democratie (F.R.U.D.) የጋራ ግንባር መሠረቱ::[121]

የጋራ ግንባሩ መሪዎች አዋድ ሀሰን፣ ዓሊ ማኬ እና ሞመድ አራሚስ ቀድሞ M.P.L. በኋላ F.D.L.D. የሚባለው የአፋሮች ድርጅት አባል የነበሩና ከ900 በላይ ከሆኑ ወገኖቻቸው ጋር እ.ኤ.አ. ከ1976 (1968/69ዓ.ም.) አንስቶ በወታደራዊው መንግስት እርዳታና ድጋፍ ፖለቲካዊና ወታደራዊ ሥልጠና ያገኙ ናቸው:: ፍሩድ (F.R.U.D.) የተሰኘው የአፋር ተቃዋሚ አንጃዎች ህብረት ከሐምሌ 1983 ጀምሮ በጅቡቲ የተከሰተውን የፖለቲካ ሽኩቻ በዋነኝነት ከማቀጣጠሉም ባሻገር በኢትዮጵያና በጅቡቲ ግንኙነት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳደረ እንቅስቃሴ ማድረግ ቻለ::

[121] ዝኒ ከማሁ፤ አምባሳደር ወሰን በሻህ ለሥዩም መስፍን (ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር) ስለ ጅቡቲ ወቅታዊ ሁኔታ የቀረበ ማስታወሻ፡ ታህሳሥ 5፣ 1984:: Schraeder, 203-221. Kadamy, 513-519.